# ኢትዮጵያ፡ የእግዚአብሔር መንግሥት አገልግሎት።

# Ethiopia: The Kingdom of God Services

ኢትዮጵያ፡ የእግዚአብሔር መንግሥት መኾኗን፥ ኢትዮጵያውያንም፡ የቅዱሱ ኪዳን ሕዝብ መኾናቸውን ለማስረዳት፥ የ"ኢትዮጵያ" እና "የኢትዮጵያውያን" የኾነውንም ኹሉ ለመጠበቅና ለማሳወቅ።
To reveal the truth about Ethiopia's entity as the Kingdom of God and Ethiopians' identity as the People of the Holy Covenant with God; and so, to safeguard and promote all that pertains to Ethiopia and Ethiopians.

---

መስከረም ፳፩ ቀን፥ ፲፱፻፺፯ ዓ.ም.

ይድረስ፦ ለክቡር የመቶ አለቃ ግርማ ወልደ ጊዮርጊስ፣
የኢትዮጵያ ርእሰ ብሔር፣
ብሔራዊ ቤተ መንግሥት፣
አዲስ አበባ፣ ኢትዮጵያ።

<u>ጉዳዩ፡ "ድሮና ዘንድሮ" ስለሚለው መጽሓፍዎ፡ ግልጽ ደብዳቤ፥ ከታላቅ መልእክት ጋር።</u>

ክቡር ርእሰ ብሔር!

ለታላቁ ማዕርግዎ በሚገባው ኢትዮጵያዊ ባህል፡ የአክብሮት ሰላምታዬን፡ አቀርብልዎታለሁ። እግዚአብሔር ይመስገን፡ እኔ፡ ከነቤተሰቤ ደህና ነኝ።

በቅርቡ፡ ወደተባበሩት የአሜሪካ ግዛቶች መናገሻ ከተማ፡ ወደዋሽንግተን ዲ.ሲ. መጥተው በነበረ ጊዜ፡ በልጅዎ፡ በመሓንዲስ ሶምሶን ግርማ አማካይነት የላኩልኝ፡ "ድሮና ዘንድሮ" የሚለው መጽሓፍዎ ደረሰኝ፣ እግዚአብሔር ይስጥልኝ!

ቀደም ብሎ፡ በልጅዎ፡ በመምህርት መና ግርማ በኩል ደርሶዎ በነበረው፡ በተለይ፡ "ኢትዮጵያ፡ የዓለሙ መፋረጃ!" በሚለው መጽሓፌ መቅድም ውስጥ የሠነዘርሁት አስተያየት፡ በዚህ ድርሰትዎ ታትሞ መውጣትና በይፋ ለሕዝብ መናኘት፡ እውን ኾኖና ተፈጽሞ በማየቴ፡ ደስ አለኝ።

ያም አስተያየቴ፡ "*በእኔ፡ በግሌ በኩል ያለውን ብቻ አስታውሼ የጻፍሁት እንጂ፡ እያንዳንዱ ኢትዮጵያዊ ደግሞ፡ በእየበኩሉ የደረሰበትን፥ ያየውንና የሚያውቀውን ኹሉ፡ ሳይፈራና ይሉኝታ ሳይዘው፥ ወይም* ***<u>ሌላ ጥቅም ሳያታልለው፡</u>*** ***<u>በእግዚአብሔር እውነት፡</u>*** *በግልጽ የሚናገርና የሚጽፍ ቢኾንማ ኖሮ፡ የዛሬውም ኾነ የወደፊቶቹ ትውልዶች፡ የቱን ያህል በተጠቀሙ ነበር፣ ...ይህ ዓይነቱ አሠራር፡ ቀደም ብሎ ተለምዶ ቢኾን ኖሮ፡ ማለትም፡ በዚህ ዘመናችን፥ ከዚያም በፊት፡ የኾነውን ኹሉ፡ ትውልዱ፡ በግልጽ እንዲያውቀው ተደርጎ ቢኾን ኖሮ፡ አገራችንን፡ ዛሬ ደርሶባት ከሚታየው ጥፋትና ውድቀት ማዳን በተቻለ ነበር።*" የሚለው ነው።

በዚህ ረገድ፡ ጤናማ ህልውናችንን፡ ሲጠናወትና ሲያጥመነምን ከኖረው የጠንቅ ክምችት መካከል፡ አንዱን ለማስወገድ፡ መጽሓፍዎ፡ የበኩሉን አስተዋጽዖ የሚያበረክት፥ በአርአያነቱም የሚጠቅም ስለኾነ፡ ያቀረቡትን ድርሰት፥ በእርሱም አማካይነት፡ የፈጽሙትን ተግባር፡ በዚህ መልኩ፡ ማድነቄን ልገልጽልዎ እወድዳለሁ።

...፪

---

መልእ. ሣ. ቁ. ፰፻፲፪፣ ስልክ ቁ. ፲፮-፲፰-፹፭፣ ፳-00-፹፭፣ አዲስ አበባ፣ ኢትዮጵያ።
P. O. Box 812, Tel. Nos. 16-18-85; 20-00-85, Addis Abeba, Ethiopia.
P.O.Box 43262, Washington, DC 20010-9262 U.S.A.
Tel. (301) 587-8074 ~ Fax: 301-587-1971 ~ E-mail: ekogyesus@aol.com
Website: www.ethkogserv.org

መጽሓፉን በማነብበት ጊዜ፡ በተለይ፡ በግል፡ የቅዱሱ ኪዳን ኢትዮጵያዊ ማንነቴን፥ ይልቁንም፡ የእግዚአብሔር መንግሥት ለኾነችው ኢትዮጵያ፡ በቃል ኪዳን የተቀበልሁትን፡ ተልእኮ፡ በይፋ አውጇ የምኖር ኢትዮጵያዊ አገልጋይ በመኾኔ፡ ይህንኑ ኃላፊነቴን የሚመለከቱና የነኩ፡ አንዳንድ፡ መሠረታውያን ጉዳዮችን፡ በውስጡ አግኝቻለሁ፤ እነዚህንም ጉዳዮች፡ ከዚሁ ማንነቴና ኃላፊነቴ የተነሣ፡ በዝምታ፥ ወይም፡ በቸልታ፥ ወይም፡ በይሉኝታ፥ ወይም፡ በሓሜታ፥ ወይም፡ በዋይታ ሳልፋቸው የማልችል በመኾኔ፡ ተገቢውን አስተያየት፡ በግልጽ ልሰጥባቸው ተገድጃለሁ፡፡ ስለዚህ፡ ይህን ደብዳቤ የጻፍሁልዎ፡ ይኸንኑ ግዳጄን "ልፈጽም!" ብዬ መኾኑን፡ እርስዎም፡ አውቀውት፡ አሳቤን፡ በጽሙና እንዲያዳምጡኝ፡ ፈቃድዎንና ትዕግሥትዎን፡ በትሕትና እጠይቃለሁ፡፡

፩ኛ፡- በመጽሓፍዎ ውስጥ፡ ኢትዮጵያዊው የሥነ ጽሑፍ፥ የሆህያትና የአኀዛት ሥርዓት ተስተካክሎና ተሟልቶ አለመቅረቡን፡ አስቀድሜ ልጠቁም እወድዳለሁ፡፡ በተለይ፡ በስምዎ ተዘጋጅቶና ታትሞ፡ ለሕዝብ የተሠራጨው፡ ይህ ድርሰት፡ እንዲህ ኾኖ መቅረቡ፡ አኹን፡ እርስዎ፡ ከሚገኙበት፡ ከታላቁ ኃላፊነትዎ አኳያ ሲመዘን፡ አሉታዊ ምሳሌነቱ፡ በዚሁ ውርሳችን ላይ የሚያስከትለው ተጽዕኖ፡ በቀላል ሊገመት አይቻልም፡፡ ስለዚህ፡ ብርቱ ጥንቃቄ ሊደረግበት ያስፈልግ የነበረ ግዳጅ መኾኑን እየገለጽሁ፡ ለዚህ እውነታ፡ ከዚህ የሚከተሉትን ጥቂት ማስረጃዎች፡ ለዓይነት ያህል አቀርባቸዋለሁ፡-

ሀ. "የቀብር ሥርዓትን መወሰን" በሚለው ርእስ ሥር፡ በኢትዮጵያዊው ትክክለኛ የአኀዝ አጻጻፍ ሥርዓት፡ ፻፳፯ ተብሎ ሊጻፍ በሚገባው፡ በገጽ 127 ላይ፡ "ለንብረ ኡድ ቄስ ኤርሚያስ" ተብሎ የተጻፈው ስም፡ አንዱ ምሳሌ ይኾናል፤ የዚህ ስም ቃላት፡ ሊጻፉ የሚገባቸው፡ "ለንቡረ እድ ኤርምያስ" ተብሎ ነበር፡፡ በሌሎቹ፡ በማንኛዎቹም፡ የባዕዳን ቋንቋዎች፡ አንድ ቃል፡ ከየራሳቸው ሥነ ጽሑፍ ውጪ በኾነ ሌላ መልክ፡ ያለሥርዓት ተጽፎ ቢቀርብ፡ የቱን ያህል፡ እንደሚያስነውርና እንደሚያስነቅፍ፡ የየቋንቋውና የየሥነ ጽሑፉ ባለቤት የኾነው፡ እያንዳንዱ ዜጋ ያውቀዋል፡፡ "ቄስ" የሚለውም ቃል፡ ሥልጣነ ክህነት ያለው ኢትዮጵያዊ፡ የሚጠራበትና የሚታወቅበት የማዕርግ ስም ሲኾን፡ እኔም፡ የአኵስም ጽዮን ንቡረ እድ እስከኾንሁበት ጊዜ ድረስ፡ ስጠራበት ቆይቻለሁ፤ እስከዛሬና አኹን፥ ወደፊትም፡ ስጠራበትና ስታወቅበት፡ እጅግ ደስ ብሎኝ እቀበለዋለሁ፡፡ ይኹን እንጂ፡ የቅስናው ሥልጣነ ክህነት፡ "ንቡረ እድ" በሚለው ማዕርግ ውስጥ የታቀፈ ስለኾነ፡ እንኳንስ፡ "ንብረ ኡድ" ተብሎ፡ በስሕተት ተጽፎ ይቅርና፡ በትክክልም ቢኾን፡ ኹለቱንም ማዕርጋት ባዋሓደ መልክ፡ "ንቡረ እድ ቄስ" ተብሎ አብሮ አይጻፍም፤ አላዋቂነትን የሚያመለክት ድርጊት ነው፡፡

ይህ አድራጎትዎ፡ አዲስ፥ ወይም፡ እንግዳ ነገር ኾኖ፡ አላስገረመኝም፡፡ ምክንያቱም፡ እንኳንስ አኹን፡ የኢትዮጵያና ኢትዮጵያዊ የኾነው ቊም ነገር ኹሉ፡ እንዳይታወቅ፥ እንዲያውም፡ በይፋና በአዋጅ፡ ውድቅ እንዲኾን በተደረገበት፥ እንዲጠፋም በሚጣርበት ጊዜ ይቅርና፡ ለይስሙላ፡ "ታውቆና ተከብሮ ይገኝበት ነበር!" ተብሎ በሚታሰብበት፡ በአጼ ኃይለ ሥላሴ ዘመን እንኳ፡ ከምን ዓይነቱ ጕሥቍልናና ዝቅጠት ላይ ደርሶ እንደነበር የሚያመለክቱ፡ በግሌ የደረሱብኝ፡ አንዳንድ ገጠመኞች ስለነበሩ፡ እዚህ ላይ፡ ኹለቱን ያህል፡ ለምሳሌ ያህል አወሳቸዋለሁ፡-

-አንደኛው፡ የአኵስም ጽዮን ንቡረ እድ ኾኜ መሾሜን የሰማች፡ አንዲት፡ በአዲስ አበባ የምትኖር ዘመዴ፡ እጅግ ተደስታ፡ በቅርቧ ለሚገኙት ቤተሰቦቿና ጎረቤቶቿ፡ በቃል፥ በሩቅ ለሚኖሩት ዘመዶቿና ወዳጆቿም፡ በስልክ፡ "ወንድሜኮ፡ 'ዕብነ በረድ' ኾኖ ተሾመልኝ!" እያለች፡ ደስታዋን፡ በጋለ ስሜት በመግለጽ፡ የፈጸመችው የስሕተት ድርጊት ነው፤ ለእርሷም፡ ስሕተቷን ባብራራሁላት ጊዜ፡ የካህን ወገን ኾና፡ ራሷን፡ ያን ወደሚያህል ያላዋቂነት ውርደት በመጣሏ፡ ስለተሰማት ኀፍረት፡ በፊቷ ላይ ያየሁት ድንጋጤ ትዝ ይለኛል፡፡

-ሌላው ደግሞ፡ ለሥራ ጉዳይ፡ ከአኵስም፡ ወደአዲስ አበባ መጥቼ፡ ቀጠሮ ለመያዝ፡ በጠዋቱ ሰዓት፡ ወደአንድ ከፍተኛ የአጼው መንግሥት ባለሥልጣን ጽሕፈት ቤት ስልክ ደውዬ፡ ከልዩ ጸሓፊዋ በተሰጠኝ መልስ የሚጀምረው፡ የቃል ልውውጥ ነው፡- እርሷም፡ “ማን ልበል?” አለችኝ፤ “ንቡረ እድ ኤርምያስ!” አልኋት፤ የማነጋግራት በወንድ ድምፅ መኾኑን እየሰማች÷ ነገር ግን፡ የስሙ ዓይነት፡ “የሴት ነው!” ብላ ስላመነች÷ እኔም፡ ቀጠሮ ለመያዝ፡ የደወልሁ ሠራተኛ መስያት ይመስለኛል፡ “'ወይዘሮ' ናቸው? ወይስ፡ 'ወይዘሪት?'” አለችኝ፤ “አይ! ኹለቱም አይደለሁም!” አልኋትና፡ ይህን ነገር፡ እንደኢትዮጵያዊትነቷ፡ ገና በሕፃንነቷ፡ በቤተሰቧ ዘንድ÷ በልጅነቷም፡ በትምህርት ቤት፡ ልታውቀውና ልትማረው ይገባት የነበረ መኾኑን በመግለጽ፡ የንቡረ እድን ትርጕም፡ ባጭሩ አብራራሁላት፤ እርሷም፡ በተሳሳተው አነጋገርዋ አዝናና አፍራ፡ ይቅርታ እንደጠየቀችኝ÷ በመጨረሻም፡ የቀጠሮውን ጊዜ፡ እንደምታስታውቀኝ አመልክታኝ፡ እንደተሰነባበትን፡ ይህንም አስታውሳለሁ፡፡

ለ. እርስዎ፡ አኹን ከያዙት ታላቅ ደረጃ የተነሣ፡ በስምዎ ታትሞ፡ ለሕዝብ በተሠራጨ መጽሓፍ ውስጥ፡ በሙሉ፡ ከባዕዳኑ አ'ነዛት በቀር፡ ኢትዮጵያዊው አ'ነዝ፡ በአንድም ቦታ፡ ለምልክት እንኳ ተጽፎ ባለማየቴ አዝኜ፡ “በዚህ ጉዳይ ላይ፡ ምናልባት፡ እኔ ያልሰማሁት፡ 'ኢትዮጵያዊው የግእዝ ቍጥር ተወግዶ፡ የባዕዳኑ ተተክቷል!' የሚል፡ የይፋም ኾነ የምስጢር አዋጅ ተላልፎ ይኾን?” ብዬ እስከማሰብ መድረሴን፡ ልሸሽግዎ አልፈልግም፡፡

በዚህ ረገድ፡ “በተለይ፡ ለዚህ ቅርስ ጥበቃ፡ የበለጠ ኀላፊነት አለባት!” የምትባለው፡ የኢትዮጵያ ቤተ ክህነት፡ በዛሬዎቹ ተጠሪዎቿ አማካይነት፡ በዚሁ ጸረ-ኢትዮጵያ ዘመቻ ላይ፡ ቀንደኛና ቀዳሚ ተባባሪ ኾና፡ የባዕዳን መሣሪያነቷን ስላረጋገጠች፡ የእርስዎ ድርጊት፡ ይህን ያህል፡ እንግዳ ነገር ኾኖ ሊያስገርመኝ አልቻለም፡፡ ምናልባትም፡ “ስሕተቱ፡ የሕይወት ታሪክዎን እየነገሩዋቸው ከጻፉት አዘጋጅ÷ ወይም፡ በመቀመሪያው ከቀረፁት ባለሙያዎች ሊኾን ይችላል!” የሚል ግምትም ሳይሰማኝ አልቀረም፤ ይኹን እንጂ፡ የዚህን ግምቴን ትክክለኛነት፡ ለይተው የሚያውቁት እርስዎ ቢኾኑም፡ የመጨረሻው ማጣሪያ ምንባብ፡ በእርስዎ በኩል መካኼድ ስላለበት፡ ክቡርነትዎ፡ ከጕድለቱ ተጠያቂነት የሚያመልጥ አይመስለኝም፡፡ ይህን ርእሰ ነገር በሚመለከት፡ በተለይ፡ “ኢትዮጵያ፡ የዓለሙ መፋረጃ!” በሚለው መጽሓፌ ውስጥ፡ በሚበቃ ያተትሁበት ስለኾነ÷ እርስዎም ሳይመለከቱት እንዳልቀሩ ስለምገምት፡ የአ'ነዛት ትችቴን፡ በዚሁ እገታዋለሁ፡፡

እዚህ ላይ ግን፡ በትዝታ መንፈስ እንዳቀርበው የምገደድ፡ አንድ ጥያቄ አለ፤ ይህም፡ “እርስዎና እኔ፡ መሥራች አባሎች ኾነን፡ በ፲፱፻፶፪ ዓ. ም.፡ የኢትዮጵያ ድርሰት ማኅበርን ያቋቋምነው÷ ከመሥራች አባልነታችንም በላይ፡ እርስዎ፡ ለዓቃቤ ንዋይነት÷ እኔ፡ ለዋና ጸሓፊነት ተመርጠን ስናገለግል የነበርነው፡ ከቶ፡ ለምን ኖርዋል? እንድንጠብቃቸው፡ በዚያን ጊዜ ከተቀበልናቸው የማኅበሩ ዓላማዎችና አደራዎች መካከል፡ ይህ የሥነ ጽሑፋችን ቅርስ፡ አንዱ አልነበረምን?” የሚል ነው፡፡

፪ኛ፡- የቀብር ሥርዓትን በመወሰኑ ረገድ፡ ከእርስዎ ጋር ስለነበረኝ ተባባሪነቴ፡ በመጽሓፍዎ ውስጥ ለቀረበው ሓተታ፡ ተገቢውን ማስተካከያና ማሟያ መስጠት አስፈላጊ ኾኖ አግኝቼዋለሁ፡፡ በዚያን ጊዜ፡ ስለቤተ ክህነቱ አስተዳደርና አመራር፡ በነበረብኝ ኀላፊነት፡ ቤተ ክህነቱ፡ ኢትዮጵያዊ መሠረቱን እንደጠበቀና ኢትዮጵያዊ መልኩንም እንደያዘ፡ ሥራውንና አገልግሎቱን ለማቀላጠፍ፡ አስፈላጊና ጠቃሚ በኾነው ዘመናዊ መንገድ፡ የሚሻሻልበትን መስመር መወጠንና ማጥናት÷ የጥናቱንም ውጤት፡ ከዕቅድ ጋር፡ ለወሳኙ ጉባዔ አቅርቦ የተወሰነውን በሥራ ላይ ማዋል፡ የጠቅላይ ሥራ አስኪያጃጅነቴ ግዳጅ በመኾኑ፡ ይህም የቀብር ነገር፡ የወቅቱ አሳሳቢ ችግር ስለነበረ፡ በሥጋዊው በኩል ብቻ ሳይኾን፡ በሃይማኖታዊውና በመንፈሳዊው ጎኑ ጭምር፡ ያስከተለው ጠንቅ ተጠንቶ÷ መፍትሔው በሥራ ላይ እንዲውል የተደረገ ተግባር ነው፡፡

ኢትዮጵያ፡ መንግሥታዊ ሥራዋን የምታካኺደው፡ በቤተ ሕዝቧ፥ በቤተ ምልክናዋና በቤተ ክህነቷ አማካይነት በመኾኑ፡ እኔም፡ ይህን ተግባር፡ እንደሌላው አገራዊ፥ ሕዝባዊና መንግሥታዊ ጉዳይ፡ ከውጥኑ ጀምሮ፡ እስከፍጻሜው ድረስ የተከታተልኩት፡ ከሚመለከታቸው፡ የመንግሥቱ የአገልግሎት ዘርፎች፡ ሹማምንትና ሠራተኞች ጋር በመመካከርና በመተባበር ስለነበረ፡ እርስዎም፡ በዚያን ጊዜ፡ በቤተ ሕዝቡ ውስጥ በነበረዎ የአገልግሎት ተጠሪነት፡ በዚህ መልኩ፡ ተሳትፈው፡ ኢትዮጵያዊ ግዳጅዎን ለመፈጸም ችለዋል ማለት ነው። ይህን ስለመሰለው አሠራራችን፡ እዚህ ላይ ምሳሌን መጥቀስ ቢያስፈልግ፡ እርስዎ ጭምር በሚያስታውሱት መጠን፦

-የሰበካ ጉባዔዎችን፡ በየገጠሩ ቤተ መቅደሶችና በየከተማው አድባራት ከማቋቋም ጀምሮ፥

-በየዓመቱ፡ ለጥምቀት በዓል አዳር የሚወጡት፡ በመኻል ከተማና በአራቱ ማዕዘናት ያሉት፡ የአዲስ አበባ ታቦታት ኹሉ፡ በጃንሜዳ እንደሚደረገው፡ በየአግጣጫቸውና በየክልላቸው፡ በአንድነት ተሰባስበው የሚያድሩበትን ቦታ እስከመመደብ፥

-ደግሞም፡ በአዲስ አበባ መናገሻ ከተማ፡ የነዋሪው ሕዝብ ብዛት እየጨመረ በመኼዱ፡ በጊዜው የነበረውንና የወደፊቱን ችግር በመመልከት፡ ዛሬ፡ አዳዲሶቹ አብያተ ክርስቲያናት የታነጹበት ቦታ፡ ተቀይሶ እንዲጠበቅ እስከማድረግ ድረስ የተከናወነው ሥራ ኹሉ የተካኼደው፡ በዚሁ መልክ እንደነበረ ማውሳት ይቻላል።

፫ኛ፦ "የመንግሥት ሥራ ትቶ፡ ለፓርላማ መወዳደር" በሚለው ርእስ ሥር፡ በኢትዮጵያዊው ትክክለኛ የአኀዝ አጻጻፍ ሥርዓት፡ ፻፴፮ ተብሎ ሊጻፍ በሚገባው፡ በገጽ 136 ላይ፡ ከራስዎና ከሌሎቹ የምክር ቤት ምርጫ ተወዳዳሪዎች የስም ዝርዝር ውስጥ፡ "እነቄስ ኤርሚያስ ከበደ" ተብሎ የተጻፈውን ስሜን አነበብሁት።

ይህ፡ እንዴት ሊኾን እንደቻለ፡ እጅግ አስደንቆኛል፤ ያስደነቀኝም፡ በስሜ ላይ የተደረገው፡ የሆሄያት ስሕተት፡ በድጋሚ መታየቱ አይደለም፤ ነገር ግን፡ ያልኾነውን ነገር፡ እንዴት "ኾነ!" ብለው ሊጽፉት እንደቻሉ ነው፤ ማለትም፡ በዚያ የምርጫ ውድድር ውስጥ፡ ጨርሶ ተሳታፊ ያልነበርሁትን፡ እኔን፡ ልክ እንደነበርሁ አድርገው፡ መጻፍዎ ነው፤ ይህ ከባድ ስሕተት፡ በመጽሓፍዎ ውስጥ በመገኘቱ፡ እኔን የሚመለከተው ክፍል ብቻ ሳይኾን፡ "ሌላውም ኹሉ፡ እንዲህ የተሳሳተ ሊኾን ይችላል!" ብሎ፡ የአንባቢን ሕሊና፡ ወደጥርጣሬ እንዳይመራ እሠጋለሁ፤ ለዚህም ማረጋገጫ፡ ሌላ ማስረጃ ማቅረብ ሳያስፈልግ፡ እዚሁ ላይ፡ ለምሳሌ፡ ከእኔ የሕዝብ እንደራሴነት ምርጫና አገልግሎት በኋላ፡ ለአራተኛው የምክር ቤት ዘመን ተወዳድረው የተመረጡትን፡ የአቶ ቃኘው ቅጣቸውን ስም፡ አለጊዜውና አለቦታው፡ በስሕተት ማስገባትዎ፡ የጎላው ኾኖ ሊጠቀስ ይቻላል።

ደግሞም፡ ይህ እውነታ የተፈጸመበት ዘመን፡ ይህን ያህል ሩቅ ባይኾንም፡ "ምናልባት፡ ከዕድሜ መግፋት የተነሣ፡ በመዘንጋት ሊኾን ይችላል!" ብዬ እንድገምት እገደድ ይኾናል፤ ዳሩ ግን፡ ይህ ግምቴ፡ ትክክል ኾኖ ከተገኘ፡ በመጽሓፍዎ ውስጥ የሥፈሩትን ነገሮች እውነተኛነት፡ አኹንም፡ ከባሰ ጥርጥር ላይ ስለሚጥለው፡ የድርሰትዎን ዓላማ፡ በበለጠ ሊጎዳብዎት ይችላል። እንግዲያ፡ ይህ ኹሉ ሊኾን ካልቻለ፡ ሌላ ምን ይኾናል? "እኔንና በተለይ፡ ሕይወቴን፡ መሥዋዕት በማድረግ፡ በቃል ኪዳን የቆምሁለትን የአገልግሎት አቋም ለመጉዳት ሲሉ፡ አውቀውና አቅደው አድርገውት ይኾናል!" ብዬ ላስብን? እንዲህ ከኾነ፡ ለኹሉ፡ እንደየሥራው የሚከፍለውን፡ የእውነተኛውን ዳኛ፡ የመጨረሻ ፍርድ እየተጠባበቅሁ፡ በእኔ በኩል፡ እንዲህ እንዳስብ ያደረጉኝን፥ ራስዎ፡ በዚሁ መጽሓፍዎ ውስጥ የጠቀሷቸውን ድርጊቶችዎን፡ ከዚህ በማከታተል እገልጻለሁ።

…፬

እርስዎ፡ በሕዝብ እንደራሴነት ተመርጠው፡ ወደቤተ ሕዝቡ፡ ለመጀመርያ ጊዜ የገቡት፡ በኹለተኛው ብሔራዊ የምክር ቤት የምርጫ ውድድር ዘመን፡ ማለትም፡ በ፲፱፻፺፫ ዓ.ም. ሲኾን፡ በዚያን ጊዜ፡ እኔ፡ አብሬዎ አልተወዳደርሁም፡፡ እኔ፡ አብሬዎ የተወዳደርሁት፡ እርስዎ፡ ለሦስተኛው የምክር ቤት ዘመን፡ እንደገና በተወዳደሩበት፡ በ፲፱፻፺፯ ዓ.ም ነው፡፡ በዚያን የውድድር ጊዜም፡ እኔ ተመርጬ፡ ወደምክር ቤቱ ስገባ፡ እርስዎ፡ እንደመጽሓፍዎ አገላለጽ፡ “በምርጫው ያገኙት ውጤት፡ አነስተኛ ስለነበር”፡ ሳይገቡ ቀርተዋል፡፡ እነዚህን ኹሉ ኹኔታዎች፡ ከማንም የበለጠ፡ በተለይ፡ እርስዎ፡ ደህና አድርገው ያውቁታል፤ ያስታውሱታልም፡፡ “ደህና አድርገው ያውቁታል፤ ያስታውሱታልም!” የሚለውን አንቀጽ በአጽንዖት ላሰምርበት እወድዳለሁ፤ ምክንያቱም፤ “እነቄስ ኤርሚያስ ከበደ” ብለው ስሜን፡ በተወዳዳሪዎቹ ዝርዝር ውስጥ ያስገቡት፡ አውቀው እንጂ፡ ሳያውቁ፡ በስሕተት አለመኾኑን ለማስገንዘብ ስለምፈልግ ነው፡፡

ይህን እውነታ ለማረጋገጥ ደግሞ፡ ብዙም አያደክምም፤ የውድድሩ ዓይነትና ከላይ የተጠቀሰው ራሱ፡ የምርጫው ውጤት ይመሰክራሉ፤ ይኸውም፡ ከመጀመሪያዎቹም ኾነ፡ ከኋለኞቹ ተወዳዳሪዎችዎ ይልቅ፡ የእኔ ተወዳዳሪነት፡ በእርስዎ የሕይወት ዓላማና ተግባር ላይ፡ ምን ያህል የተጽዕኖ ኃይል ኖሮት፡ ያን የመሰለውን ከባድና የጎላ ቀውስ ሊያስከትልብዎ የቻለ በመኾኑ ነው፡፡ በዚያ ውድድር ላይ፡ ብዛት ከነበራቸው ተወዳዳሪዎች መካከል፡ በሕዝብ ፊት ቀርበን፡ እስከመጨረሻው ድረስ፡ እንናገር፥ እንከራከር፥ ለጥያቄዎችም፡ መልስ እንሰጥ የነበርነው፡ እርስዎና እኔ ብቻ እንደነበረ ይታወሳል፡፡ በዚያን የምርጫ ጊዜ፡ በእርስዎና በእኔ መካከል፡ የታየው የውድድር አካኼድ፡ እርስዎ፡ በመጽሓፍዎ ውስጥ ካሞገሱት፡ ከመጀመሪያው ይልቅ፡ የሚበልጥ እንደነበረ ይዘነጉታልን? የሚወደሰው፡ እርስዎ ያሸነፉበት ብቻ ሊኾን ይገባልን? እንደውድድሩ አያያዝማ፡ “ሲኾን ሲኾን፡ ኹለታችንም እንመረጣለን፤ አለዚያም፡ እኔ ቀርቼ፡ እርስዎ፡ በውድድሩ አሸንፈው፡ በሕዝብ እንደራሴነትዎ ይቀጥላሉ!” ብዬ አስብ ነበር እንጂ፡ “እርስዎ ቀርተው፡ እኔ እመረጣለሁ!” ብዬ ጨርሶ አላሰብሁም ነበር፡፡ በዚያን ጊዜ፡ መራጩ ሕዝብ፡ ራሱ፡ በሰጠው ውሳኔ መሠረት፡ እርስዎን ሳይመርጥዎ በመቅረቱ፡ እንደገና ወደቤተ ሕዝቡ ምክር ቤት ሳይገቡ ቀሩ እንጂ፡ እኔ፡ በእርስዎ ላይ፡ ክፉዉን፡ እንኳንስ ማድረጉ፡ ማሰቡም እንደሌለብኝ፡ የሚያውቁ ይመስለኛል፡፡

ታዲያ! በሕይወትዎ ዓላማና የኑሮ ግዳጅዎ ላይ፡ ይህን የመሰለውን ከባድ ውጤት ያስከተለውን፡ የቅርቡን የምርጫ ኹኔታ ረስተው፥ ወይም፡ ዘንግተው፥ ወይም፡ ገለል አድርገው፡ እንዴት፡ የሩቁን አስታውሰው፡ የእኔን ስም፡ እንደዚያ በስሕተት ሊጽፉት ቻሉ? በእርስዎ ቦታ፡ እኔ በመተካቴ፡ እስከዛሬ ድረስ “አዝነውብኛል፤ ቂምም ይዘውብኛል!” ማለት ነውን? ይህን ያደረጉት፡ በግል፡ እኔን ብቻ ሳይኾን፡ በይበልጥ፡ የተወለድሁበትንና የምኖርበትን፥ በእግዚአብሔርም እውነት የምጋደልለትን፡ የኢትዮጵያዊነት ተልእኮዬን ለመንካት፡ ኾን ብለው ያደረጉት መኾኑን፡ ከዚህ የሚቀጥለው ማብራሪያ ያስረዳል፦

በዚያን የመጀመሪያ ምርጫ ውድድርዎ ጊዜ፡ ዋና ተወዳዳሪዎ ኾነው፡ የቀረቡት እጩ፡ በጄኔራል ዊንጌት የግብረ ገብ መምህር የነበሩት፡ መምሬ ዘውዴ የተባሉት መኾናቸውን፡ በመጽሓፍዎ ሓተታ ውስጥ፡ በሰፊው ገልጸውታል፡፡ ነገር ግን፡ በዚያኑ ጊዜ፡ ከእርስዎ ጋር ይወዳደሩ የነበሩትን፡ የሌሎቹን እጩዎች ስም በጻፉበት ዝርዝር ውስጥ፡ የመምሬ ዘውዴ ስም አብሮ ሊገኝ ሲገባ፡ ያ ቀርቶ፡ እንዲገኝ የተደረገው፡ የእኔ ስም ብቻ ነው፤ እርሱም፡ ሌሎቹ እጩዎች ኹሉ፡ ስማቸው፡ በነጠላ እየተጻፈ ሲቀርብ፡ በእኔ ስም ላይ ብቻ፡ “እነ” የሚለው፡ ተውሣከ ታክሎበት፡ “እነቄስ ኤርሚያስ ከበደ” ተብሏል፤ ለምን? በዚያን ውድድር ላይ፥ በዚያን ቀን፥ በዚያን ሰዓትና በዚያ ቦታ፡ ጨርሶ ያልነበርሁትን እኔን፡ ቄስ በመኾኔ ብቻ፡ ከመምሬ ዘውዴ ጋር፡ አንድ አድርገው፡ በአሳብ፥ በቃልና በጽሑፍ ፍላፃ ለመምታት እንዲያመችዎ ያቀነባበሩት ዘዴ መኾኑ ሊታበል አይቻልም፤ ይህ እውነታ፡ ለሌላው የማይከሠትለት መስሎ ቢታይዎ፡ ለእኔ፡ “ይህን ማስተዋል ይሣነዋል!” ብለው እንዴት ገመቱ?

አዎን! በኹለተኛው ውድድርዎ ጊዜ፡ በተለይ እኔ፡ እጩ ኾኜ፡ ባልገባ ኖሮ፡ እርስዎ ይመረጡ ስለነበረ፡ የኹለታችን ውድድር ውጤት፡ ሊያስደስትዎ እንዳልቻለ ይታወቃል፤ ይኹን እንጂ፡ ከአያሌ ዓመታት በኋላ፡ ይህን ያህል፡ የመቈጨትን ስሜት አሳድሮብዎ፡ ያውም፡ ከዚያ የሥልጣን ደረጃ ይልቅ፡ እጅግ ከፍ ባለው፡ በዛሬው ሉዓላዊ ቦታ ላይ ኾነው፡ በእኔ ላይ፡ ይህን የመሰለውን፡ የቆየ ሥውር ደባ መፈጸምዎ “ለምን ይኾን?” ብሎ ለማሰብ፡ በእርግጥ ይከብዳል፡፡ ዳሩ ግን፡ ያተኮሩት፡ ቀደም ብዬ እንደጠቀስሁት፡ በግል በእኔ ላይ ሳይኾን፡ በይበልጥ፡ በተልእኮዬ ላይ ስለኾነ፡ አይገርመኝም፤ ምክንያቱም፡ እኔ፡ መላ ሕይወቴን ተሠማርቼበት የምገኝበት ይህ አገልግሎቴ፡ ምናልባት፡ እንደርስዎና እንደመሰሎችዎ ምኞትና ጥረት ሳይኾን፡ ከመጥፋት ተርፎ፡ እንዲያውም፡ በበለጠ እያየለና እየገነነ በመኼድ፡ ይኸው ዛሬ፡ ለእርስዎ መልስ ለመስጠት እስከመቻል በመድረሱ፡ ወደፊት፡ እንዲህ ከቀጠለ፡ ተመልሶ ይሰፍንና፡ እርስዎ፡ እንደሚመስልዎ፡ አኹን ላሉበት ማዕርግዎ ያበቃዎትን መሠረታዊ እምነትዎን “ይጻረራል!” ብለው አስበው በመሥጋት፡ በሥውር የወረወሩብኝ፡ የጥላቻ ፍላፃ መኾኑን፡ የአኹኑ ድርጊትዎ ስላረጋገጠው ነው፤ እኔም፡ ተከላክለው በሚያድኑኝ፡ በእግዚአብሔር እውነትና ብርሃን ጋሻነት ተማምኜ፡ ለተወረወረብኝ ፍላፃ፡ በተገቢው መልክ፡ የሰጠሁትን ግልጽ ምላሽ፡ እነሆ ልኬልዎታለሁ፡፡

መምሬ ዘውዴ፡ ከእርስዎ ጋር በመፎካከር፡ ለምርጫ፡ በእጩነት፡ ገብተውበት በነበረው ውድድር ላይ፡ እርስዎ የነበረዎት፡ የእምነትና የአስተሳሰብ አቋም፡ ግልጽ ኾኖ፡ ከመጽሓፍዎ ይነበባል፤ ይኸውም፡ “የግብረ ገቡ መምህርና ቄሱ፡ መምሬ ዘውዴ፡ ክፍላቸው በኾነው፡ በዚያው፡ በቤተ ክህነቱ ውስጥ ተወስነው፡ ሃይማኖታዊና መንፈሳዊ ተግባራቸውን ማከናወን እንጂ፡ የእኔ ክፍል በኾነው፡ በሥጋዊው አስተዳደርና አመራር ውስጥ አያገባቸውምና፡ በዚህ ውድድር፡ መምረጥ ያለባችሁ፡ እኔን እንጂ፡ እርሳቸውን አይደለም!” የሚለው ነው፡፡ በእርስዎና በእኔ መካከል በተካኼደው፡ በኹለተኛው ውድድር ጊዜም፡ እኔን በሚመለከት የነበረዎ አቋም፡ ይህ እንደነበረ፡ እነሆ፡ በአኹኑ አድራጎትዎ ከሥተውታል፡፡ በዚያን፡ በመጀመሪያው ውድድርዎ ጊዜ፡ እርሳቸው፡ መምሬ ዘውዴ ቀርተው፡ እርስዎ የተመረጡት፡ ምናልባት፡ እርስዎ እንደመሰለዎት፡ በዚያ አቋምዎ ትክክለኛነት ከኾነ፡ ታዲያ፡ በኹለተኛው ውድድር ጊዜ፡ ለምን እርስዎ፡ ያውም፡ የምክር ቤቱ ተደጋጋሚ ሊቀ መንበር ኾነው፡ በአባሎቹ ተመርጠው ሲሠሩ የቆዩት ቀርተው፡ እኔ፡ ቄሱ፡ አሸንፌ ለመግባት ቻልሁ? እንዲያ፡ በቤተ ሕዝቡ፥ በቤተ ክህነቱና በቤተ ምልክናው ውስጥ እየተዘዋወርሁ ለማገልገል የቻልሁት፡ በዚያን ጊዜ፡ ኢትዮጵያዊው ሥርዓተ መንግሥት ጸንቶ ይሠራ የነበረ በመኾኑ አይደለምን? እዚህም ላይ፡ እኛን ዒላማዎ አድርገው፡ በብዕርዎ ፍላፃ ሊመቱ ያቀዱት፡ በግል ሰውነታችን፡ መምሬ ዘውዴንና እኔን ሳይኾን፡ ባዕዳን ጠላቶቻችን፡ ከቀድሞ ጀምሮ፡ እስከዛሬ ሊያጠፉት የሚታገሉትን፡ ጥንታዊዉንና ዘለዓለማዊዉን የኢትዮጵያ ሥርዓተ መንግሥት መኾኑን፡ እውነተኛ ተመልካች የኾነው፡ የመጽሓፍዎ አንባቢ፡ በቀላሉ ይረዳዋል፡፡

በዚያ ውድድር ላይ ከደረሱት ኹኔታዎች መካከል፡ አንዱን፡ የእኔን ተልእኮ በሚመለከት፡ በመጽሓፍዎ ውስጥ ለተወሳው ርእሰ ነገር፡ አጠር ያለ አስተያየትን ሠንዝሬ እንዳልፍ እገደዳለሁ፡፡ ይኸውም፡ የ“አንበሳ”ን ምሥል፡ የምርጫ ምልክቱ አድርጎ፡ ይወዳደርዎ ከነበረው፡ ከአንዱ እጩ ጋር በተፈጠረው አምባጓሮ መነሻነት፡ በተለይ እርስዎ፡ *“ሞዐ አንበሳ፡ ዘእምነገደ ይሁዳ”* በሚለው፡ የተቀደሰ ብሔራዊ ዓርማችንና ማኅተማችን ውስጥ፡ የሚታየውን የአንበሳ መልክ፡ “ጫካ ከተወለደው፡ ከጠፍራሙ አንበሳ” ጋር በማነጻጸር የሠነዘሩት ትችትዎ፡ ከማናቸውም ዓይነት ሕፀፅ፡ የጠራ ሊኾን ስለሚገባ፡ ለዚሁ አቀራረብዎ፡ ተገቢ ማብራሪያን መስጠት የሚያስፈልግ በመኾኑ ነው፡፡ ይህ አምላካዊው ቃል፡ በራእየ ዮሓንስ፡ ምዕራፍ ፭፥ ቍጥር ፭ ላይ ተጽፎ የሚነበብ ሲኾን፡ *“ከይሁዳ ነገድ የተወለደው አንበሳ፡ ድል አደረገ!”* የተባለው፡ በቀጥታ፡ ኢየሱስ ክርስቶስ መኾኑ፡ እዚያው ምዕራፍ ውስጥ፡ በባለራእዩ ወንጌላዊ ተብራርቷል፡፡ ስለዚሁ አንበሳ አቋም፡ “አንካሴና ባንዲራ ያለበት ዘንግ ይዞ፡” የሚለው አገላለጽዎ፡ “የኢትዮጵያ ሰንደቅ ዓላማ የሚውለበለብበትን ባለመስቀል ዘንግ ይዞ፡” ተብሎ ቢስተካከል፡ የበለጠ ይሠምራል እላለሁ፡፡

የኢትዮጵያዊነት አብነት እንደኾነው፡ እንደቀዳሚ ምሳሌው፡ እንደመልከ ጼዴቅ፡ በቤተ ሕዝብ ወገንነቱ፥ በቤተ ክህነት ሥልጣኑና በቤተ ምልክና ሹመቱ ብቻ ሳይኾን፡ ከኢትዮጵያዊት እናቱ፡ ከቅድስት ድንግል ማርያም፡ በሰውነት በመወለዱ፡ በትውልዱና በመልኩ ጭምር ኢትዮጵያዊ የኾነው ኢየሱስ ክርስቶስ፡ ወደአይሁድ የተላከው፡ ልክ፡ የእስራኤልን ልጆች፡ ከግብፅ የባርነት አገዛዝ፡ ነጻ ያወጣቸው ዘንድ፡ የእርሱ ሌላ አርአያው የኾነውን፡ ሙሴን፡ እግዚአብሔር፡ ወደፈርዖን በላከው ዓይነት መኾኑ ይታወቃል፤ ያን ሙሴ፡ እግዚአብሔር፡ ለዚያ ተልእኮ የመረጠውና የጠራው፡ አስቀድሞ፡ በጣዖት አምልኮ ከኖረበት፡ ከግብፅ፡ ወደኢትዮጵያ አምጥቶ፡ ስለአምልኮተ እግዚአብሔርና ስለኢትዮጵያዊነት፡ ከኢትዮጵያዊው ካህን፡ ከዮቶር፡ የተሟላ እውቀትን እንዲያገኝና እነዚህን ምስጢራት፡ በሃይማኖት እንዲቀበል ካደረገ፥ ኢትዮጵያዊቷን፡ የዮቶርን ልጅ፡ ሲጳራን አግብቶ፡ ልጆችን ከወለደም በኋላ መኾኑ አይዘነጋም፤ ስለዚህ፡ *"ሞዐ አንበሳ"*፥ ወይም፡ *"ድል አድራጊው አንበሳ"* የተባለው ኢየሱስ ክርስቶስ፡ ኢትዮጵያዊ በመኾኑ፡ አንበሳው፡ የእኛ የኢትዮጵያውያን፡ የብቻችን ብሔራዊ፥ ሕዝባዊና መንግሥታዊ ምልክታችን ኾኖ መኖሩ፥ እውነተኞቹ እስራኤልም፡ እኛ ኢትዮጵያውያን መኾናችን፡ አያስደንቅም።

*"ሞዐ አንበሳ"* ከሚለው ቃል ጋር፡ *"ዘእምነገደ ይሁዳ"* የሚለው ሐረግ፡ ተያይዞ የሚነበብበት ምክንያት ደግሞ፡ ኹለት መሠረታውያን መነሻዎች አሉት፤ ከእነዚህም መካከል፡ ፩ኛው፡ ኢየሱስ ክርስቶስ፡ በኢትዮጵያዊነቱ፡ የኖኅ ልጆች ከኾኑት፡ ከካምና ከያፌት ብቻ ሳይኾን፡ የሴም ነገድ ከኾነውና "እስራኤል" ከተባለው፡ ከያዕቆብ፡ ልጅ፥ እርሱም፡ *"ሥርዉ ለዳዊት"፥ ወይም፡ "የዳዊት ሥር"* ከተባለው፡ ከይሁዳ ዘር፡ *ከዳዊትም* የተወለደ መኾኑን ለማመልከት ነው፤ ፪ኛውም መነሻ፡ የሚከተለውን ጥቅስ መሠረት ያደርጋል፤ ይኸውም፡ *"ይሁዳ፡ የአንበሳ ደቦል ነው! ...ገዢ የኾነው እስኪመጣ ድረስ፡ በትረ መንግሥት፡ ከይሁዳ አይጠፋም!"* ሲል፡ እግዚአብሔር፡ ከ፲፪ቱ የያዕቆብ ልጆች መካከል ፩ዱ ለኾነው፡ ለይሁዳ፡ በአባቱ አንደበት፡ የሰጠው የተስፋ ቃል ነው።

ይኹን እንጂ፡ "አይሁድ" የተባሉት የእስራኤል ሕዝብ፡ ቀድሞ፡ በሙሴ ላይ፥ ኋላም፡ በኢየሱስ ክርስቶስ ላይ በፈጸሙት ክህደት፥ ዓመፅና አመንዝራነት ምክንያት፡ ለዚህ የተስፋ ቃል፡ ሊበቁ ስላልቻሉ፡ በሙሴ አማካይነት፡ ለእስራኤል ተሰጥታ የነበረችው፡ የድንግል ማርያም አርአያ የኾነችው፡ ታቦተ ጽዮንና የኢየሱስ ክርስቶስ መታወቂያ የኾነው፡ *"ሞዐ አንበሳ ዘእምነገደ ይሁዳ!"* የሚለው መለኮታዊ ቃል፡ ኹለቱም፡ ከቃል ኪዳን ባለቤቶቻቸውና በረከቶቻቸው ጋር፡ የኢትዮጵያውያን ሀብታት ኾኑ! ለእግዚአብሔር ምስጋና፥ ለወላጆቻችንም፡ ባለውለተኛነታችን ይድረሳቸውና! በዚህም፡ *"'የእስራኤል ልጆች ሆይ! እናንተ፡ ለእኔ፡ እንደኢትዮጵያ ልጆች አይደላችሁምን?' ይላል እግዚአብሔር፤"* የሚለው አምላካዊ ማረጋገጫ እውን ኾኖ ተፈጽሟል።

፬ኛ:- ኢትዮጵያዊ ስለኾነውና እግዚአብሔር ስለሠራው፥ ኢትዮጵያውያንም ጠብቀውት ስላኖሩት፡ የኢትዮጵያ ሥርዓተ መንግሥት፡ በተከታታይ ታትመው በተሠራጩት፥ ምናልባትም፡ በእጅዎ በሚገኙትና አንብበዋቸው ሊኾኑ በሚችሉት፡ "ኢትዮጵያዊው፡ በማንነቱ ፍለጋ!"፥ "Ethiopia: The Classic Case" እና "ኢትዮጵያ፡ የዓለሙ መፋረጃ!"፥ እንዲሁም፡ "ኢትዮጵያና ኢትዮጵያዊነት" በተባሉት መጻሕፍቴ ውስጥ፡ የሚበቃ ሓተታ የሰጠሁበት ስለኾነ፡ እዚህ ላይ፡ አግባብነት ያላቸውን፡ አንዳንድ ቊም ነገሮች ከማመልከት በቀር፡ ብዙም የምጨምረው ነገር አይኖረኝም።

ኢትዮጵያዊው ሥርዓተ መንግሥት፡ የእግዚአብሔር፥ ከእግዚአብሔርና በእግዚአብሔር ስለኾነ፡ ፍጹም ነው፤ እንከን የለበትም። ከዚህ የተነሣ፡ ኢትዮጵያና ኢትዮጵያውያን፡ በምድር ላይ ተሠራጭቶ ያለውን የሰውን ዘር ኹሉ፡ ማለትም፡ የኖኅ ልጆች የተባሉትን፡ የሴምን፥ የካምንና የያፌትን ነገዶች፥ በሃይማኖትም በኩል፡ በዓለም ላይ የሰፈኑትን፡ የኪዳነ ልቦናን፥ የኪዳነ ኦሪትንና የኪዳነ ክርስትናን፥ እንዲሁም፡ የእስልምናን፥ ሌሎቹን፡ የአሕዛብንና የአረማውያንን እምነቶች ሳይቀር፡ እየተቀበሉ፥ ለእንግዶቹ፡ የመኖርና የመሥራት ፈቃድን፥ የማምለክ ነጻነትንም እየሰጡ፡ በመልካም ሲያስተናግዱ ኖረዋል፤ ይኖራሉም።

ይልቁንም፡ የታላላቆቹ የዓለም ሃይማኖቶች መሥራቾችና ቀንደኞች ተከታዮች፡ በየአገራቸው፡ የሃይማኖት መከራ በጸናባቸውና ለስደት በተዳረጉ ጊዜ፡ ደገኛውን የታመነ መጠጊያ አግኝተው፡ ከመደምሰስ የተረፉት፥ በዓለምም ላይ፡ ዛሬ ከሚገኙበት አቋም ደርሰው፡ እንዲህ ሊደረጁ የቻሉት፡ ይህ፡ የእግዚአብሔር ሥርዓተ መንግሥት ወደሠለጠነባት፡ ወደኢትዮጵያ መጥተው፡ በኢትዮጵያውያን ዘንድ በመጠለላቸው መኾኑ፡ በዓለም ዐቀፍ ደረጃ የታወቀ እውነታ ነው፡፡ በዚህ መልክ፡ በጥገኝነት፡ ወደኢትዮጵያ መጥተው፡ ለመስተናገዳቸው፡ ቋሚ ማስረጃዎች ኾነው የሚጠቀሱ ዜና ድርጊቶች አሉ፤ እነዚህም፡-

-በጥንቱ የኪዳነ ልቦና ዘመን፡ "ኢትዮጲስ" የተባለው፡ የኢትዮጵያውያን አባትና የኢየሩሳሌሙ ካህን ንጉሥ፡ የመልከ ጼዴቅ ልጆች፡ ካህኑ ዮቶርን በመሰሉት ተጠሪዎቻቸው አማካይነት፡ ወደኢትዮጵያ ተመልሰው መግባታቸው፥

-በመካከለኛው የኦሪት ዘመን፡ የእስራኤል ሕዝብ መሪ የኾነው፡ ሙሴ፡ ቀደም ብሎ፡ ብቻውን ተሰድዶ፡ ወደኢትዮጵያ መምጣቱ፥ ኋላም፡ በኢትዮጵያዊቷ ንግሥት ማክዳ የኢየሩሳሌም ጉዞ ምክንያት፡ እውነተኞቹ እስራኤላውያን፡ ከታቦተ ጽዮን ጋር፡ ተሰድደው፡ ወደኢትዮጵያ መፍለሳቸው፥

-በመጨረሻውም፡ የክርስትና ዘመን፡ "ተስዓቱ ቅዱሳን"ን የመሰሉ የተዋሕዶ ሃይማኖት ተጋዳዮች የኾኑ መንፈሳውያን አርበኞች፡ ወደኢትዮጵያ መሰደዳቸው ናቸው፡፡

ከዚህ በኋላ፡ የእስልምና ሃይማኖት መሥራች፡ መሓመድ፡ ተከታዮቹን ቤተሰቦች፡ በዚሁ የስደት ኹኔታ፡ ወደ ኢትዮጵያ ልኮ፥ እነርሱም፡ በመልካም ይዞታ ተስተናግደው፡ ወደአገራቸው መመለሳቸው፡ ሌላው ማስረጃ ኾኖ ይጠቀሳል፤ ይህም፡ በይበልጥ፡ በሃይማኖቱ ተከታዮች ዘንድ፡ ታምኖበት፡ እነሆ፡ ሲነገር ይኖራል፡፡

እነዚህ ኹሉ ሕያዋን ምስክሮች፡ የኢትዮጵያዊዉን ሥርዓተ መንግሥት መለኮታዊነትና ፍጹምነት ያረጋግጣሉ፡፡ ይህ፡ የኢትዮጵያ ሥርዓተ መንግሥት፡ እንዲህ እንከን የሌለበት፡ ፍጹም ሲኾን፡ በእኛ በተቀባዮቹ ኢትዮጵያውያን ዘንድ እንዳይሠራና ፍሬያማ እንዳይኾን፥ እንዲያውም፡ ለነቀፌታ እንዲጋለጥ ያደረጉትና እያደረጉ ያሉት፡ ከራሳችን መካከል የወጡት፡ የሓሰትና የክፋት ሰዎች ናቸው፡፡ ሥርዓቱን፡ ከእኛ ወርሰው እየተጠቀሙበት ባሉት፡ እንግሊዝን በመሰሉት አገሮች ዘንድማ፡ ይኸው፡ በገሃድ ሥራ ላይ ውሎ፡ ሲጠቅምና መልካም ፍሬን ሲያበረክት፥ ሲወደስም የሚታይ አይደለምን?

ይኸው ሥርዓተ መንግሥት፡ ዛሬ፡ በኢትዮጵያ፡ እንዲህ፡ በሰዎች ስሕተትና ጥፋት ምክንያት፡ አኹን ወድቆ ከሚገኝበት ጉሥቁልና ላይ ደርሶ ቢታይም፡ የዚሁ ሥርዓተ መንግሥት፡ የሚያስፈራውና የማይበገረው ኃይሉ፡ በሓሰትና በክፉ መንገድ ሊጠቀሙበት የሞከሩትን ግለሰቦችና ወገኖች ኹሉ፡ በየራሳቸው የተንኰል ሥራ ጠፍተው እንዲቀሩ የማድረግ ችሎታው ነው፤ እነርሱ፡ ጠፍተው ሲቀሩ፡ እርሱ ግን፡ ሕያው ኾኖ፡ በህልውናው የመቀጠሉ፥ እንዲህ እያለም፡ ለዘለዓለም የመኖሩ እውነታ፡ በኢትዮጵያ መሪዎችና ሕዝብ ላይ፡ እስከዛሬ ድረስ፡ በገሃድ እየተፈጸመ ለመታየቱ፡ እርስዎና እኔ፥ የአኹኑም የኢትዮጵያ ትውልድ፡ በቂ ምስክሮች ነን፡፡

እኛ፡ ኢትዮጵያውያን፡ ይህን ሥርዓተ መንግሥት፡ "በእውነትና በትክክል፡ ሥራ ላይ እናውለው!" ባልንበትና ወይም፡ በምንልበት ጊዜያት ኹሉ፡ ጥቅሙ፡ ለእኛው፡ ለራሳችን ብቻ ሳይኾን፡ በይበልጥ፡ በኢትዮጵያ ውስጥና ከኢትዮጵያ ውጪ፥ በመላውም ዓለም ለሚኖሩ፡ "የተለያየ ዘር፥ ቀለምና ሃይማኖት አለን!" ለሚሉት፡ ለአይሁድና ለክርስቲያኖች፥ ለእስላሞችና ለአረማውያንም ጭምር ኾኖ ይገኛል፤ ምክንያቱም፡ ከላይ እንደተዘረዘረው፡ እያንዳንዳቸው ወገኖች፡ በየመኖርያቸውና በየዘመናቱ፡ መከራና ስደት በደረሰባቸው ጊዜ፡ ኢትዮጵያ፡ መሸሻና መጠጊያ ኾና፡ ሊያስጥማቸው ከተቃረበው የጥፋት ማዕበል ልታተርፋቸው የቻለች በመኾኗ ነው፤ አኹንና ወደፊትም፡ ሊደርስባቸው ከሚችል፡ ከማናቸውም ሰው-ሠራሽ፥ ወይም፡ ተፈጥሮኣዊ መቅሠፍት፡ ጥላ ከለላ ኾና ልታድናቸው የምትበቃበት ምስጢራዊው ኃይል ስላላትም ነው፡፡

ይህ ምስጢራዊ ኃይል፡ ከዚህ ሥርዓተ መንግሥት መለኮታዊነት የተነሣ፡ ራሷና እርሷን ጥላ ከለላ ያደረጉ ኹሉ፡ እንደማይጠፉ በሚያስተማምነው አምላካዊው የጥበቃና የምሕረት ቃል ኪዳን፡ እውን ኾኖ መሥራቱ ተረጋግጧል።

በቀደመው ዘመን፡ "እባብ"፥ በመጨረሻውም ዘመን፡ "ዘንዶ" ተብሎ፡ በእነዚህ አውሬዎች የተመሰለው ዲያብሎስ፥ የእርሱ ጭፍሮች የኾኑት ያገር ተወላጆችና ባዕዳንም፡ ኢትዮጵያንና ኢትዮጵያውያንን፡ ደብዛቸውን ሳይቀር ለማጥፋት፥ ይህም ካልተሳካላቸው፡ በእነርሱ የበላይነት ሥር፡ እኒህኑ ኢትዮጵያንና ኢትዮጵያውያንን፡ ተገዢዎቻቸውና ተመጽዋቾቻቸው አድርገው ለማኖር፡ እንዳለፉት ዘመናት ኹሉ፡ ዛሬም እንዲህ፡ እየተረባረቡባቸው ያሉት፡ ያለምክንያት አይደለም፤ ምክንያቱ፡ ዛሬ፡ "በህብቱም፥ በጥበቡም፥ በኃይሉም፡ ከእኛ የሚበልጥና የሚቀድም፡ ማንም የለም!" ብለው፡ በዕብሪትና በትምክህት ከተወጠሩት አገሮች፥ ከቀሩትም የዓለም ሕዝቦች ኹሉ ይልቅ፡ ኢትዮጵያንና ኢትዮጵያውያንን፡ የሚያስቀድመው፥ የሚያስበልጠውም፡ ይኸው ሥርዓተ መንግሥታችን፡ እንደማሰናከያ ድንጋይ፡ ከፊታቸው ቆሞ ስለሚመሰክርባቸው መኾኑን፡ እርስዎም፥ ሌላውም፥ ኹሉም፡ በየልቦናችሁ ታውቁታላችሁ።

አዎን! እኛ ኢትዮጵያውያን፡ ከቃል ኪዳን አምላካችን ጋር፥ እርስ በርሳችንና በመካከላችንም፡ ፍቅርና ሰላም በማጣታችን፡ አያያዙንና አጠባበቁን ስላላወቅንበት፥ ስላበላሸነውም ነው እንጂ፡ ከዚሁ ሥርዓተ መንግሥታችን የተነሣ የታደልናቸው፥ በተፈጥሮ ጸጋዎቿ ወደር የሌላት፥ የአዳምና ሔዋን ምድረ ገነት የኾነችው አገራችን ኢትዮጵያና ለብልህነቱ፡ ከሌላው ሰብአዊ ፍጡር ቢበልጥ፥ ወይም፡ ቢስተካከል እንጂ፡ በምንም መመዘኛው፡ የማያንሰው፡ ኢትዮጵያዊው አንጎል፡ በባዕዳን ወደረኞቻችን ዘንድ፡ ጥላቻን ፈጥሮ ጥርሳቸው ውስጥ ያስገባን መኾኑ ግልጽ ነው።

እኔ፡ ቀድሞም ኾነ ዛሬ፥ ወደፊትም፡ በሕይወተ ሥጋ እስካለሁ ድረስ፡ በኢትዮጵያዊነቴ፡ የማበረክተው አገልግሎቴ፡ በዚሁ ሥርዓተ መንግሥታችን መሠረት መኾኑን፡ ይኸው ይመለከቱታል፤ እንዲያ ካልኾነማ፡ በቀደመው ጊዜ፡ እንዴት፡ እኔ ቄሱ፡ በቤተ ሕዝቡ፥ በቤተ ክህነቱና በቤተ ምልክናው ውስጥ፡ የሕዝብ እንደራሴ፥ ካህንና ሠራተኛ ኾኜ፡ በሥልጣን ጭምር፡ የኢትዮጵያን ሕዝብና መንግሥት ለማገልገል እችል ነበር? እንደዚያ ለማገልገል የቻልሁት፡ ከዚሁ፡ ከጥንታዊው ሥርዓታችን የተነሣ አይደለምን? ይህም መብት፡ ለእያንዳንዱ ኢትዮጵያዊ፡ ለወንዱም፥ ለሴቱም፡ በቀጥታ፡ ከእግዚአብሔር የተሰጠ ጸጋ ነው፤ እርስዎም፡ በኢትዮጵያዊነትዎ፡ በእርግጥ የሚያምኑ ከኾነ፡ ይኸው ጸጋ፡ ለእርስዎም የተሰጠ መኾኑን ሳበሥርልዎ፡ ደስ ይለኛል።

ለዚህ ነበር እኮ፡ እርስዎና እኔ፡ በንግድ፥ በተግባረ-ምርትና ዕቅድ ምልክና (Ministry of Commerce, Industry and Planning)፥ በአዲስ አበባ ከተማና በብሔራዊው የሕግ መምሪያ ምክር ቤቶች፥ እንዲሁም፡ የአዲስ አበባ ደብረ ብሥራት ቅዱስ ገብርኤል ቤተ ክርስቲያን ሰበካ ጉባዔን ባቋቋምን ጊዜ፡ በእነዚህ ኹሉ፡ የቤተ ሕዝቡ፥ የቤተ ምልክናውና የቤተ ክህነቱ ዘርፎች ውስጥ፡ ኹለታችንም፡ በየግላችን ኾነ፡ አብረን ስንሠራ የነበርነው! ይህን እውነታ አያውቁትም ኖርዋልን? ወይስ፡ አልተቀበሉትም ኖርዋል? ወይስ፡ አያምኑበትም ኖርዋል?

የአጼ ኃይለ ሥላሴ ትውልድ፡ በዚህ ሥርዓተ መንግሥት ላይ በፈጸመው ክህደትና ዓመፅ፥ ምንዝርናም ጠንቅ የተነሣ፡ ከራሳቸው ጀምሮ፡ የቤተ ሕዝቡ፥ የቤተ ክህነቱና የቤተ ምልክናው ተጠሪዎች፡ ከነባልደረቦቻቸውና ጭፍሮቻቸው፥ የትውልዱ አባላት የኾኑት ተራዎቹ አዛውንትና ወጣቱ፥ ወንዱና ሴቱ፥ ኹሉም፥ ኹላችንም፡ የከፈልነውንና እየከፈልን ያለነውን ዋጋ ይኸው፡ እርስዎም፥ እኔም፥ ሌላውም፡ እያየነው አይደለምን? የተከፈለውና እየተከፈለ ያለው ዋጋ፡ እንደክረምት ማዕበል በፈሰሰውና እየፈሰሰ ባለው፡ ኢትዮጵያዊ ደም ብቻ የተወሰነ ሳይኾን፡ ይኸው፡ እየቀጠለ በኼደው፡ በድርቁና በረሃቡ፥ በደዌውና በቸነፈሩ፥ በእርስ በርሱ ጦርነትና በስደቱ፥ እንዲሁም፡ እነዚህ መቅሠፍቶች ባስከተሉት መከራና ሥቃይ ጭምር አይደለምን?

ከአጼ ኃይለ ሥላሴ ዘመን አንሥቶ፡ እነዚህ ኹሉ አሠቃቂ ኹኔታዎች እየተፈጸሙና እየደረሱ ባለፉባቸው፡ እስከዛሬ ድረስ ባሉት አገዛዞች ውስጥ፡ እርስዎ፡ እየተሾሙና እየተሸለሙ፥ እየተሞገሱም ከማደግ በቀር፡ በእነዚህ፡ የኢትዮጵያ ሕዝብና የመሪዎቹ ጽዋ በኾኑት መከራዎችና ሥቃዮች ውስጥ፡ ምንም ዓይነት ክፉ እጣ፡ በአንዳቸውም በኩል ያልደረሰብዎ መኾኑን፡ ራስዎም፡ በመጽሓፍዎ ውስጥ፡ በሥዕሎች እያስደገፉ ባሠፈሩት የሕይወት ታሪክዎ አረጋግጠውታል። ይህን ታሪክዎን ያነበበ ማናቸውም አስተዋይ ተመልካች፡ "ይህ እንዴት ሊኾን ቻለ?" የሚል መክፈቻ ጥያቄ፡ በሕሊናው ውስጥ ተኰስትሮ፡ ማሰላሰል መጀመሩ አይቀርም።

አዎን! መቼም፡ ለዚህ አካኼድ፡ አንድ መነሻ ምክንያት መኖር አለበት። እነዚያ አገዛዞች፡ የዛሬው ጭምር፡ የየራሳቸው፡ የተለያየ የእምነት አቋም ስላላቸው፡ አንድ ዜጋ፡ በእያንዳንዳቸው ውስጥ ለማገልገል፥ ከዚያም በላይ፡ የሥልጣን ሹመትን ለመቀበል፡ በግድ፡ የእምነታቸው ተከታይ መኾን ይኖርበታል፤ ያ ዜጋ ደግሞ፡ ራሱ፡ ቀድሞውኑ፡ እምነት የሌለው፥ ወይም፡ የሃይማኖት አመንዛሪ፡ ማለትም፡ እምነቱን የሚቀያይር ካልኾነ በቀር፥ በተለይ፡ በአንዱ፡ የቅዱሱ ኪዳን ኢትዮጵያዊነት ሃይማኖቱ ጸንቶ ሊገኝ የሚገባው ኢትዮጵያዊ፡ ይህን ሊያደርግ አይቻለውም፤ ታዲያ፡ አንዱ በሌላው ላይ፡ በዓመፅና በኃይል ተነሥቶ እየገለበጠው በተተካው ተከታታይ አገዛዝ ውስጥ፡ እርስዎ፡ እንዴት፡ ለተራ ሹመት ብቻ ሳይኾን፡ ዛሬ ለደረሱበት፡ ለዚህ ርእሰ ብሔርነት ሊበቁ ቻሉ? የአምላክን መኖር የሚጠይቀውን ሃይማኖት ቀርቶ፡ እርስዎ ያገለገሏቸውንና የሚያገለግሏቸውን፡ የእነዚያንና የእነዚህን፡ ሃይማኖት አልባ አገዛዞች እምነተ-ቢስነት ተቀብለዋል ማለት ነውን? አለዚያ፡ የፊተኞቹ ቀርተው፡ የኋለኞቹና የዛሬዎቹ፡ የአገዛዝ መሪዎች፡ እንዴት አምነው ተቀበሉዎ? ወይስ፡ አንዱን አገዛዝ ለመጣል፡ ከመጪው ጋር ቀድመው ያካኼዱት የነበረ ምሥጢራዊ ግብር ኖሮ፡ በተተኪው አገዛዝ ዘንድ፡ ለከፍተኛ ሹመት የሚያሳጭዎ ኾነ? ወይስ፡ ከራስዎ የእምነት ዓላማ ለመድረስ፡ የቀደመውን አገዛዝ፡ መሣሪያ በማድረግ፡ በብልህነቱ፥ ወይም፡ በብልጠቱ፡ ከዚያ አገዛዝ ልቀው ተገኙ ማለት ነውን? ላዩ፡ "እምነት"፥ ወይም፡ "መተማመን" የሚባለው ፍሬ ሓሳብ፥ ዘይቤው ሳይቀር፡ ሃይማኖት በሌላቸው ሰዎች ዘንድ፡ እንዴት ሊኖር ይችላል? አይችልም።

የእርስዎ የእምነት ዓላማ፡ ከቀድሞ ጀምሮ እስካኹን፥ አኹንም፡ ባሉበት ሉዓላዊ ቦታ ኾነው፡ እያደረጉት ያለው ጥረት፡ ዝንተ ዓለም ጸንቶ የኖረውን፡ የኢትዮጵያን ሥርዓተ መንግሥት፡ ጨርሰው ለመደምሰስ መኾኑ፡ ከመጽሓፍዎ፡ በቀላሉ ለመረዳት ይቻላል። ይህ ባይኾን ኖሮ፥ ማለትም፡ በኢትዮጵያዊነትዎ የሚያምኑ ቢኾን ኖሮ፡ ዛሬ በያዙት ማዕርግዎ፡ ኹሉንም የኢትዮጵያ ዜጋ፡ በኅሣም፥ በሃይማኖትም፡ በአንድ ዓይን የሚያዩ መኾንዎን ለማሳመን እንኳ ሲሉ፡ በቅርቡ፡ የትግራይን ምድር በጎበኙበት ጊዜ፡ ሲኾን የአኵስም ጽዮንን፥ አለዚያ፡ ከሌሎቹ ታላላቅ አድባራት፥ ወይም፡ ገዳማት መካከል፡ ወደአንዳቸው እንኳ ሳይኼዱ፡ እንዴት ይቀሩ ነበር? ከእነዚህ ይልቅ፡ "ነጃሺ" የተባለውን የእስላሞችን መስጊድ ብቻ ጎብኝተው የተመለሱ አይደለምን? ይህም፡ በኢትዮጵያዊው ሥርዓተ መንግሥት ላይ ያለዎትን ግልጽ ንቀት፥ ጥላቻና ተቃውሞ፡ ለደጋፊዎችዎና ለተባባሪዎችዎ ለማረጋገጥ፥ ለሌላውም፡ በይፋ ለማሳወቅ መኾኑ፡ ሌላ አስረጅ፡ ከቶ አያስፈልገውም። በተለይም፡ "ታሪካዊ ሀብታችንን መጠበቅና መንከባከብ መቻል፡ የድሮውን፥ የአሁኑንና የነገውን ትውልድ ማስተሳሰር ነው።" በማለት፡ የመስጊዱ ጉብኝትዎን ያከበሩበትን ዝግጅት፡ በተጨማሪ አጕልተው ለማሳየት ሲሉ፡ ላወጡት ሥዕል፡ ማብራሪያ እንዲኾን፡ በግርጌው ያሠፈሩት መግለጫ፡ በዚህ ረገድ ያለዎትንና ከላይ የተጠቀሰውን የእምነት አቋምዎን ያጸናዋል።

ይህን የመሰለው ግብር ደግሞ፡ ከኢትዮጵያዊ ፈጽሞ አይጠበቅም፤ ምክንያቱም፡ ኢትዮጵያዊ፡ ከፈጣሪው፡ ከእግዚአብሔር ጋር፡ በቃል ኪዳን የተሣሠረ፥ የማይናወጽና የማይለዋወጥ ሃይማኖት ያለው ስለኾነ ነው፤ እኔ፡ "ኢትዮጵያዊ" ስል፡ በዛሬው ትውልድ ዘንድ፡ በአንደበቱ፡ "ነኝ!"፥ በተግባሩ ግን፡ "አይደለሁም!" የሚለውን ማለቴ ሳይኾን፡ የቃል ኪዳን ሃይማኖቱን ከመጠበቁ የተነሣ፡ እየወረደበት ያለውን የተግሣፅና የቅጣት መስቀል፡ እነሆ፡ በትዕግሥት ተሸክሞ፡ ይኸው፡ ለዚህን ያህል የዓመታት ዕድሜ፡ መከራውንና ሥቃዩን ሲገፋ የሚታየውን ማለቴ መኾኑን እንዲያውቁልኝ እፈልጋለሁ።

፳ኛ፡- በእርስዎ በኩል፡ በመሠረቱ፡ ስለኢትዮጵያና ስለኢትዮጵያዊነት ህልውና፡ እምነቱ ቢኖርዎትም፥ ባይኖርዎትም፡ "ኢትዮጵያዊ"፡ ማነው? "ኢትዮጵያዊነት"ስ ምንድር ነው? ለሚሉት ጥያቄዎች፡ ትክክለኛውን መልስ ለማግኘት፡ በመጽሓፍዎ ውስጥ፡ ስማቸውን ካነሡዋቸው፡ ከአባትዎ፡ ከግራዝማች ወልደ ጊዮርጊስ ሉጫና የእርሳቸው ባለአደራ አባት ከነበሩት፡ ከፊታውራሪ ህብተ ጊዮርጊስ ዲነግዴ የተሻለና የበለጠ፡ ሌላ ማስረጃ መጥቀስም፥ ማቅረብም አይቻለኝም፤ ስለኹለቱም ማንነትና ምግባር፡ ከእኔ የተሻለና የበለጠ፡ እርስዎ ያውቃሉ፤ ይመሰክራሉም። ለእርስዎም ኾነ፡ ለእኔ፥ ለሌላውም፡ "ኢትዮጵያዊ ነኝ!" ለሚል፡ የዘመኑ ትውልድ አባል ኹሉ፡ ስለኢትዮጵያዊነት፡ ፍጹም አርአያዎቻችንና አብነቶቻችን ናቸው። እውነተኞች ኢትዮጵያውያን ኾነው፥ ኖረው፥ ሠርተውና አገልግለው፡ ለእርስዎና ለእኔ፥ ኢትዮጵያንና ኢትዮጵያዊነትን፡ ለልጆቻችን፡ እናስተላልፍላቸው ዘንድ፡ በፍጹም መልኩ፡ አስረክበውን አልፈዋል።

እነርሱ፥ እኛና ልጆቻችን፡ በአንድ፡ ታላቅ የፍሬ ዛፍ ልንመሰል ይቻላል፤ ከግንዱ ከበቀለው፡ ከእነርሱ ቅርንጫፍነት፡ እኛ አቈጥቍጠን፡ ልጆችን አፍርተናል፤ ያው፡ የአንዱ ዛፍ አካል ነን እንጂ፡ ሌላ ዛፍ፥ ሌላ ግንድ፥ ሌላ ቅርንጫፍ፥ ሌላ ፍሬ መኾን አይቻለንም። እየራሳችንን፡ ከግንዱ ገንጥለን፡ ሌላ ዛፍ ለመኾን ከሞከርን ግን፡ የዚያ ዛፍ አካል መኾናችን ቀርቶ፡ ሌላ ዛፍ ኾነን ለመብቀል፡ እንደገና፡ እንደችግኝ መተከል ይኖርብን ይኾናል፤ ለዚያውም፡ ደርቀን፥ ወይም፡ ተረግጠን፥ ወይም፡ በስብሰን፡ በማገዶነት ወደእሳት ከመማገድ፡ ምናልባት ተርፈን ለመገኘት ከቻልን ማለት ነው።

ኢትዮጵያዊነት፡ ከዛሬው ትውልድ ድክመትና ስንፈት የተነሣ፡ እነሆ፡ ደርሶበት እንደሚታየው፡ እያንዳንዱ ግለሰብ፡ ራሱ ካላበላሸውና ካላረከሰው በቀር፡ በምድር ላይ የሚንቀሳቀሰውን ማናቸውንም ሰብአዊ ፍጡር፡ ከመጨረሻው የሕይወት ልዕልና ያደርሰው ዘንድ፡ እግዚአብሔር፡ በፍጹም ለጋሥነቱ፡ ለሰው ልጆች ኹሉ የሰጠው ጸጋ በመኾኑ፡ ስማቸው ከላይ የተጠቀሰው፡ ወላጆችዎ፡ መርጠው ተቀብለውት፥ እየራሳቸውም፡ በነፍስና በሥጋ፡ ተጠቅመውበት፥ ሌላውንም ወገናቸውን ጠቅመውበት አልፈዋል፤ ከተጠቃሚዎቹም መካከል፡ ልጃቸው፡ እርስዎና እኔ እንገኛለን።

የዲነግዴ ልጅ፡ አባ መላና የሉጫ ልጅ አባትዎ፡ በዓለማዊው የመከራ ኑሮ ተሠቃይቶ፡ በሥጋ ሞት የሚያበቃውን የሰውነት ልጅነታቸውን፡ ለምድራዊው የነጻነት ህልውናና ለሰማያዊው የዘለዓለም ሕይወት ወደሚያበቃው፡ ወደእግዚአብሔር ልጅነታቸው ከፍ አድርገውታል፤ "ዲነግዴ" እና "ዳዊ" የሚለውን፡ ሥጋዊና ምድራዊ፥ ሰብአዊና ዓለማዊ ስማቸውን፡ የእግዚአብሔር ልጅነታቸው መለያና መታወቂያ በኾነው፡ "ህብተ ጊዮርጊስ" እና "ወልደ ጊዮርጊስ" በሚለው፡ ሰማያዊና መንፈሳዊ፥ መልአካዊና ዘለዓለማዊ ስማቸው አልቀውትና ሸልመውት፡ እየራሳቸውን፡ "ኢትዮጵያዊ" ላሰኛቸው፡ ለመጨረሻው የህልውና ልዕልና፡ ማለትም፡ ለ"ኢትዮጵያዊነት" ማዕርግና ስያሜ አብቅተውታል። ይህን የመሰለውን ብቅዓት ያገኙት፡ በክርስትና ሥርዓተ ጥምቀት መኾኑ ይታወሳል፤ በዚያን ጊዜ፡ "ዐም ሓራ ኾኑ!"፡ ማለትም፡ "የነጻ ሕዝብ ወገን ኾኑ!" ተባለ። አዎን! አንድ ሰው፡ ከክርስትና ጥምቀቱ በኋላ፡ "ክርስቲያን ኾነ!" ወይም፡ "ኢትዮጵያዊ ኾነ!" ለማለት፡ "ዐማራ ኾነ!" የሚባለው፡ በዚህ ምክንያት መኾኑ ሊታወቅ ይገባል። ሊሸሽግና ሊለወጥ፥ ሊሻሻልና ሊሻር የማይቻለው፡ ግልጹ እውነታ ይህ ነው።

ፊታውራሪ ሀብተ-ጊዮርጊስና አባትዎ፡ ግራዝማች ወልደ-ጊዮርጊስ፡ ከፈጣሪያቸው፡ ከእግዚአብሔር ባገኙት፡ በዚህ የልጅነት ጸጋ፡ "ከሥጋ፡ የኃጢኣት ቀንበር፥ ከሰይጣን፡ የክፋት አገዛዝና ከሰውነት፡ የሞት ፍዳ ነጻ ኾኑ!" ማለት ነው፡፡ ከዚያች ዳግም ልደታቸው በኋላ፡ ኹለቱም፡ በተፈጥሮም ኾነ፡ በሰው ሥራ፥ በእምነትም ኾነ፡ በምግባር፡ ከሥጋ ቍራኝነትና ከዲያብሎስ አምልኮ፥ ከሰዎች አገዛዝና ጠባብ አስተሳሰብ፡ ነጻ ዜጋ ኾነው፡ በእግዚአብሔር መንግሥት ሥር፡ በኢትዮጵያዊነት እየተገለገሉና እያገለገሉ፡ በፍቅርና በሰላም፡ መጀመሪያ፡ በዚህ ዓለም፡ ኖሩ! ከዚያም፡ ዛሬና ወደፊት፥ ለዘለዓለምም፡ በወዲያኛው ዓለም፡ በሕያውነት እየኖሩ ናቸው፡፡ እርስዎም፡ በዓለም ስምዎ፡ "ግርማ"፥ በእግዚአብሔር ልጅነትዎ ስም ደግሞ፡ "መክብበ ማርያም" የተባሉት፡ ምናልባት አላወቁት እንደኾነ እንጂ፡ እስካኹን የኖሩት፥ አኹንም እየኖሩ ያሉት፥ ወደፊትም የሚኖሩት፡ በዚህ መልክ ነው፡፡ "ዐማራ" መኾን ማለት፡ እንግዴህ ይህ ነው፡፡ በእግዚአብሔር ሕይወት፡ ነጻ ኾኖ ለሚኖርበት፡ ለኢትዮጵያዊነት ጸጋና ክብር የሚያበቃ፡ የህልውና ሥርዓት ስም እንጂ፡ ለምሳሌ፡ እንደአገውነት፥ ትግሬነት፥ ጕራጌነት፥ ሓዲያነት፥ ወላይታነት፥ አደሬነት፥ አዳልነት፥ ወይም ኦሮሞነት፡ በጠባብ ጎሠኛነት፡ ለያይቶና ከፋፍሎ የሚያኖር የጐሣ ስም አይደለም፡፡

የዚህን አባባሌን እውነተኛነት፡ ራስዎም፡ በገሃድ ይመለከቱታል፤ እስኪ እግዚአብሔር ያሳይዎ! ፈጣሪ አንድ ባደረገውና ወላጆቹ በተሠዉለት፡ በኢትዮጵያ አንድ ብሔርነት፥ አንድ ሕዝብነትና አንድ መንግሥትነት፡ እስከዛሬና ዛሬም፡ ከልቡ አምኖ፡ በሰላሙ ዘመን፡ በወዙ እየታገለ፥ በችግሩም ጊዜ፡ ደሙን እያፈሰሰ የኖረው፥ አኹንም፡ እየኖረ ያለው፡ ማነው? እንደአባቶችዎ፡ በዐማራነቱ ያመነው ወገን አይደለምን? እንደእርስዎ ያለው፡ ጎሠኛውማ፡ ይኸው፡ ይህን አንድነት፡ ለመለያየትና ለመከፋፈል ሲዳክር ይታያል፡፡ አባቶችዎን የመሰሉት፡ ደጋጎቹ የቀደሙት ኢትዮጵያውያንና ኢትዮጵያውያት፡ መሥራቿ ኾኖ ያቋቋማትና ባለቤትዋ ኾኖ የሚመራት፥ እረኛዋም ኾኖ የሚጠብቃት፡ ራሱ፡ ፈጣሪ መኾኑን በማረጋገጥ፡ እርሱን፡ አምላካቸውን፡ "እግዚአ 'ብሔር'"፥ እርሷን፡ አንዲት አገራቸውንም፡ "ብሔረ ኢትዮጵያ" ብለው ሠይመው፡ በአንድነት ኖረውባታል፤ በአንድነት አኑረዋታልም፡፡ እንዲህ፡ በአንድነት የኖሩትን፡ አንዲቱን "ብሔር"፥ አንዱን ሕዝብ፥ አንዱን መንግሥት፡ እርስዎና መሰሎችዎ፡ አልሳካ አላችሁ እንጂ፡ ለያይታችሁና ከፋፍላችሁ፡ "ብሔሮች"፥ "ሕዝቦች" እና "መንግሥቶች" በሚል ባዕድ ዘዬ፡ ልታባዙ እየሞከራችሁ አይደለምን? ይኸውም፡ "የትግሬ ብሔር፥ ሕዝብና መንግሥት"፥ "የጕራጌ ብሔር፥ ሕዝብና መንግሥት"፥ "የኦሮሞ ብሔር፥ ሕዝብና መንግሥት" እያላችሁ ማለት ነው፡፡

በዘርና በሃይማኖት ጎሠኝነት ላይ የተመሠረተውን፡ ይህን ክፉ ድርጊታችሁን፡ በእውነትና በመንፈስ ቅዱስ ኃይል ተቃውመው ለመደምሰስ፡ የቅርብ ጊዜ ቁርጥ አርበኞች ኾነው የተሠዉ፥ ሕያዋን ምስክሮች ኾነውም የሚጠሩ፡ ከእርስዎ አባቶች ጋር፡ ለመልካም አብነት ከሚጠቀሱት ዕልፍ አዕላፋት ስመ-ጥሩዎች መካከል፡ በጣት የሚቆጠሩትን፡ እጅግ ጥቂቶቹን ብቻ ማውሳት ይቻላል፤ እኒህም፡ በትግሬዎች በኩል፡ እነአጼ ዮሓንስና እነራስ አሉላ፥ በኦሮሞዎችና በጉራጌዎች፥ በእስላሞችም በኩል፡ "መሓመድ አሊ" ይባሉ የነበሩት፡ እነንጉሥ ሚካኤል፥ እነራስ ጐበና ዳጨውና እነደጃዝማች ባልቻ አባ ነፍሶ፡ ቀደምት ኾነው የሚገኙት ናቸው፡፡

የእውነተኞቹ ኢትዮጵያውያን አባቶችዎ አምላክ፡ የኢትዮጵያን ብሔር፥ ሕዝብና መንግሥት አንድነት ለማረጋገጥ፡ በዚህ ረገድ፡ በዘመናችን፡ በእውን እየሠራ ያለውን ተአምር፡ አስተውሎ ለመመልከት፡ ከሥራዎቹ መካከል፡ መጠቃቀስ ይቻላል፤ እነዚህም፡-

-እግዚአብሔር የሠራውን ሥርዓተ ብሔር፥ ሥርዓተ ሕዝብና ሥርዓተ መንግሥት በማፍረስ፡ የእርስዎንና የመሰሎችዎን ዓላማ፡ በተግባር ለማዋል፡ ከሠላሳ ዓመታት በፊት የተነሣው የቅጣት እሳትና የጥፋት ማዕበል፡ በጠላት በኩል፡ በምኞት እንደታቀደው፡ ይህችን አገር፡ ሳይለያይና ሳይከፋፍል፥ ሕዝቧንና መንግሥቷንም ሳይደመስስ፡ እነሆ፡ የአገሪቱ፡ የነጻነት ህልውና፡ "ኢትዮጵያ" ከሚለው፡ የአንድነት ስሟና ሰንደቅ ዓላማዋ፥ ሕዝቧና መንግሥቷ ጋር፡ እስካኹን፡ በአንድነት ጸንቶ መገኘቱ፥

-ቀድሞ፡ “የባሕር ነጋሽ ግዛት”፥ ዛሬ “ኤርትራ” የሚባለው፡ የኢትዮጵያ ሰሜናዊ ክፍለ አገር፡ በባዕዳን የጠላትነት ድርጊት፡ ለጥቂት ጊዜ፡ በቅኝ አገዛዝ ቀንበር ሥር ወድቆ ከቆየ በኋላ፡ ያለጦር ኃይል፡ በእግዚአብሔር ሥርዓተ መንግሥት በተካኼደው፡ ሰላማዊ ትግል ብቻ፡ በጽሞና፡ ወደእናት አገሩ ተመልሶ መዋሐዱ፥ ዳሩ ግን፡ ትውልዱ፡ ከእግዚአብሔር ሥርዓተ መንግሥት ውጪ ኾኖ፡ በጦር ኃይል በመጠቀሙ፡ ያው ግዛት፡ ይባሱኑ፡ ራሱን እንደባዕድ አገር ቆጥሮ፡ ከእናት አገሩ መገንጠሉ፥ ወደፊትም፡ እንደገና፡ ወደእናት አገሩ ተመልሶ፡ በሰላም ሊዋሐድ የሚችለው፡ በዚሁ ሥርዓተ መንግሥት አማካይነት ብቻ መኾኑ፥

- የኢትዮጵያውያንና የዓለም ልሳናት፡ መሠረትና ምንጭ የኾነው፡ “ግእዝ”፥ ከእርሱ የተገኘውም፡ “ኢትዮጵያኛ” የሚባለው፡ “ዐማርኛ”፡ ከምግብ ገበታችንና ልብሳችን ጋር፡ ይኸው፡ እስካኹን፡ የኢትዮጵያውያን ኹሉ መገናኛና መግባቢያ፥ መዋሐጃና መታወቂያም ኾኖ መቀጠሉ ናቸው።

“ዐማራ ነኝ!” ከሚለው ወገን መካከልም ቢኾን፡ በእግዚአብሔር መልክ የተፈጠረውን፡ ማናቸውንም ሌላ ሰው፡ እንደራሱ፡ በእኩልነት ዓይን አይቶ፡ የፍቅር ምግባርን የሚፈጽምለት ካልኾነ በቀር፥ ማለትም፡ በዕብሪትና በትምክህት ክፉ መንፈስ ተመልቶ፡ ራሱን፡ ከፍ፥ ሌላውንም፡ ዝቅ አድርጎ የሚመለከትና የሚይዝ ከኾነ፥ እርስ በርሱም፡ “እኔ 'ሸዌ' ነኝ!”፥ “እኔ 'ጎጃሜ' ነኝ!”፥ “እኔ 'ጎንደሬ' ነኝ!”፥ “እኔ 'ወሎዬ' ነኝ!”፥ ከዚህ አልፎም፡ በጎጠኝነት፡ “እኔ 'መንዜ' ነኝ!”፥ “እኔ 'ዳሞቴ' ነኝ!”፥ “እኔ 'ጋይንቴ' ነኝ!”፥ “እኔ 'የጁዬ' ነኝ!” በማለት፡ ራሱን የሚከፋፍል ከኾነ፡ ይህን የመሰለው፡ ሰብአዊ ፍጡር፡ “ዐማራ” አይደለም፤ “ክርስቲያን”ም አይደለም፤ “ኢትዮጵያዊ”ም አይደለም።

እርስዎ ግን፡ “እውነተኛ ኢትዮጵያዊ” የሚያሰኙትን ባሕርያት፡ እንዲህ፡ ከወላጆችዎ ወርሰውና ራስዎም ተቀብለው፡ ይዘው የሚገኙ በመኾንዎ፡ “ሙሉ ዐማራ ነኝ!” ሊሉ ሲገባዎ፡ አላሉም። እንዲያውም፡ በመጽሓፍዎ ውስጥ፡ ይህን እውነታ አድበስብሰው ሊያልፉት ሞክረዋል፤ “ዐማራ” መባልንም የፈለጉ አይመስልም፤ ይልቁንም፡ ዐማራነትዎን ለመሻር እንደፈለጉ በገሃድ ይታያል። ምክንያቱም፡ ራስዎን፡ ለአንባቢው፡ አጋንነው ያስተዋወቁት፥ አብራርተው የጻፉትም፡ በይበልጥ፡ በአባትዎ የጕሣ ሓረግ በኩል ያለውን፡ ኦሮሞነትዎን ብቻ በመኾኑ ነው፤ ጉራጌነትዎንም ቢኾን፡ በውስጠ-ታዋቂ አመለከቱት እንጂ፡ በግልጽ ሊያነሡት አልደፈሩም፤ “ዐማራነትዎን”ማ፡ እንኳንስ፡ ቁም ነገሩን፡ ስሙን እንኳ አልጠቀሱትም፤ ለምን?

የሚገርመው ደግሞ፡ ከአቶ ሉጫ አረዶ የተወለዱትና “ዐማራነታቸውን”፡ በሃይማኖትም፥ በምግባርም ያረጋገጡት፡ አባትዎ ግራዝማች ወልደ ጊዮርጊስ፡ “ዐማራነታቸው” ከተረጋገጠላቸው፡ ከአቶ መኰሪያ ካብትህይመርና ከወይዘሮ በላይነሽ አሰግዴ የተወለዱትን፡ ዐማራዋን ወይዘሮ ወሰንየለሽን አግብተው፡ እርስዎን በመውለዳቸው፥ እርስዎ፡ የ“ዐማሮች” ልጅ፡ ፍጹም “ዐማራ” መኾንዎ ነው። እርስዎም፡ በተወለዱ፡ በአርባ ቀንዎ፡ የክርስትና ጥምቀትን ተቀብለውና “መክብበ ማርያም” ተብለው፡ በመንፈስ ቅዱስ የተቀዳጁትን፡ የእግዚአብሔር ልጅ የመኾንን ክብር፡ እስካኹን አጽንተውት በመኖርዎ፡ “ዐማራነትዎን” ራስዎም አምነውበትና በይፋ አሳውቀው፥ ሠርተውበትና ተሹመውበት ኖረዋል።

ክቡር የመቶ አለቃ! አላስተዋሉትም እንዴ! አባትዎም፥ እናትዎም፡ እየራሳቸውን ያውቁትና ለሌላውም አሳውቀው የኖሩት፥ ለእርስዎም አውርሰዎ ያለፉት እኮ፡ ራስን፡ ከኹሉም ዓይነት ጨቋኝ ኃይል፡ ነጻ አድርጎ፡ ለፍጹም ኢትዮጵያዊነት ያበቃዎትን “ዐማራነታቸውን” እንጂ፡ ወደ“ኦሮሞነት”፥ ወይም፡ ወደ“ጕራጌነት” የሚመልስዎትን፡ ጠባቡን የጎሠኝነት አስተሳሰብና ይትበሃል አይደለም። ይህን ጎሠኝነቱንማ፡ እንደነርሱ፡ እርስዎም፡ በመንፈስ ቅዱስ የእውቀትና የዕድገት ጸጋ፡ ትተውትና ተሻግረውት ከመጡ ዘመናት የተቈጠሩ አይደለምን? አለዚያማ፡ ወላጆችዎ፡ በጎሠኝነቱ የሚያምኑ ቢኾኑ ኖሮ፡ ቀድሞውንስ፡ መቼ ይጋቡ ነበር? እርስዎስ፡ ከእነርሱ፡ መቼ ይወለዱ ነበር?

እውነታው፡ ይኼ ስለኾነ፡ ልንክደው ከቶ አይቻለንም፤ እግዚአብሔር የሠራውና የመሠረተው፥ ያጸናውና የጠበቀው፥ ወላጆችዎም፡ ማናቸውንም ዓይነት መሥዋዕትነት እየከፈሉበት ያኖሩት ስለኾነ፡ ይህ እውነታ፡ በምንም መንገድ ሊለወጥና ሊፈርስ አይችልም።

እስኪ፡ በራስዎ ላይ የደረሰውንና በመጽሓፍዎ ውስጥ ያስረዱትን፥ እስከዛሬም መፍትሔ ያላገኙለትን ውስብስብ ችግር ይመልከቱት! ኹሉም፡ የየራሱን፡ የውስጥ ማንነቱን፡ በግሉም፥ በቤተሰቡም፥ በኅብረተሰቡም ዘንድ ጠብቆ፡ በአገር ደረጃ ግን፡ በኢትዮጵያዊነት፡ ተስማምቶና ተባብሮ፡ በፍቅርና በሰላም ይተዳደር በነበረበት፡ በዚያ፡ እርስዎና እኔ በምናውቀው፡ በእግዚአብሔር ሥርዓተ መንግሥት ዘመን፡ "ክስታኔ" በተባሉት፡ በሶዶ ጉራጌዎችና በሶዶ በሚኖሩ ኦሮሞዎች መካከል፡ ምንም ዓይነት ችግር፥ ጥያቄም አልነበረም። እንዲያውም፡ የጠንቀኛው ጎሠኝነት ፈሊጥና አመራር፡ መስፈን በጀመረበት ጊዜ፡ የሶዶ ጉራጌዎች፡ ለረዥም ዘመን፡ በመካከላቸው፡ በሰላም የሚኖረውን፡ ሌላውን ወገን ኹሉ፡ "ኦሮሞ ነኝ!" የሚለውን ጭምር፡ የጎሣ ልዩነት ሳያደርጉበት፡ "ክስታኔ ነህ!" ማለትም፡ "እንደኛው፡ የሶዶ ጉራጌ ነህ!" ብለው አቅፈው ለማኖር ያካኼዱትን ጥረትና ትግል፥ እርስዎም፡ ይህንኑ ጥረታቸውንና ትግላቸውን፡ በአንድ በኩል፡ እንዴት አድርገው፡ እንዳመከኑባቸው ጠቅሰውታል፤ በዚህ አንጻር ደግሞ፡ ለራስዎ ያላደረጉትን፡ ነገር ግን፡ እርስዎ፡ "ምንም አያውቁም!" በሚሏቸው፡ በንጹሓኑ ወገኖች እርካብነት፡ የሥልጣን ፍትወትዎን ለማርካት ሲሉ፡ "የለም፤ እኛ ኦሮሞዎች ነን እንጂ!" አሰኝተው፡ እንዳሞኟቸውና አንድ፡ ወንድማማች የኾኑትን የኢትዮጵያ ልጆች እንደለያዩዋቸው፡ ያለኀፍረትና ያለይሉኝታ ጽፈውታል።

ለዚህ ሙያዎ፡ መርህ ያደረጉትን ፍልስፍናዎን፡ ራስዎ፡ ደግመው እንዲያጤኑት፡ እስኪ፡ በመጽሓፍዎ ውስጥ የሠፈረውን የራስዎን ቃል ልጥቀስልዎ! ይኸውም፡ ***"በመሠረቱ፡ ማንነትን፡ መፍጠርም ኾነ፡ ያልኾኑትን፡ 'ነህ!' ማለት፥ ወይም፡ የኾኑትን፡ 'አንተ፡ አይደለህም!' በማለት፡ መስጠትም ኾነ፡ መውሰድም፡ የማይቻል ሃሳብ ነው።"*** የሚለው ነው። ይህን ሲሉ፡ ከቶ ምን ማለትዎ ይኾን? በየቦታው እንዳብራራሁት፡ ራስዎ፡ ለራስዎ፡ የሌለውን "ማንነት"፡ አልፈጠሩምወይ? አዎን፥ ፈጥረዋል፤ ያልኾኑትንስ፡ "ነኝ!" አላሉምወይ? አዎን፥ ብለዋል፤ "'አንተ፡ አይደለህም!' በማለት፡ መስጠትም ኾነ፡ መውሰድ፡ የማይቻለውን አሳብ"፡ እርስዎ፡ በራስዎ ላይ፡ እንዲቻል አላደረጉትምወይ? አዎን፥ አድርገውታል። ታዲያ! ራስዎ የካዱትን ማንነትዎን፡ ለጥቅምዎ ሲኾን፡ እንዴት፡ ሌሎች አምነው እንዲቀበሉትና እንዲፈጽሙት ያደርጋሉ? ይህን የመሰለውን አድራጎት፡ እንግዴህ፡ ምን ይሉታል? እግዚአብሔርና ይህ የተንኰል በደል የተፈጸመበት ሕዝብ፡ በየበኩላቸው ይፍረዱ እንጂ፡ ሌላማ፡ ምን ይባላል!?

አኹን ግን፡ እርስዎና እርስዎን የመሰሉ ሰዎች፡ አባቶቻችንና እናቶቻችን፡ በከባዱና በረቀቀው፥ እጅግ በበዛውና በረዘመው፡ የሕይወት መሥዋዕትነታቸው ያዋሓዱትን፥ እግዚአብሔርም፡ በልጁ ደም ሳይቀር፡ አንድ ያደረገውን ሕዝብ፡ ለመለያየት በመሞከር፡ የጎሠኝነትን ጠንቅ ፈጥራችሁ፡ በእነዚህ ኢትዮጵያውያን መካከል ጸንቶ የቆየውን አንድነት ስላፈረሳችሁት፡ በአንዲት፡ አነስተኛ፡ የኢትዮጵያ ምድራዊ ክልል ውስጥ እንደቤተሰብ፡ ተፈቃቅረውና ተፈቃቅደው፡ እየተጋቡና እየተዋለዱ፥ አብረው፡ በሰላምና በፍቅር ይኖሩ የነበሩት፡ እኒህ፡ የአንዲት ኢትዮጵያ ልጆች፡ ዛሬ፡ ይኸው፡ "የሶዶ ጉራጌዎች" እና "የሶዶ ኦሮሞዎች" ተባብለው እንዲለያዩና ለኹለት እንዲከፈሉ ኾኖ፡ እነሆ፡ በእርስዎና እርስዎን በመሰሉት፥ በሌላውም ባዕድ አማካሪ ዘንድ፡ መፍትሔ ሊገኝለት የማይቻል፡ ያልነበረ ችግር መጣ! ይህ ችግር፡ እኒህንና መላውን የኢትዮጵያ ሕዝብ፡ እከባድ ጉዳት ላይ ሲጥል፡ እርግጥ፡ እርስዎን ጠቅሟል፤ ምክንያቱም፡ "ከኹለቱም ጎሣዎች ተወልጃለሁ!" የሚሉት እርስዎ፡ ይህንኑ አባባልዎንና ማንነትዎን፡ እንደገና ክደው፡ በራስዎ ብቻ፡ "ኦሮሞ ነኝ!" ስላሉ፥ ብዙ ቁጥር ወዳለው፡ ወደኦሮሞው ጎሣም ስለወገኑ፡ ይኸው፡ አብዛኛውን የምርጫ ድምፅ አግኝተው፡ ዛሬ ላሉበት ቦታ ያበቃዎ በመኾኑ ነው።

ቀድሞዉንም ቢኾን፡ የጎሠኝነቱ መሠረታዊ ፈሊጥ የተፈለገው እኮ፡ ለዚሁ፡ የጥቂቶችን የሥልጣን ጥማት ለማርካት ስለኾነ፡ አዎን! ለእርስዎና እርስዎን ለመሰሉትም ኹሉ፡ ይኸው፡ ሠርቶና ጠቅሞ ተገኝቷል።

ምንጊዜም፡ የሥልጣን ጥመኞች፡ ይህን የመሰለውን፡ አቋራጭ መንገድ እንዲከተሉ የሚገደዱት፡ ያለምክንያት አይደለም፤ የሥልጣኑ መድረክ፡ እጅግ ከመስፋቱና መሰላሉም፡ ወደዐናቱ ግድም፡ እጅግ እየጠበበ የሚኼድ ከመኾኑ የተነሣ፡ ከአያሌዎቹ ባለሙያዎች ጋርና መካከል ኾኖ፡ መወዳደሩ ስለሚያቅታቸውና ስለሚያስጨንቃቸው ነው፤ አዎን! እንደእነፊታውራሪ ሀብተ ጊዮርጊስ ያሉት፡ ብዙዎች ባለሙያዎች በሚካፈሉበትና ለሥልጣን ብቁ በሚያደርገው፡ በሙያው የትግል መስክ ላይ፡ የሚቀርበውን ውድድርና ፈተና ተቋቁመው ማለፍና ማሸነፍ እንደማይቻላቸው ስለሚያውቁት ነው፤ ይህን ኹሉ የአርበኝነት መሥዋዕትነት፡ ገና ሲያስቡት ስለሚዘገንናቸው፡ እኒህ፡ የሥልጣን ጥመኞች፡ የሥልጣን ጥማታቸውን ለማርካት ብቻ ሲሉ፡ የወንድማማችንና የእኅትማማችን ደም እስከማፋሰስ ያደረሰውንና የሚያደርሰውን፡ አቋራጩን፡ የጎሠኝነት አመራር ፈሊጥ አንግበው ይነሣሉ፤ ሊጠቀሙበት፥ ቢያስፈልግም፡ ለእርድ ያዘጋጁትን፡ የዋሁንም ሕዝብ፡ እንዲከተላቸው፡ በተንኰል ሞረድ በሰላና በጠንቀኛ መርዝ በታለለ፡ በዚያ፡ ማር-ለበስ አንደበታቸው ያሳምኑታል፤ ያን፡ በምኞት ሲቃጠሉበት የኖሩትን የብልጠት ልጓም ከጨበጡ በኋላ ግን፡ ያን ያሞኙትን ሕዝብ መልሰው፡ እርሱ፡ አድልቦ ባበረከታቸው የሥልጣን ፈረስና አደላድሎ በጫነላቸው የሀብት ኮርቻ ላይ ተቀምጠው፡ ይጋልቡበታል፤ ይፈነጩበታል፤ ጉግሥ ይጫወቱበታል።

እግዚአብሔር ወልድ ኢየሱስ ክርስቶስ፡ ሰው ኾኖ፡ በደሙ የዋጃቸውን፡ የደካሞቹንና የየዋሆቹን ጥቅምና ደኅንነት መሥዋዕት በማድረግ፡ እንዲህ፡ የራስዎ ፍላጎት ስለተፈጸመና ዓላማዎ ከግብ ስለደረሰ፡ የተከተሉት መንገድ፡ በኢትዮጵያዊነት ዓይን ሲታይ፡ ትክክል ነው ማለት አይደለም። ምክንያቱም፡ ከላይ እንደተብራራው፡ እርስዎ፡ ይህን አኹን የያዙትን ቦታ ያገኙት፡ ያልኾኑትን፡ በሓሰት "ነኝ!" ብለው ስለኾነ ነው፤ ይኸውም፡ ራስዎ እንዳረጋገጡትና እውነታውም እንደሚያሳየው፡ እርስዎ፡ እንደማናቸውም ኢትዮጵያዊ፡ "ሙሉ ዐማራ" ነዎት እንጂ፡ ብቻው ጉራጌ፥ ወይም፡ ብቻው ኦሮሞ አይደሉም፤ ከዚህ "ዐማራነትዎ" የተነሣ፡ አዎን፥ እርስዎ፡ "ኢትዮጵያዊ" ነዎት። የኢትዮጵያና የወላጆችዎ፥ የእርስዎም አምላክ፡ እግዚአብሔር፡ ለዚህ ክብር ያበቃዎት፥ የሌላውን አላውቅም እንጂ፡ እኔም፡ በዚሁ ማዕርግዎ የተቀበልሁዎ፡ በዚሁ ኢትዮጵያዊነትዎ መኾኑን፡ እርስዎም አምነው እንዲቀበሉት እሻለሁ።

በእርስዎ ዘንድ፡ ይህ የጎሠኝነት ጠንቅ፡ እጅግ የጸናብዎ መኾኑ የሚታወቀው፡ በቅርቡ፡ ለግል ጉብኝት፡ ወደዋሽንግተን ዲሲ ከተማ መጥተው ሣለ፡ በዚህ አካባቢ ለሚኖረው የኢትዮጵያ ኅብረተሰብ ባሰሙት ንግግር፡ በአጼ ኃይለ ሥላሴ ዘመን፡ በኢትዮጵያ፡ "የተደረገ ነው!"፥ ዛሬም፡ በአሜሪካ ግዛት፡ "እየተደረገ ነው!" ብለው፡ እርስዎና እርስዎን የመሰሉት ጥቂቶች፡ ለምታራምዱት የጎሠኝነት ፈሊጣዊ አመራር፡ የሚያግዙ መስሎዎ፡ ስላቀረቧቸው ምሳሌዎች የተናገሩትን ቃል፡ በአንድ፡ የኢትዮጵያ መንግሥት ነፋስ ድምፅ ላይ፡ ራሴ ሰምቼዋለሁ፤ በዚያ ንግግርዎ፡ አጼ ኃይለ ሥላሴ፡ እርስዎ፡ እንደጎሣ ለቆጠሩትና እኔ በበኩሌ ግን፡ ሰምቼው ለማላውቀው፡ ለአንድ የዐምሓራ ማኅበር፡ የበላይ ኾነው ይመሩ እንደነበሩ በመግለጽ፥ የአሜሪካ ጥቁሮችም፡ በዚህ አገራቸው፡ በጎሠኝነት እምነት ላይ የተመሠረተ፡ የራሳቸውን የዘር ልዩነት የሚያንጸባርቅ ድርጅት አቋቁመው የሚሠሩ በማስመሰል፡ ስለምሳሌዎቹ አብራርተዋል፤ አድማጩ ሕዝብ፡ እርስዎ የሚከተሉትን፡ ጠባቡን የጎሠኝነት እምነት፡ "ትክክለኛና መልካም ነው!" ብሎ፡ ምሳሌዎችዎን፡ በማሳመኛ ማስረጃነታቸው እንዲቀበላቸው፡ የተቻለዎትን ሙከራ አድርገዋል።

እኔ በማስታውሰው መጠን፡ አጼ ኃይለ ሥላሴ፡ ለምሳሌ፡ እርስዎና እኔ፡ በመሥራች አባልነት ላቋቋምነው፡ ለ"ኢትዮጵያ ድርሰት ማኅበር"፡ ጠይቀን እንደነበረው፥ ፈቃዳቸውን ለጠየቀ፡ ለማናቸውም ሕዝባዊ የልማት፥ ወይም፡ የሙያ ማኅበር፥ እርስዎ፡ አባል ለነበሩበት፡ ለሜጫና ቱለማ የልማት ማኅበርም እንኳ ቢኾን፥ የበላይ ጠባቂ ይኾኑ እንደነበረው ዓይነት፡ ምናልባት፡ እርስዎ ላሉት፡ ሕዝባዊ፥ ወይም፡ ማኅበራዊ ድርጅት፡ በዚያ መልክ፡ የበላይ ጠባቂነቱን ተጠይቀው፡ ፈቅደው ይኾናል እንጂ፡ በዚያን ጊዜ፡ አኹን፡ እርስዎ በሚያምኑበት፡ የሳሣኝነት መንፈስ ለተደራጀ ሕጋዊ አካል፡ እርሳቸው፡ "ይህን አቋም ይይዛሉ!" ብሎ ለማመን እጅግ ያዳግታል።

የአሜሪካ ጥቁሮችም ቢኾኑ፡ እርስዎ አምነው በሚሠሩበት ዓይነት፡ "እስከመገንጠል" የሚያስችል፡ ሕጋዊ መብት ያለው፡ የጎሣ ድርጅት፡ በአገራቸው ያቋቋሙ መኾናቸውን አላውቅም፤ ሕገ መንግሥታቸውም የሚፈቅድላቸው አይመስለኝም፤ ካለም፡ ብዙዎቹ የአገሩ መንግሥት፡ የጸጥታና የደኅንነት መሥሪያ ቤቶች፡ እንኳንስ፡ እንደርስዎ ባለ፡ በአንድ የአገር ርእሰ ብሔር አንደበት የተነገረውን ቀርቶ፡ በሥውር የተተነፈሰውንና በሉኖሳስ የተነገረውን ሳይቀር ተከታትለው ስለሚደርሱበት፡ "ጥሩ ፍንጭ አበርክተዋቸዋል!" ማለት ነው። አለዚያ ግን፡ በርእሰ ብሔርነትዎ፡ የኢትዮጵያን ሕዝብና መንግሥት የሚወክሉ ስለኾኑ፡ እንኳንስ፡ የእንግድነት ቆይታ ባደረጉበት አገር፡ የውስጥ ጉዳይ፡ ይህን የመሰለ ትችት መስጠት ይቅርና፡ በሌላውም፡ በሚያስቡት፥ በሚናገሩትና በሚያደርጉት ኹሉ፡ በብርቱ ሊጠነቀቁ የሚያስፈልግ ይመስለኛል። ከዚህ ጋር በተያያዘ የሚደንቀኝ ነገር ቢኖር፡ የእርስዎን ንግግር ለመስማት ተሰብስቦ ለነበረው ኅብረተሰብ፡ እርስዎ፡ ስለአሜሪካ ጥቁሮች፡ በጥያቄ መልክ ለሠነዘሩለት፡ ከላይ ለተጠቀሰው አስተሳሰብዎ፡ ከመካከሉ፡ መልስ ሊሰጥዎ የሞከረ፡ አንድም ኢትዮጵያዊ መኖሩን ሳልሰማ በመቅረቴ ነው።

እዚህ ላይ፡ የእርስዎ ንግግር በተላለፈበት፡ በዚያው ነፋስ ድምፅና በዚያው ዝግጅት፥ በዚያው ሰዓትና በዚያው አቅራቢ፡ ልዩ አርእስት ይዞ፡ ተከታትሎ የተደመጠ፡ አንድ ሌላ እንግዳ ተናጋሪ እንደነበር አወሳልዎ ዘንድ እገደዳለሁ፤ ያም ልዩ አርእስት፡ በርስዎ በኩል የቀረበውን የሚቃረንና እርስዎ የገነቡትን የሚያፈራርስ ስለነበረ፡ ይህ ዝግጅት፡ ኾን ተብሎ የተቀነባበረ፥ ወይም፡ በአጋጣሚ የደረሰ ይኹን፡ ለማወቅ፡ በእኔ በኩል፡ እንደተሳነኝ እገኛለሁ።

አርእስቱ፡ ብሔራዊ ቋንቋችን የኾነውን "ዐማርኛ"ን የሚመለከት ሲኾን፡ ይህ፡ ኢትዮጵያኛ ቋንቋችን፡ በገዛ አገሩ እየተሰጠው ያለው ግምትና ለወደፊት የሚጠብቀው ዕድል፡ ገና ያልተረጋገጠ በኾነበት፥ በተለይም፡ እርስዎ በሚወክሉት የኦሮሞ ጎሣ ዘንድ፡ ብሔራዊ ህልውናው ተሠርዞና በላቲኑ የባዕዳን ፊደል ተተክቶ ባለበት ጊዜ፡ የተባበሩት የአሜሪካ ግዛቶች መናገሻና የዓለም አህጉራት መናኸሪያ ከተማ ለኾነችው፡ ለዋሽንግተን ዲሲ፡ አንዱ መንግሥታዊ ቋንቋ ኾኖ እንዲያገለግል፡ በሕግ መታወጁን መነሻ በማድረግ፡ የቀረበ ልዩ ዝግጅት ነበር።

ያ እንግዳ፡ በዚያ ዝግጅት ላይ የተናገረው ቁም ነገር፡ ፍጹም እውነተኛነቱ፡ የኢትዮጵያው ርእሰ ብሔር እርስዎ፡ ቀደም ብለው ከሰጡት መግለጫ አንጻር ሲታይ፡ የእርስዎን ስሑት ዓላማ፡ ውድቅ ለማድረግ፡ መከላከያ ኾኖ እንዲያገለግል መቅረቡ፡ በገሃድ ስለሚታወቅ፡ በዝግጅቱ ውስጥ፡ የኢትዮጵያ አምላክ፡ ረቂቅ እጅ እንዳለበት አልጠራጠርም፤ ያ እንግዳ ተናጋሪ፡ እርሱ ራሱ፡ በሃይማኖቱ፡ እስላም፥ በጎሣው፡ አደሬ፥ ልሳኑ፡ አደሬኛ ሲኾን፡ ከሌሎቹ ኢትዮጵያውያን ጋር የሚያገናኘውና አንድ የሚያደርገው፥ በዓለም ሕዝቦችም ዘንድ፡ በማንነቱ የሚያሳውቀውና የሚያኮራው፡ ያ የጎሣ ማንነቱ ሳይኾን፡ ለኢትዮጵያዊነቱ መለያና መመኪያ የኾነው፡ ይህ፡ ኢትዮጵያኛው ቋንቋ "ዐማርኛ" መኾኑን፡ እያብራራ በኩራት ሲናገር፡ ሰሚውን፡ እውነተኛ ኢትዮጵያዊ ኹሉ እንዳኮራ አምናለሁ።

ለዚህ እውነታ ትክክለኛነት፡ ማረጋገጫ ይኾነው ዘንድ ያቀረበው ማስረጃ፡ የዝግጅቱ አስተናባሪ ላቀረበለት ጥያቄ፡ በሰጠው፡ ቀላልና ግልጽ፥ ቀጥተኛና አጭር በኾነው መልሱ ውስጥ፡ ተጠቃልሎ ተሰምቷል፤ ይኸው መልሱ፡ ይህን በሚመስል ቃል ይነበባል፦

"እየው! ተመልከተው! ራሳችንን፡ 'ኢትዮጵያውያን' ብለን የምንጠራውን፡ እኛን፡ የሕዝብ ወገኖች፡ ማለትም፡ አንተን ጠያቂውን፥ እኔን ተጠያቂውንና ሌሎቹን አድማጮቻችንን፡ በዚች አፍታ፥ በዚህ መድረክ ላይ፥ በዚህ ጉዳይ፡ ያገናኘ፥ ያነጋገረና ያወያየ፥ ያግባባና ያስማማ፥ በጠቅላላ አንድ ያደረገ፡ ማን ወይም ምን ይመስልሃል? ይህ፡ "ዐማርኛ" የምንለው፡ ኢትዮጵያኛው ቋንቋችን አይደለምን? እንግዴህ፡ እኛ ኢትዮጵያውያን፡ በሌላውም ኹሉ፡ ኾነን ልንገኝ የሚገባን፡ እንዲህ ሊኾን ይገባል!"

እርስዎስ ቢኾኑ፡ "ኦሮሞ ነኝ!" ካሉና በእርግጥ ኦሮሞ ከኾኑ፥ ከዐማራነትዎ ይልቅ ኦሮሞነትዎን ካስበለጡና ካስቀደሙም፡ ይህን የሕይወት ታሪክዎን፡ ጊዜ ጠብቀው ለመረጡት፡ ለዚሁ ጎሣ፡ ታማኝ ኾነው በመገኘት፡ ለምን፡ በኦሮሞ ቋንቋዎና በባዕዱ Latin ፊደልዎ ጽፈውና አሳትመው አላሠራጩትም? ለምን ኢትዮጵያኛ ቋንቋችን በኾነው፡ በ"ዐማርኛ" ፊደልና ቋንቋ፡ ጽፈውና አሳትመው አሠራጩት? ከኦሮሞ ቋንቋዎና ከባዕዱ የLatin ፊደልዎ ይልቅ፡ የ"ዐማርኛ"ው፡ የሚሻልዎና የሚበጅዎ ስለኾነ አይደለምን? የኢትዮጵያ ልጆች የኾኑት ወላጆችዎና እነርሱን የመሰሉት፡ ዐማሮች አባቶችና እናቶች፡ ግእዝን መሠረት አድርገው፡ "ዐማርኛ"ን፡ ከነሥነ ጽሑፉ የፈጠሩት፡ ያለምክንያት እኮ አይደለም፤ የተቀደሰ ታላቅ ዓላማ ነበራቸው:: ያም፡ "በጎሣና በቋንቋ፥ በእምነትና በባህል የተለያዩትን ወገኖች፡ በማገናኘትና በማግባባት፥ በማስማማትና በማዋሓድ፡ ልጆቻቸው፡ በእግዚአብሔር ሃይማኖትና ምግባር፡ አንድ አገርና አንድ ሕዝብ ኾነውላቸው፡ በነጻነትና በሰላም፡ በልጽገው ለመኖር እንዲችሉ፡ 'ያስፈልጋቸዋል፥ ይጠቅማቸውማል!'" ብለው አምነው፡ ለኢትዮጵያና ለኢትዮጵያውያን አገልግሎት ይውል ዘንድ፡ የፈጠሩላቸው ፍቱን መሣሪያነቱ ነው:: ለእርስዎና "ዐማርኛ"ን፡ በዚሁ መንፈስ እየተጠቀመበት ላለው፡ ለዛሬው የኢትዮጵያ አገዛዝ፡ እውነታውን፡ በዚህ ገጽታው፡ ለመመልከት የሚከብዳችሁ አይመስለኝም!

ክቡር ርእሰ ብሔር!

ፈቃድዎ ኾኖ፡ በዚህ የመልስ ደብዳቤዬ የተካተተውን ምዕዳኔን የሚቀበሉት ቢኾን፡ ለዚህ ላበቁዎ ወላጆችዎ፥ ዛሬ ላሉትና ከእርስዎ በኋላ ለሚኖሩት ልጆችዎ፥ ከዚህ ላደረሰችዎ አገርዎና በየጊዜው ለሚመርጥዎ ወገን፥ በአጠቃላይም፡ ዛሬ፡ በዚህ ሹመትዎ ለሚወክሉት የኢትዮጵያ ሕዝብ ሲሉ፡ ቢያስፈልግም፡ ራስዎን መሥዋዕት አድርገው፡ በእግዚአብሔር ልጅነትዎ ኃይል፡ ይህን፡ የጎሠኛነት ጠንቅ፡ በመጀመሪያ፡ ከውስጥዎ ያስወግዱት! ከዚያ በኋላ፡ በአገር ደረጃ፡ ችግሩ የሚወገድበት መንገድ፡ አውቆ ይከተላል:: በዘመናችን፡ በአገራችን የደረሰው፡ ይህ ኹሉ ችግር የመጣው፡ በእኛው፡ ማለትም፡ በእርስዎና በእኔ እንደመኾኑ፡ የሚወገደውም፡ በእውነት ከፈለግን፡ በእኛው መኾኑን ሳበሥርልዎ ደስ ይለኛል::

እግዚአብሔር፡ ስለእኛ መልካም ሕይወትና ህልውና ያለው ፈቃድ፡ ምን ዓይነት እንደኾነ፡ ከመጀመሪያዎቹ ሰዎች፡ ከአዳምና ሔዋን አንሥቶ፡ እስከዛሬ በተነገረን ዜናና፥ በተለይም፡ ኢትዮጵያን የመሰለች፡ በተፈጥሮ ጸጋዎች የበለጸገች አገርን ለሰጠን፡ ለእኛ፡ ለኢትዮጵያውያን በተደረገልን መለኮታዊ ቸርነት አውቀነዋል:: ከዚህ፡ የቸርነት ስጦታው መካከል፡ ክፉውንና ደጉን ለይተን ከምናውቅበት፡ በመልኩ ከመፍጠሩ ቀጥሎ፡ እያንዳንዳችን በግል፥ ኹላችንም በጋራ፡ በፈለግነው መልክ እንኖር ዘንድ፡ የመምረጡን ነጻነትና የመወሰኑን ሥልጣን፡ ለእያንዳንዳችን ማጎናጸፉ ይገኛል:: ከዚህ የመምረጥ ነጻነትና የመወሰን ሥልጣን የተነሣ፡ እርስዎም፥ እኔም፡ ባመንበት አቋምና በፈለግነው ሙያ፥ በመረጥነው ሥራና በወሰነው አገልግሎት፡ ይኸው እየኖርን እንገኛለን::

እንደዚሁ ኹሉ፡ እርስዎንና እኔን የሚያጠቃልለው፡ ይህ፡ የዛሬው የኢትዮጵያ ትውልድ፡ በዚህ የመምረጥ ነጻነቱና የመወሰን ሥልጣኑ ተጠቅሞ፡ እግዚአብሔር የመሠረተለትን፥ ወላጆቹም የተሠዉለትን፥ እርሱም የተረከበውን፡ የኢትዮጵያዊነትን ውርስ፡ ለልጆቹ ለማስተላለፍ ቢስማማ፡ ይኾንለታል፥ ይሳካለታል፥ ይከናወንለታል፤ የአምላክንና የቀደሙትን ወላጆቹን ፈቃድ በመፈጸሙም፡ በረከትን ያገኛል ማለት ነው::

እርስዎ፡ ከወላጆችዎ፡ የወረሱት፡ ለዘመናት፡ እንደወርቅ፡ በመከራ እሳት ተፈትኖ፡ በጥራት የወጣውን፡ "ዐማራነት"፥ እርሱም፡ "ክርስቲያንነት"፥ እርሱም፡ "ኢትዮጵያዊነት" መኾኑን፡ ከላይ አመልክቻለሁ፡፡ እርስዎስ፡ ልጆችዎ፡ አምነው ቢቀበሉትም፥ ባይቀበሉትም፡ በዚህ ረገድ፡ ለእነርሱ የሚያወርሷቸው፡ ምን ሊኾን ነው? የማናቸውንም፡ የትውልዱን አባል፡ የወደፊት ውስብስብ ችግር ለማሳየት፡ ከልጆችዎ መካከል፡ አንዱ፡ ትንሹ የኾነውን፡ ሶምሶንን፡ በእግዚአብሔር ፈቃድ፡ በምሳሌነት አቀርበዋለሁ፤ ይህንም ሳደርግ፡ ሶምሶን፡ በአባቱም፥ በእናቱም በኩል ያሉትን፡ የአያቶቹንና የወላጆቹን አቋምና ፈለግ በመከተል፡ በእውነተኛ ኢትዮጵያዊነቱ ጸንቶ ስለሚገኝ፡ ከፈጣሪው በቀር፡ ያለሌላ መሪ፡ በራሱ ፍላጎት፥ ምርጫና ውሳኔ ብቻ፡ ችግሩን፡ ራሱ የፈትታው መኾኑን በማሳወቅ ነው፡፡

በመንፈስ ቅዱስ፡ ከእግዚአብሔር ባገኘው ልጅነቱ የተነሣ፡ በዐምሓራነት፥ በክርስቲያንነትና በኢትዮጵያዊነት ስሙ፡ "ኃይለ-ኢየሱስ" የተባለው፡ ልጅዎ ሶምሶን፡ ከላይ እንደተገለጸው፡ በእርስዎ፡ በአባቱ በኩል ብቻ ሳይኾን፡ በእናቱ፡ በወይዘሮ ሳሌምም በኩል፡ ሙሉ ዐማራ፥ ማለትም፡ ሙሉ ክርስቲያን፥ ማለትም፡ ሙሉ ኢትዮጵያዊ ነው፤ ምክንያቱም፡ ወይዘሮ ሳሌም፡ በዐምሓራነታቸው፥ በክርስቲያንነታቸውና በኢትዮጵያዊነታቸው ጸንተውና አገልግለው ካለፉት አባታቸው፡ ከአቶ ጳውሎስ መንአመኖ እና በኹለቱም ወላጆቻቸው በኩል፡ ሙሉ ዐማራ ከኾኑት፡ ከእናታቸው፡ ከወይዘሮ ጠንፌለሽ ደጀኔ በመወለዳቸው ነው፡፡ እንግዴህ፡ በማንነቱ፡ ማለትም፡ በኢትዮጵያዊነቱ፡ እንዲህ ባለ፡ የተደላደለና የማይናወጽ መሠረት ላይ የታነጸውን ልጅዎን፡ እርስዎ እንደኾኑት፡ እርሱንም፡ "እንደእኔ ኹን?" የሚሉት ከኾነ፡ እንዴት አስቸጋሪ እንደሚኾንበት፡ እስኪ፡ ችግሩን፡ ለአንዲት አፍታ እንኳ፡ በማስተዋል ይመልከቱለት!

የእናቱ አባት፡ አቶ ጳውሎስ መንአመኖ፡ የትግራይ የጎሣ ሐረግ ስላለባቸው፡ "ትግሬ ነኝ!" ብለው፡ ዛሬ፡ ኢትዮጵያንና ኢትዮጵያውያንን፡ "የትግራይ ዘር፥ የትግራይ ቋንቋ፥ የትግራይ ብሔርና የትግራይ መንግሥት" ብለው፡ ለመከፋፈል ከሚሞክሩ ጎሠኞች ጋር ይቀላቀልን? ወይስ፡ እርስዎ፡ በአባትዎ፡ የኦሮሞነት፥ በእናትዎም፡ የጉራጌነት የጎሣ ሐረግ ስላለብዎ፡ እርሱም፡ "ኦሮሞ ነኝ!" ብሎ፡ ዛሬ፡ ኢትዮጵያንና ኢትዮጵያውያንን፡ "የኦሮሞ ዘር፥ የኦሮሞ ቋንቋ፥ የኦሮሞ ብሔርና የኦሮሞ መንግሥት" ብለው፡ ለመከፋፈል ከሚሞክሩ ጎሠኞች ጋር ይቀላቀልን? ወይስ፡ "ጉራጌ ነኝ!" ብሎ፡ ዛሬ፡ ኢትዮጵያንና ኢትዮጵያውያንን፡ "የጉራጌ ዘር፥ የጉራጌ ቋንቋ፥ የጉራጌ ብሔር፥ የጉራጌ መንግሥት" ብለው፡ ለመከፋፈል ከሚሞክሩ ጎሠኞች ጋር ይቀላቀልን? ከፈጣሪው፡ በተፈጥሮ በተሰጠው፡ የመምረጥ ነጻነትና የመወሰን ሥልጣን ቢኖረውም፡ እርስዎ፡ ወደየትኛው የጎሣ ጎራ "ይወግን!" ይላሉ? እንደእርስዎ፡ ወደኦሮሞው? አለዚያ ደግሞ፡ ወደጉራጌው? ወይስ፡ ወደትግራዩ? ወደየትኛው ይላሉ? ምናልባት፡ እርስዎ፡ "የእኔ ምርጫ፡ ወደኦሮሞው ስለኾነ፡ የእርሱም፡ ይኸው ሊኾን ይገባል!" ይሉ ይኾናል፤ ነገር ግን፡ ለምን ወደጉራጌው፥ ወይም፡ ወደትግራዩ አይኾንም? መለኪያው፥ መመዘኛው ምንድር ነው? እርስዎ፡ ከ"ጉራጌነቱ" ይልቅ፡ "ኦሮሞነቱ"ን የመረጡበት፡ መለኪያዎ፥ መመዘኛዎ፡ ከቶ ምንድር ነበር? ያን ማለቴ ነው፡፡

የራስዎን ጊዜያዊ የግል ደስታና ጥቅም ብቻ ለመጠበቅ ሲሉ፡ እርስዎ ያደረጉትን የምርጫና የውሳኔ ፈለግ "ልከተል!" ካላለ በቀር፡ ልጅዎ፡ ወደየትኛው የጎሣ ጎራ እንደሚወግን፡ መርጦ ለመወሰን፡ የቱን ያህል የተወሳሰበ ችግር እንደሚገጥመው፡ ግልጽ ነው፡፡ እርስዎም፡ ይህን፡ የትውልዱን ልጆች ችግር ለመረዳት፡ የሚከብድዎ አይመስለኝም፡፡

እንግዴህ፡ ከአባቶቻችንና ከእናቶቻችን የወረስናቸውን፡ "አንዲቷን ኢትዮጵያንና አንዱን ኢትዮጵያዊነትን"፡ እኛ የዛሬዎቹ አባቶችና እናቶች፡ ለልጆቻችን እያስረከብናቸው ያለነው፡ ይህ፡ እርስዎና መሰሎችዎ ያደረጋችሁትንና እያደረጋችሁ ያላችሁትን፡ እጅግ ከባድና አዳጋች፥ ውስብስብና ጠንቀኛ ችግር የኾነውን፡ የመከፋፈልና የመለያየት ግብርን ኾኖ መገኘቱ፡ እጅግ አያሳዝንምን? እጅግስ አያሳፍርምን?

ልጅዎ፡ ወደደም፥ ጠላም፡ በዚህ፡ በግልም ኾነ፥ በቤተሰብ፥ በአገርም ደረጃ፡ የመኖር፡ ወይም፡ የመጥፋት፡ ምርጫንና ውሳኔን እንዲያደርግ ይገደዳል፤ ይህም ማለት፡ ወይ "ኢትዮጵያዊነቱን አጽንቶ ጠብቆ"፡ መልካም ህልውናን፡ በዘለዓለም ሕይወት ውስጥ የመቀጠልን፥ ወይም፡ "ኢትዮጵያዊነቱን አጥቶና ትቶ"፡ በዘለዓለም ሞት ውስጥ፡ የሥቃይ ደይንን፡ የመግፋት ምርጫንና ውሳኔን ማድረግ፡፡ አዎን! በዚህ ምርጫውና ውሳኔው፡ ወይ እንደእርስዎ መኾን፥ አለዚያ ደግሞ፡ አኹን በሚገኝበት አቋሙ ጸንቶ መቀጠል ሊኖርበት ነው፤ ይኸውም፡ "ዐምሓራነቱን፥ ክርስቲያንነቱን፥ ኢትዮጵያዊነቱን"፡ ወይ መካድ፥ ወይም፡ ማጽናት ሊኖርበት ነው፡፡ ታዲያ፡ በራሱም ሕሊና፥ በሰውና በእግዚአብሔር ዘንድ የሚያስሞግሰው፥ የሚያስከብረውና የሚያስመርቀው ምርጫና ውሳኔ የትኛው ይመስልዎታል? እርስዎ ራስዎ፡ ለዓለሙ፡ በይፋ ያሳወቁትን፡ የእርስዎ የኾነውን፡ ይህ፡ እርስዎ፡ ዛሬ የሚገኙበትን፡ የክህደት፥ የዓመፅና የአመንዝራነት አቋም? ወይስ፡ እኔ በማውቀው መጠን፡ ልጅዎ ሶምሶን፡ ዛሬ፡ ራሱ ጸንቶበት የቀጠለውን፡ የኢትዮጵያዊነት ሃይማኖት፥ የኢትዮጵያዊነት ምግባርና የኢትዮጵያዊነት ጽናት አቋም?

ለእርሱ፡ በተጻራሪው ወገን፡ እርስዎ አባቱ፡ ያደረጉት ምርጫና ውሳኔ አለ፤ በተባባሪው ወገን ደግሞ፡ እኚህ እናቱ፡ ያደረጉት ምርጫና ውሳኔ አለ፤ እርሱ፡ በመካከል ቆሞ፡ ወደኹለታችሁም ወላጆቹ፡ ፊቱን መለስ ቀለስ እያደረገ፡ ሲያማትር፡ በአንክሮና በተዘክሮ አየዋለሁ፤ ዲያብሎስን ድል የመንሣት ኃይል ያለው መንፈስ ቅዱስ፡ ሓሰትን፡ በእውነት አሸንፎ፡ ክፉው ጊዜና ጠንቁ፡ ሊለያያችሁ ያልቻለውን፥ እርስዎም፡ በመጽሓፍዎ ውስጥ፡ በሥዕል አስደግፈው እንዳቀረቡት፡ "እግዚአብሔር አንድ ያደረጋችሁን" አባቱንና እናቱን፡ የምትሓት በኾነው፡ በስምና በይስሙላ ሳይኾን፡ አማናዊ ብርሃን በኾነው፡ በእግዚአብሔር የቃል ኪዳን ጸጋ፡ በነፍስ፥ በሥጋና በመንፈስ፡ እንደገና፡ "በተዋህዶ ያገናኝለታል!" ብዬ አምናለሁ፤ እጸልያለሁም፡፡

፮ኛ፡- የእግዚአብሔር መንግሥት የኾነችውን ኢትዮጵያን፡ በታማኝነት ለማገልገል፡ በራሴ ፈቃድ፡ ቃል ኪዳን የገባሁ መኾኔን፥ ይህን ኃላፊነቴን በሚመለከትም፡ በመጽሓፍዎ ውስጥ፡ በግልጽ ተጽፈው ለቀረቡትና ከእውነት ርቀው ላገኘኋቸው ኹኔታዎች ኹሉ፡ ተገቢውን የመልስ አስተያየት እንድሰጥ መገደዴን፡ ቀደም ብዬ አስታውቄአለሁ፡፡ እርስዎም፡ አኹን ከያዙት ርእሰ ብሔርነትዎ የተነሣ፡ ለአገሪቱ ብሔራዊ አቋምና ባህል መጠበቅ፥ ለሕዝቡም መልካም ሕይወትና የሥርዓት አኗኗር መከናወን፥ በተለይም፡ "ኢትዮጵያዊ" ያሰኘዎትን የእግዚአብሔርን ልጅነት፡ በምስጢረ ጥምቀት ላገኙባት፡ የክርስቲያን ሃይማኖትዎ መከበር፡ በአርአያነትዎና በተጠሪነትዎ፡ ኃላፊነትም፥ ግዴታም እንዳለብዎ፡ አያጠያይቅም፡፡

በዚህ ረገድ፡ እኔም፡ የተመለከትኋቸውና የተገነዘብኋቸው ዓበይት ነገሮች ቢኖሩ፡ የእነዚህን ነገሮች አሳሳቢነት እያወቅሁ፡ እንዳላወቀ፥ እያየሁ፡ እንዳላየ፥ እየሰማሁ፡ እንዳልሰማ፥ እያነበብሁ፡ እንዳላነበበ ኾኜ፡ ይህን ግዳጄን ሳልፈጽም ብቀር፡ በሕሊናዬ ዘንድ ብቻ ሳይኾን፡ በሕዝብና ይልቁንም፡ በእግዚአብሔር ፊት፡ በኃላፊነት እንደምጠየቅ፡ ለእርስዎ ማስረዳት የሚያስፈልገኝ አይመስለኝም፡፡ ምናልባት፡ ይህን የመሰለውን ኃላፊነቴን፡ በሰዎች ዘንድ እንደተለመደው፡ የተለያዩ ምክንያቶችን በመደርደር ብሸሸው፡ በተለይ፡ እኔን ለመሰለ አገልጋይ፡ ከእውነተኛ ኢትዮጵያዊ ምግባር ውጪ የሚያደርግ መኾኑ፡ "ኢትዮጵያዊ ነኝ!" በሚለው ዘንድ ቀርቶ፡ በሌላውም፡ ሰብአዊ ፍጡር ዘንድ፡ በይፋ እንደሚታወቅ እገምታለሁ፡፡ ስለዚህ፡ በዚህ መልክ፡ ከዚህ በላይ የሠነዘርሁትና አከታትዬ የምሠነዝረው አሳብ፥ ወይም፡ አስተያየት ኹሉ፡ በአዎንታዊ ባሕርዩ እየታየ፡ በክቡርነትዎ ፊት፡ ተቀባይነትን ያገኝልኝ ዘንድ፡ አስቀድሜ እማፀናለሁ፡፡

ምንነቱን፡ ከላይ ባጭሩ በገለጽሁት ሥርዓተ መንግሥታችን መሠረት፡ ኢትዮጵያዊነት የሚጀምረው ከራስ ነው፤ እንኳንስ፡ እርስዎ፡ አኹን ካሉበት የርእሰ ብሔርነት ቦታዎ የተነሣ፡ የዛሬዪቷን ኢትዮጵያ፥ ከመላው ሕዝቧና መንግሥቷ ጋር፡ በአገር ብቻ ሳይኾን፡ በዓለምም ደረጃ የሚወክሉት፡ ታላቁ ባለማዕርግ ይቅሩና፡ እኔ አንዱ፡ ተራውና ምስኪኑ ሰው እንኳ፡ በእውነተኛው ኹለንተናዬ፡ ራሴ፡ "ኢትዮጵያ" ነኝ! አዎን! "ኢትዮጵያ" ማነው? "ኢትዮጵያ"ማ፡ ፀሓዩቱና አየሩ፥ ውኃውና ምድሪቱ፡ ከአዝርዕቱ፥ ከአትክልቱና ከዕፀዋቱ፥ ደግሞም፡ ከእንስሳቱና ከአራዊቱ፥ ከአዕዋፋቱና ከዓሣቱ ጋር፡ በጠቅላላው፡ ፍጥረተ-ዓለሙ፡ ከመጀመሪያው፡ በፈጣሪው ተዘጋጅቶ የተሰጠውና በእግዚአብሔር መልክ የተፈጠረው፥ በመጨረሻም፡ ባላጋራው ዲያብሎስ፡ ባመጣበት ጠንቅ ምክንያት፡ ከዚያ መልካም ሕይወት ወጥቶ፡ ወደክፋት ባርነት፥ ወደኃጢኣት ቀንበርና ወደሞት ፍዳ ቢወድቅ፡ ራሱ፡ እግዚአብሔር ቤዛ ኾኖት ያዳነው፡ እያንዳንዱ ሰው ነው፤ እርሱ ነው፡ "ኢትዮጵያ"፡፡ እርሱም፡ ወንዱ፡ "ኢትዮጵያዊ"፥ እርሷ፡ ሴቷ፡ "ኢትዮጵያዊት" ይባላሉ፡፡

ይህ "ኢትዮጵያዊ"፥ ይህች "ኢትዮጵያዊት"፡ በዚህ ኢትዮጵያዊነታቸው፡ ፍጹም የኾነውን ሰብአዊ ክብርና መብት፡ ከሌላ ፍጡር ሳይኾን፡ በቀጥታ፡ ከፈጣሪያቸው የተቀዳጁ እንደመኾናቸው መጠን፡ ለዚህ ክብርና መብት በቅተው ይገኙ ዘንድ፡ ሊፈጽሙት የሚገባቸው ግዳጅ ደግሞ አለ፡፡ ታዲያ! እርስዎ፡ ይህን ግዳጅ ፈጽመዋልወይ? በሥርዓተ መንግሥታችን መሠረት፡ ከላይ፡ ቀደም ብዬ በገለጽሁት፡ "መክብበ ማርያም" በተባሉበት፡ "ኢትዮጵያዊ ምእመንነትዎ" ምክንያት፡ ይህ ጥያቄ፡ ሊቀርብልዎ ይገባ የነበረው፡ በቤተ ክህነቱ ተጠሪዎች በኩል ሲኾን፡ እርስዎ፡ አኹን ከሚገኙበት ማዕርግዎ የተነሣ፡ በመምህረ ንስሓዎ አማካይነት፡ በቀጥታ፡ በብፁዕ እጨጌ ጳውሎስ ነበር፡፡ ነገር ግን፡ እርስዎ ብቻ ሳይኾኑ፥ መምህረ ንስሓዎና እጨጌ ጳውሎስ ጭምር፡ በዚህ ረገድ ያለውን፡ የየግላችሁን ግዳጅ፡ ኹላችሁም አለመፈጸማችሁን ያረጋገጥሁት፡ በአንድ በኩል፡ እውነቱን፡ በቅርብ በማውቀው መጠን፡ እርስዎ፡ የጋብቻ ኑሮዎን በሚመለከት፡ እያካኼዱት ያሉት የተዛባ ኹኔታ፡ በንስሓ እንዲስተካከልና እንዲታደስ በማድረግ ፈንታ፡ እየቀጠለ በመኼዱ፥ በሌላ በኩል ደግሞ፡ መምህረ ንስሓዎና እጨጌ ጳውሎስ፡ ይህን ጥያቄ አቅርበውልዎት፡ እርስዎ፡ በዚህ የይቅርታ ጸጋ ለመጠቀም ፈቃደኛ ኾነው ካልተገኙ፡ መምህረ ንስሓዎም ኾኑ፡ እጨጌው፡ ከኢየሱስ ክርስቶስ፡ በቃል ኪዳን የተቀበሉትን የክህነት ሥልጣን፡ በእርግጥ፡ በታማኝነት ጠብቀውት የሚገኙ ከኾነ፡ በዚሁ ሥልጣናቸው፡ ሊያወግዙዎ ሲገባቸው፡ ይህን ተግባራቸውን ሳይፈጽሙ በመቅረታቸው ነው፡፡

ክብርት ባለቤትዎ፡ ወይዘሮ ሳሌም ጳውሎስ፡ እንደልጃችሁ ሶምሶን፡ በእኔ የተልእኮ አገልግሎት ውስጥ ተሳታፊ ኾነው፡ እንደሥርዓተ መንግሥታችን መመሪያ፡ የቅዱሱ ኪዳን ኢትዮጵያዊነታቸውን፥ ከዚህም የተነሣ፡ የጋብቻ ሕይወታቸውን፡ በንስሓና በቅዱስ ቍርባን፡ ጠብቀው፥ አክብረውና አጽንተው ስለሚኖሩ፡ ማንነታቸውንና ምንነታቸውን፡ ደህና አድርጌ አውቀዋለሁ፤ እመሰክርላቸውማለሁ፡፡ እርስዎም፡ ይህን የእርሳቸውን ፈለግ ተከትለው በመፈጸም፡ እንደእኔ እምነት፡ "ለዚህ የክብር ደረጃ ያበቃዎት እግዚአብሔር፡ ከእርስዎ የሚጠብቀውን፡ የሃይማኖትና የምግባር ፍሬ የኾነውን፡ የንስሓ በረከትን ያቀርቡለታል!" ብዬ፡ ከግል ሙከራዬ ጋር፡ ለአያሌ ዓመታት ብጠብቅ፥ እስካኹን፡ ምንም ዓይነት ውጤትን ስላላገኘሁ፡ ለዚህ የጋብቻና የቤተሰብ ችግር፡ እውነተኛውን መፍትሔ ይሰጥ ዘንድ፡ የእግዚአብሔርን ረድኤት በመሻት፡ እየጸለይሁ ሣለሁ፡ "ድሮና ዘንድሮ" የሚለው መጽሓፍዎ ደረሰኝ! እርሱም፡ ይህን ግልጽ ደብዳቤ እንድጽፍልዎ፡ ከአምላክ የተላከ፡ አስገዳጅ ምክንያት ኾነኝ፡፡ እኔም፡ ተልእኮዬ በመኾኑ፡ ይህንኑ ግዳጅ ተቀብዬ፡ እስካኹን ያሰማሁዎትን የእግዚአብሔርን መልእክት፡ በዚህም መልኩ፡ እያብራራሁ፡ እንደሚከተለው አቀርብልዎታለሁ፡-

እኛ ኢትዮጵያውያን፡ ከእግዚአብሔር ከተቀበልናቸው፡ ከሰባቱ ቅዱሳት ኪዳናት መካከል፡ ዋናው፥ የመጀመሪያውና መሠረታዊው ቃል ኪዳን፡ “ጋብቻ” መኾኑን፡ ኢትዮጵያዊው ሥርዓተ መንግሥታችን፡ አበክሮ ይናገራል። ከዚህ የተነሣ፡ በመለኮታዊው ሕግ ብቻ ሳይኾን፡ በምድር ላይ ተበትነው በሚኖሩ ሕዝቦች መካከል፡ በአዋጅ ጸንተው በሚሠሩ፡ ሰብአውያን ሕጎች ጭምር፡ ከፍተኛ ማዕርግ ተሰጥቶት፥ ልዩ የክብር አስተያየትም ተደርጎለት፡ በጥንቃቄ ሲጠበቅ እንመለከታለን። ስለዚህ፡ “ጋብቻ”፡ በባልና በሚስት መካከል፥ በኅብረተሰቡም ዘንድ፡ እጅግ ሊከበርና በታማኝነት ሊጠበቅ የተገባ መኾኑ አያከራክርም።

እኔ በተገኘሁበት፡ በዚህ፡ በዘመናችን የኢትዮጵያ ትውልድ ዘንድ ግን፡ ሳየው የኖርሁትና ዛሬም እያየሁ ያለሁት፡ “ጋብቻ”፡ ሲቃለልና ሲዘበትበት፥ ሲናቅና ሲቀለድበት፥ ሲነቀፍና ሲዋረድ፥ በመጨረሻም፡ ሲረክስ ነው። በኢትዮጵያዊው ጋብቻ ላይ እየተፈጸመ ያለው፡ ይህን የመሰለው ጥቃትና በደል፡ ሴቶች፥ ወይም፡ ሚስቶች፡ በወንዶች፥ ወይም፡ በባሎች ላይ ከሚፈጽሙት ይልቅ፡ ወንዶች፥ ወይም፡ ባሎች፡ በሴቶች፥ ወይም፡ በሚስቶች ላይ በሚፈጽሙት አሠቃቂ ግፍ፡ ጎልቶና በዝቶ ይታያል። እግዚአብሔር፡ የሠራውና የመሠረተው የዚህ ሥርዓት እንዲህ መቃለልና መናቅ፥ መቀለጃና መዘበቻ መኾን፥ መነቀፍና መዋረድ፥ በመጨረሻም፡ መርከስ ማለት ደግሞ፡ ምን ማለት ነው? ይህ፡ ትውልድ፡ ይህን ጥቃትና በደል፡ በሥርዓቱ ላይ ብቻ ሳይኾን፡ የሥርዓቱ ሠሪና ባለቤት በኾነው፡ በራሱ በእግዚአብሔር ላይ ጭምር፡ በቀጥታ ፈጽሚል ማለት አይደለምን? ከዚህ የተነሣስ፡ እግዚአብሔርንና ሥራዎቹን፥ ሥርዓቶቹንም ኹሉ፡ በራሱ በትውልዱ ዘንድ ብቻ ሳይኾን፡ በዓለም ሕዝቦች፥ በአረማውያን ዘንድ ሳይቀር፡ መሳቂያና መሣለቂያ ማድረግ አይደለምን? ኢትዮጵያዊው ጋብቻ፡ ይህ ጕሥቍልና እየደረሰበት፥ በደሉም እየተፈጸመበት ያለው፡ በቤተ ሕዝቡና በቤተ ምልክናው አባሎች ዘንድ ብቻ ሳይኾን፡ የሥርዓቱ ባለአደራ ጠባቂና አስከባሪ ዘርፍ በኾነችው፡ በቤተ ክህነቱም አባሎች ዘንድ በመኾኑ፡ እጅግ ያሳዝናል፤ ያሳስባልም። ለዚህ የጋብቻ ኹኔታችን እውነታ፡ ማረጋገጫ የሚኾን ማስረጃን ለመፈለግ፡ ሩቅ መኼድ የለብንም፤ በአኹኑ ጊዜ፡ ይኸው ትውልድ፡ ለአንድ አገር ህልውና፡ መሠረቱና ግድግዳው፥ ጣሪያውም በኾነው፡ በጋብቻ ሥርዓቱ ላይ በፈጸመው፡ በዚህ ደባው ምክንያት፡ እየከፈለ ያለውን የእጁን ዋጋ፡ ዓለም ኹሉ፡ እነሆ፡ በገሃድ እያየው ነው።

በማንኛቸውም የዓለም ሃይማኖታውያን አገሮች ዜጎች፥ በአዳዲሶቹ የሃይማኖት ተቋሞች አማኞችና አባሎች ዘንድ ሳይቀር፡ “ጋብቻ”፡ በተቀደሰ ሥርዓት ተከብሮ እንዲጠበቅ ሲደረግ፡ ለሰባት ሺህ፡ አራት መቶ ዘጠና ሰባት ዓመታት፡ ኪዳነ ልቦናን፥ ኪዳነ ኦሪትንና ኪዳነ ምሕረትን፡ እንደሰንሰለት አያይዞ ባስገኘው፡ በእግዚአብሔር ሕገ መንግሥታዊ አምልኮት እየተመራች በኖረችው ኢትዮጵያና ኢትዮጵያውያን ዘንድ፡ “ጋብቻ”፡ በዚህ በዛሬው ዘመን፡ በእንደዚህ ያለ ኹኔታ ላይ መገኘቱ እጅግ ያሳፍራል። እንደድቅድቅ ጨለማ፡ ገበና-ከታች በኾነው አስፈሪ ዝምታችን፡ በብረት ዛንጅር ጠርቀን፥ ዘግተንበትና ደብቀነው የኖርነውን፡ ሌላውን ኹሉ በሽታችንን፡ ለጊዜው ወደጎን ልተወው ሣልል፡ “ኢትዮጵያዊው፡ በማንነቱ ፍለጋ!” እና “ኢትዮጵያ፡ የዓለሙ መፋረጃ!”፥ እንዲሁም፡ “ኢትዮጵያና እና ኢትዮጵያዊነት” በተባሉት መጻሕፍቴ ቊልፍ ብርሃንነት፡ ከፋፍቼና ገላልጬ፡ ከነመፈወሻው መድኃኒቱ ስላቀረብሁ፡ ያን ሰፊ ሓተታ፡ ለእነዚያ መጻሕፍቴ ትቼ፡ እስኪ፡ በዚሁ፡ በተነሣንበት፡ በ“ጋብቻ” ርእስ ላይ ብቻ አተኵረን እንነጋገር!

ይህ፡ የዛሬው የኢትዮጵያ ትውልድ፡ በዚህ ረገድ፡ በኢትዮጵያዊው የጋብቻ አኗኗር ሥርዓት ላይ፡ በይፋ ሲያካኺድ ለሚታየው አሳፋሪ ግብር፡ ዛሬ የኢትዮጵያን ሕዝብ ትውልድ ከሚወክሉት፡ ከእርስዎ የበለጠ አብነትና የተሻለ ማስረጃ የሚኾነኝ፡ ሌላ ኢትዮጵያዊ አላገኘምና፡ በመጽሓፍዎ ውስጥ፡ በሥዕሎች እያስደገፉ ያሠፈሩዋቸውን፡ “ሙሽራዬ!” እና “እግዚአብሔር አንድ ያደረገውን፡ ሰው አይለየውም!” የሚሉትን ቃላት፡ መነሻ በማድረግ፡ የታዘዝሁትን መልእክት፡ ለእርስዎ፥ በእርስዎም አማካይነት፡ ለዚሁ፡ ለኢትዮጵያ ሕዝብ ትውልድ አቀርባለሁ።

ይህን ግዳጄን የምፈጽመውም፡ በአንድ በኩል፡ እነዚሁ የፍቅርና የቅዱሳት መጻሕፍት ቃላት፡ እኔ፡ በእውን ከማውቀውና ከዚህ በታች በሚነበበው ጥቅስ እንደሚታየው፥ የኢትዮጵያ ሕዝብ፡ በይፋ ከሚያውቀው፥ እርስዎም፡ አኹን ከሚገኙበት አቋምዎ ጋር የማይጣጣሙ ኾነው ስላገኘኋቸው፡ በሃይማኖት ብርሃን ተገላልጠው ሊታዩና በምግባር መሣሪያ ተቃንተው ሊስተካከሉ እንደሚገባ በማሳየት ይኾናል፤ በሌላው በኩል ደግሞ፡ በእርስዎና በባለቤትዎ መካከል ያለው፡ ይኸው ጋብቻ፡ ተጠብቆ ሊቀጥል የቻለው፡ በቃል ኪዳኑ የታመነው እግዚአብሔርና ፈቃዱን እየፈጸሙ የሚኖሩት ባለቤትዎ፡ የየበኩላቸውን ድርሻ አጽንተው በመገኘታቸው መኾኑን፡ ለራሴ ተገንዝቤ፡ ለእርስዎና ለሌላውም ለማስገንዘብ ነው፡፡

ጋብቻዎንና የቤተሰብ አኗኗርዎን በሚመለከት፡ የኢትዮጵያ ሕዝብ፡ በይፋ የሚያውቅ ለመኾኑ፡ በቃልና በእስትንፋስ፥ ወይም፡ በምሥጢርና በጨለማ ከሚናኘው በቀር፡ በብዙኃን መገናኛዎች ጭምር፡ በይፋ ከተነገረውና ከተጻፈው፥ ከበርካታው ስብስብ መካከል፡ አንዱን፡ በቅርቡ ያነበብሁትን፡ ቅንጫቢ፡ እንደሚከተለው፡ ለዓይነት ያህል አቅርቤዋለሁ፤ ይኸውም፡ በአንድ ጦማረ ሕዝብ፥ ወይም መጽሔት ላይ፡ “የአንድ ቀን ሥልጣን ቢኖረኝ!” በሚል ርእስ፡ “ከሰይፈ” ከተጻፈ አጭር ትችት የተገኘ ነው፤ ቃሉም፡ እንዲህ ይላል፡–

*“ከዚህ ቀደም ያነሣሁትን ጥያቄ፡ በዚህ አጋጣሚ፡ ደግሜ አነሣለሁ፤ 'ቀዳማዊት እመቤት' የምትባለው፡ የርእሰ ብሔሩ ባለቤት? ወይንስ፡ የርእሰ መንግሥቱ? ምናልባት፡ 'መቶ አለቃ ግርማ፡ ሚስት የላቸውም!' ተብሎ፡ ኹሉ ነገር፡ በዘፈቀደ መከወን አለበትን? በዕድሜ የገፉ አዛውንት፡ በፕሬዚዳንትነት መሾማቸው፡ ምናልባት፡ የቀዳማዊት እመቤትነቱ ጥያቄ እንዳይነሣ ይኾን? …እኔ፡ የአንድ ቀን ሥልጣን ቢኖረኝ፡ ወ/ሮ አዜብ፡ እንደባለቤታቸው፡ በጕልበት፡ 'ቀዳማይ እመቤት' እየተባሉ መጠራታቸውን፥ ይህም፡ ሕገወጥ መኾኑን፡ በሜዲያ ለ24 ሰዓታት አስነግራለሁ፡፡”*

ጥንታዊ የኾነ፡ የራሳችን ቋንቋና ሥርዓተ መንግሥት ያለን፡ እኛ ኢትዮጵያውያን፡ “አጼ”፥ ወይም፡ “ርእሰ ብሔር” እና “እቴጌ”፥ ወይም፡ “ርእስተ ወይዛዝር” በማለት ፋንታ፥ ይልቁንም፡ “እመቤታችን!” የምንላት፡ ብሔራዊት እናታችንና አገራችን የኾነችውን፡ ቅድስት ድንግል ማርያም ብቻ መኾኑ እየታወቀ፡ የባዕዳንን ሥርዓት ተውሰን ለመተካት በተነደፈው ዕቅድ መሠረት፡ “President”, “First Lady” ማለታችን፥ ለ፳፬ ሰዓታት ብለን፡ በራሳችን አኀዛት መጻፍ ሲገባንም፡ 24 ብለን፡ በባዕዳኑ ቍጥሮች መጻፋችን፡ አግባብ አለመኾኑን፡ እዚህ ላይ እንድጠቍም ይፍቀዱልኝ!

ክቡር ርእሰ ብሔር!

እርስዎና እኔ፡ በ፲፱፻፶፪ ዓ.ም.፡ በሥራ ከተገናኘን በኋላ፡ ቤተሰቦቻችን ተቀራርበው፡ መልካም ጊዜን እንዳሳለፍን ትዝ ይለኛል፡፡ በደርግ፡ የጦር ኃይል በተካኼደው ብሔራዊ የሥርዓት ለውጥ ምክንያት፡ እኔ፡ “የአገዛዙ ተቃዋሚ!” ተብዬ፥ በታጠቁ፡ የጦር ወታደሮች ተከብቤና ተይዤ፡ ወደእሥር ቤት በመግባቴ፡ ይኸው ግንኙነታችን ተቋርጦ፡ ለብዙ ዓመታት፡ በዚሁ ኹኔታ ቆየ፡፡ ግንኙነታችን፡ በቤተሰብ ደረጃ ሊቀጥል የቻለው፡ ባለቤቴ ወይዘሮ ራሔል ዘካርያስና እኔ፡ ከደርግ እሥር ተፈትተንና አገር ለቅቀን፡ የስደት ኑሮን በቀጠልንበት፡ በአሜሪካ፡ ባለቤትዎ፡ ወይዘሮ ሳሌም ጳውሎስና ልጅዎ፡ ሶምሶን ግርማ፡ “ኢትዮጵያ፡ የእግዚአብሔር መንግሥት አገልግሎት” በሚለው፡ እኔ በምገኝበት ተልእኮ ውስጥ ለመሳተፍ፡ በፈቃዳቸው በመምጣታቸው ነበር፡፡ እርስዎም፡ ለርእሰ ብሔርነቱ ሹመት ከመብቃትዎ በፊት፡ ባለቤትዎና ኹለት ልጆችዎ ወደሚገኙበት፡ ወደአሜሪካ መጥተው በነበረ ጊዜ፡ በቤተ ክርስቲያን ተገኝተው በተመለከቱት፡ እኒሁ ባለቤትዎና ይኸው ልጅዎ፡ እርሱ በክህነት ጭምር፥ እርሳቸው፡ በቅዱስ ቍርባን ተሳትፎ፥ ኹለቱም፡ በማኅበራዊ አገልግሎት፡ ከእኛ ጋር ያላቸውን አንድነት ለማወቅ ችለዋል፡፡

ያ አጋጣሚ ጊዜና ኹኔታ፡ እጅግ አመቺ ስለነበር፡ ራሳቸውን ለንስሓና ለቅዱስ ቊርባን አብቅተው፡ በእውነተኞዪቱ የእግዚአብሔር መንግሥት ውስጥ፡ ኢትዮጵያዊዉን ሕይወት እንደሚኖሩት፡ እንደባለቤትዎ፡ “እርስዎም፡ በእኔ አማካይነት የሰሙትን፡ የእግዚአብሔርን የግብዣ ጥሪ በመቀበልና ራስዎን፡ በንስሓ አንጽተው፡ ከቀረበልዎት፡ ከዚያ የዘለዓለም ሕይወት ገበታ፡ ቅዱስ ቊርባኑን በመሳተፍ፡ ከባለቤትዎ ጋር ያለዎትን የተቀደሰውን የጋብቻ አንድነት አድሰውና አጽድቀው ያጸኑታል!” ብዬ፡ በዚያን ጊዜ ተመኝቼ ነበር፤ ነገር ግን፡ ያም፡ ሳይኾን ቀረ! ከዚያን ጊዜ ጀምሮ፡ ይህን ሃይማኖታዊ ምግባር፡ “አንድ ቀን ይፈጽሙታል!” ብዬ፡ ተስፋ አድርጌ ብቆይም፡ በእርስዎ በኩል፡ ምንም ዓይነት የፈቃደኝነት ጭላንጭልን እንኳ ማየት ሳልችል፡ የስደት ተልእኮዬን ስለጨረስሁ፡ እኔ፡ ከነቤተሰቤ፡ ወደአገሬ፡ ወደኢትዮጵያ ተመለስሁ:: የተመለስሁትም፡ ለእግዚአብሔርና ለራሳቸው ብቻ ሳይኾን፡ ለእርስዎ ጭምር፡ ታማኞች የኾኑትን፡ ባለቤትዎንና ልጅዎን፡ ዓቅሜ እስከፈቀደ ድረስ፡ እነርሱ ወደሚኖሩበት፡ ወደአሜሪካ አገር እየተመላለስሁ እንደማገለግላቸው ቃል ገብቼላቸው ነበር:: ዛሬ፡ ይህን ደብዳቤ፡ ከአሜሪካ ልጽፍልዎ የበቃሁት፡ በዚያ ቃሌ መሠረት፡ ለዚሁ አገልግሎት፡ በአጠገባቸው በመገኘቴ መኾኑን ላሳውቅዎ እወድዳለሁ::

እንዳጋጣሚ፡ እኔ፡ ከላይ በገለጽሁት መልክ፡ በመጀመሪያ፡ ወደአገሬ ተመልሼ፡ አዲስ አበባ ባለሁበት ጊዜ፡ እርስዎ፡ ለኢትዮጵያ፡ ርእሰ-ብሔርነት ተመርጠውና ተሾመው፡ በብሔራዊ ቤተ መንግሥት ሣሉ፡ ልጅዎ፡ መምህርት መና ግርማ፡ ልትጠይቅዎ፡ ከአሜሪካ ስለመጣች፡ በእርሷ አማካይነት፡ ከእርስዎ ጋር በስልክ ተገናኝተን ለመነጋገር፥ ለቤተሰባዊ ግብዣም፡ ባለቤቴንና እኔን፥ ከልጆቻችን ጋር፡ ወደቤተ መንግሥት ጠርተውን፡ እንደገና፡ በዓይነ ሥጋ ለመተያየት ችለናል:: በእነዚያ ግንኙነቶቻችን ጊዜ፡ በስልክና በአንደበት ከተለዋወጥናቸው ቃላት መካከል፡ በእኔ በኩል፡ ለፍሬያማነታቸው እጅግ ጓጉቼና ተማምኜ፡ እየመላለስሁ የተናገርኋቸውን፡ ዋናዎቹን፡ ምንጊዜም የምዘነጋቸው አይደሉም፤ እነርሱም፡ *“ምንተኑ አዐስዮ ለእግዚአብሔር፡ በእንተ ኵሉ ዘገብረ ሊተ!”* ይህም ማለት፡ “ይህን ኹሉ ሳደረገልኝ፡ ለእግዚአብሔር፡ የምከፍለው ዋጋ፡ ከቶ ምንድር ነው?” የሚለውን፡ የአመስጋኙን ነቢይ ቃል በማዘከር፡ “ሕይወትዎንና ጤንነትዎን፡ ከባለቤትዎና ከልጆችዎ ጋር ጠብቆ፡ ለዚህ ታላቅ ክብርና ማዕርግ ላበቃዎ እግዚአብሔር፡ የሚመልሱት ውለታ፡ እንግዴህ ምንድር ነው?” የሚሉት ናቸው:: ስልክ ደውለው ያነጋገሩኝና ወደቤተ መንግሥት የጋበዙኝ፡ ይህን፡ ውለታዎን ሊፈጽሙ እንደነበረ፡ ከማመን በቀር፡ ሌላ ግምት፡ ጨርሶ፡ በሕሊናዬ ውስጥ አልነበረም:: መጻሕፍቴን አግኝተው፡ እያነበቧቸው መኾንዎን በገለጹልኝ ጊዜማ፡ ያ እምነቴ፡ በበለጠ ተጠናከረ!

ነገር ግን፡ ቀደም ብለው፡ ባለቤቴንና እኔን በስልክ ሲያነጋግሩንና ወደቤተ መንግሥት ሲጋብዙን፡ ለዚያ፡ እግዚአብሔር ሳደረገልዎ ቸርነት፡ እርስዎ፡ ለእርሱ፡ ስለሚመልሱት ውለታ ሊያማክሩን መስሎን የነበረው፡ ያ ጉጉት፥ ያ ግምት፥ ያ እምነት ኹሉ፡ ከዚያ የቤተ መንግሥት ግብዣ ፍጻሜ በኋላ ተንኰታኰተ! ይህን ኹሉ ቸርነት ሳደረገልዎ ፈጣሪ፡ “ይመልሳሉ!” ብለን የጠበቅነውም ያ ውለታ፡ ራስዎን በንስሓ፡ ለሥጋ ወደሙ አብቅተው፡ በዚሁ፡ የንጽሕናና የቅድስና ሕይወት ከሚኖሩት ባለቤትዎ ጋር ያለዎትን የጋብቻ አንድነት፡ በእውነተኛው ኢትዮጵያዊነት ሃይማኖትና ምግባር ማጽናትን ነበረ:: ይህን ጉዳይ፡ በሃይማኖታዊውና በክህነታዊው፥ በመንፈሳዊውና በማኅበራዊው መልኩ፡ አይቶና አመዛዝኖ፥ ተወያይቶና ተመካክሮ፡ ለመልካም ፍሬ ለማብቃት፡ በዚያን ጊዜ፡ ለእርስዎና ለባለቤትዎ፡ ከእኛ የቀረበ፡ ሌላ የቅርብ ወዳጅ ያለ አልመሰለንም ነበር፤ ወደቤተ መንግሥቱም እንድንመጣ የፈለጉን፡ ለዚሁ ዓላማ ነው ብለን አምነን ነበር:: ከዚህ የተነሣ፡ በዚያን፡ የቤተ መንግሥቱ የቤተሰብ ግብዣ ላይ፡ እርስዎ፡ “ይህን ቁም ነገሩን ያነሡልናል!” ብለን ብንጠብቅ፡ ሳያነሡብን ቀሩ፤ እርስዎ ሊያነሡት እንዳልፈለጉ እንደተረዳንም፡ እኛ ብናነሣብዎ፡ የተሰጠን መልስ፡ ፈጽመን ያልጠበቅነው ኾኖ አገኘነው::

ይልቁንም፡ ዛሬ፡ ለዚህ ታላቅ ክብርና ማዕርግ ከበቁ በኋላ፡ በተለይ፡ <u>በዚህ ዕድሜዎና የጤንነት ኹኔታዎ፡</u> ይህን፡ የእግዚአብሔርን ውለታ ለመክፈል፡ የሚያመችዎና የሚቀልዎ እንዲ፤ በማመንታት፡ እንዲህ፡ "ወደኋላ ይላሉ!" ብለን ጨርሰን ስላልጠረጠርን፡ "ተደስተን እንመለሳለን!" ያልን ሰዎች፡ ያ ቀርቶ፡ ከቤተ መንግሥቱ ግብዣ፡ እየተከዝን ተመለስን፡፡

ለባለቤትዎና ለልጅዎ፥ ለሌሎቹም መሰሎቻችን በሰጠሁት ቃል መሠረት፡ በቅዱሱ ኪዳን ኢትዮጵያዊነት ተልእኮዬ፡ የተለመደ አገልግሎቴን ላበረክታቸው፡ እንደገና ወደአሜሪካ ኼጄ፡ በዚያ ሣለሁ፡ እርስዎ፡ በቅርቡ፡ የአገሩ መንግሥት፡ የይፋ እንግዳ ሳይኾኑ፡ በግል ድርጅት ግብዣ፡ ወደዋሽንግተን ዲሲ ከተማ ለመምጣት በቁ! እግዚአብሔር፡ በእያግጣጫው የቀረበለትን፡ የኹላችንን ጸሎት ሰምቶ፡ በቸርነቱና በጥበቡ፡ ይህን ጉብኝትዎን ምክንያት በማድረግ፡ እናንተን፡ ባልና ሚስቱን፡ በአንድ ቦታ ለማገናኘት በመቻሉ፡ እጅግ ደስ ብሎን፡ አመሰገንነው፤ እንግዴህ፡ "የኢትዮጵያ አምላክ፡ መልካሚ ባለቤትዎ አሉበት ድረስ፡ በሕይወትና በጤንነት ካመጣዎ፡ እግዚአብሔር፡ እንደቃል ኪዳኑ፡ አንድ አድርጎ እስካኹን የጠበቀውን፥ ባለቤትዎም፡ በቃል ኪዳናቸው አጽንተው፡ በኢትዮጵያዊ ቅድስናው ያቆዩትን ጋብቻና ትዳር፡ እርስዎም፡ ለባለቤትዎና ለፈጣሪዎ በገቡት ቃል ኪዳን መሠረት፡ ራስዎን፡ በንስሓ አድሰው ይጠብቁታል፤ ይህንኑ፡ እርስዎም፡ በመጽሓፍዎም ውስጥ፡ በኹለታችሁ የአንድነት ብርሃናዊ ሥዕል አጠናክረው ያረጋገጡትን፡ "እግዚአብሔር፡ አንድ ያደረገውን፡ ሰው አይለየው" የተባለውን አንድነታችሁን፡ አኹን፡ እርስዎ፡ በዋሽንግተን ከተማ ቆይታ ባደረጉበት ሰሞን፡ ኹለታችሁም ተነጋግራችሁና ተስማምታችሁ፡ የእኔም የክህነት አገልግሎት ቢያስፈልግ፡ እዚሁ፡ በቅርብ ስላለሁ፡ በቅዱስ ቊርባን ካጸናችሁት በኋላ፡ እንደኢትዮጵያዊው ባህላችን፡ አብራችሁ መኖሩን ትቀጥላላችሁ!" ብዬ ስጠባብቅ፡ ይህ ሳይኾን፡ ወደአገር ቤት፡ ወደኢትዮጵያ መመለስዎን ሰማሁ፡፡ ለዚህ መልእክት መነሻ የኾነኝ፡ "ድሮና ዘንድሮ" የሚለው መጽሓፍዎም የደረሰኝ፡ ከዚያ በኋላ ነበር፡፡

፯ኛ፡- ኢትዮጵያንና ኢትዮጵያውያንን የመሰለ፡ ሃይማኖታዊ አቋምና ጥንታዊ ትውፊት ያለው፡ አንድ አገርና ሕዝብ፡ እንደዛሬው ባለ፡ ከባድ ፈተና ላይ በሚወድቅበት ጊዜ፡ ያን ችግር ተቋቊሞ፡ ከዚያ መከራ፡ በድል አድራጊነት ሊወጣ የሚችለው፡ አንድ ቆራጥ መሪን ሲያገኝ መኾኑ፡ ባለፉት ዜና መዋዕሎችም ተረጋግጧል፡፡

ታዲያ! በአኹኑ ጊዜ፡ ኃያሉና ቸሩ፡ የኢትዮጵያ የቃል ኪዳን አምላክ፡ ለዛሬዪቱ ኢትዮጵያና ሕዝቧ፡ እርስዎን፡ ርእሰ ብሔር፥ ሌሎቹንም፡ መሰሎችዎን፡ ለየቤቱ ተጠሪዎች ትኾኑ ዘንድ የመደባችሁ፡ ያለምክንያት አይደለም፤ በቂ ምክንያት እንዳለው አይጠረጠርም፡፡ እንዲህ ከኾነ፡ ቀዳሚ የኾነውን፡ የጋብቻና የቤተሰብ ኑሮዎን በሚመለከት፡ እግዚአብሔር ላደረገልዎ ቸርነቱ ከሚከፍሉት፥ ከላይ ከገለጽሁት፡ የመጀመሪያ ውለታዎ ጋር የሚያበረክቱለት፡ ሌላ ኹለተኛ ውለታ ያለ አይመስልዎትም? ይህን ኹለተኛ ውለታ፡ እንደመጀመሪያው ኹሉ፡ አኹንም፡ እኔ እንድገልጽልዎ ይፍቀዱልኝ!

ለእርስዎና ለባለቤትዎ፥ ለየቤቱ ተጠሪዎችና ለኢትዮጵያ ሕዝብ፡ በግልጽ የማስታውቀው፡ በእኔ በኩል፡ የሚሰማኝ መንፈሳዊ ተምኔትና የሚታየኝ ሃይማኖታዊ ራእይ፡ ከዚህ የሚከተለው ነው፡- "ያለዕዳውና ያለፍርዱ፡ ለፍጥረተ-ዓለሙ ቤዛ ኾኖ፡ በተቀበለው ጽኑ ፈተና፥ ባፈሰሰው ንጹሕ ደሙና በተሸከመው የመስቀል መከራ፡ እርስዎንና እኔን፥ ሌላውንም ሰብአዊ ፍጡሩን፡ ከሰይጣን ገዢነት፥ ከኃጢኣት ቀንበርና ከሞት ፍዳ፡ ነጻ ያወጣ አባትዎ ኢየሱስ ክርስቶስና፡ 'መክብበ ማርያም' አሰኝታ፡ ለእግዚአብሔር ልጅነት ያበቃችዎት፡ እናትዎ ቅድስት ድንግል ማርያም፡ የዛሬዪቱ ኢትዮጵያ ርእሰ ብሔር የኾኑበትን፡ ይህን የቸርነት ሥራና ጥሪ፡ በተለይ ለእርስዎ ያደረጉልዎ፡ ከፍተኛውን ክብርና ማዕርግ ሊያቀዳጁዎ ብቻ ሳይኾን፡ ምናልባት፡ መሥዋዕትነትን የሚጠይቀውን፡ ታላቁን ኃላፊነትና ግዳጅም እንዲፈጽሙላቸው ዐቅደው ይኾናል!

...፳፭

ክቡር ርእሰ ብሔር!

መቼም፡ በእግዚአብሔር ፊት፡ ከኃጢኣት ንጹሕ የሚኾን ፍጡር የለምና፥ ኹላችንም፡ በፊቱ፡ በደለኞች ነንና፡ ምናልባት፡ ፈጣሪ፡ እርስዎን፡ ኃጢኣተኛውን፡ በንስሓ ወደጽድቅ መልሶ፡ ይህ የኢትዮጵያ ትውልድ፡ በሥጋዊውና በነፍሳዊው፥ በመንፈሳዊውና በሃይማኖታዊው አቋሙና ምግባሩ፡ ከደረሰበት ውድቀትና ጕሥቍልና፡ እንደገና አንሠራርቶ ሊነሣና ጤናማ ህልውናውን፡ በመልካም ይዘት ሊቀጥል እንዲችል ለማድረግ፡ የማዳኑ መሣሪያ፥ የምሕረቱ ምልክትና የነሳሕያኑ (ንስሓ ለሚገቡ ኃጢኣተኞች ወገኖቹ) አብነት ሊያደርግዎ ፈልጎ ይኾናል! የአምላክን ጥበብ ማን ያውቃል?"

እዚህ ላይ፡ አስቀድሜ፡ በአኹኑ ጊዜ ያለውን፡ የእግዚአብሔርን እውነታ፡ ገሃድ ላድርግልዎ! እንደእኔ እምነት፡ አኹን ላሉበት የርእሰ ብሔርነት ክብርና ማዕርግ ያበቃዎ፡ በመንፈስ ቅዱስ የወለደዎ፡ የዘለዓለም አባትዎ፡ እግዚአብሔር መኾኑን፡ ቀደም ብዬ ገልጫለሁ። ከዚህ፡ ከበቁበት ክብርዎና ማዕርግዎ የተነሣ፡ ዛሬ፡ መኖርያዎ፡ ብሔራዊው ቤተ መንግሥት ኾኗል፤ እንደሥርዓተ መንግሥታችን፡ "ሥዩመ እግዚአብሔር" ተብሎ፡ የሚቀባው፡ "አጼ"ያችን በሚኖርበት ቤት ማለት ነው። እርስዎ፡ ይህን፡ የበቁበትን ክብርና ማዕርግ፡ የተቀበሉትና የሚያዩት፡ በሥጋዊዉና በዓለማዊው መልኩ ብቻ በመኾኑ፡ ለእርስዎ የሚያተርፍልዎ፡ ያንኑ፡ ሥጋዊዉንና ዓለማዊዉን፥ ምድራዊዉንና ጊዜያዊዉን ተድላና ደስታ ብቻ ነው፤ ከእነዚህ ሀብታት ጋር፡ ጣዕሙ፡ በቃላት ሊገለጽ የማይቻለውን፡ መንፈሳዊዉንና መልአካዊዉን፥ ሰማያዊዉንና ዘለዓለማዊዉን ጸጋና በረከት ሊያገኙ አይችሉም! እንደሥጋዊው ተድላ ደስታ ኹሉ፡ ይህንኛውንም፡ መንፈሳዊውን፡ ተድላና ደስታ ሊያስገኝልዎ የሚችለውን ጸጋና በረከት ሊታደሉ የሚችሉት፡ ከላይ እንዳመለከትሁት፡ ራስዎን፡ በቅዱሱ ኪዳን የተዋህዶ ሃይማኖትዎና ምግባርዎ አጽንተው፥ በንስሓም አጽድቀው፡ ቅዱሱን ቍርባን ሲቀበሉ ብቻ ነው። በዚያን ጊዜ፡ የእግዚአ ብሔራችን፥ ሊቀ ካህናታችንና ንጉሠ ነገሥታችን ኢየሱስ ክርስቶስ፥ የእናታችንና መቅደሳችን፥ ንግሥታችንና አገራችን ቅድስት ድንግል ማርያም ተጠሪ መኾንዎ ይሰማዎታል።

ቀጥዬ ደግሞ፡ የዚህ ሥርዓተ መንግሥታችን፡ ድንቅ ጸጋውና ዕፁብ በረከቱ፡ በምስጢራዊ ጥበቡና ተአምሩ የተከሠቱበትን፡ የባለቤትዎን አኗኗር ላመልክትዎ! ባለቤትዎ፡ ወይዘሮ ሳሌም ጳውሎስ፡ ከተወዳጁ ልጃችሁ ጋር፡ እንደእርስዎ፡ ሥጋዊዉና ዓለማዊዉ፥ ምድራዊዉና ጊዜያዊዉ ተድላና ደስታ ሳይቀርባቸው፥ መንፈሳዊዉንና መልአካዊዉን፥ ሰማያዊዉንና ዘለዓለማዊዉን ጸጋና በረከት በምልዓት ተቀብለው፥ እኔ፡ በተልእኮዬ፡ ተጠሪው በኾንሁለት አገልግሎት ዘንድ፡ "እቴጌ!" በሚለው፡ የማዕርጋቸው ስም እየተጠሩ በመሳተፍ፡ ይኸው፡ በእውነተኛው ተድላና ደስታ ይኖራሉ። የዚህ ኹሉ ጸጋና ክዋኔ ባለቤት የኾነው እግዚአብሔር፡ እርሳቸውን፡ እርስዎ ወደሚኖሩበት፡ ወደአዲስ አበባ ብሔራዊ ቤተ መንግሥት ከመውሰድ ይልቅ፡ እርስዎን፡ የኢትዮጵያን ርእሰ ብሔር፡ በቅርቡ፡ በግል ጉብኝት ምክንያት፡ እርሳቸው፡ በስደት ወደሚኖሩበት ወደአሜሪካ አምጥቶ፡ ለሦስት ቀናት ያህል፡ ወደመኖርያ ቤታቸው እየተመላለሱ እንዲያዩዋቸው፥ እርሳቸውም፡ እርስዎን፡ በመልካም አስተናግደው እንዲሸኙዎ አደረገ።

በዚህ መለኮታዊ ድርጊቱ፡ ፈጣሪዎ፡ ለእርስዎ እያስተላለፈው ያለው መልእክቱ፡ ከቶ ምን ይመስልዎታል? ምናልባት፡ እርስዎ፡ በዚህ ረገድ፡ ፈልገውትና ጠብቀውት፥ ዐቅደውትና ወስነውት የነበረው ዝግጅት፡ "የዚህን ተቃራኒውን ሊኾን ይችላል!" ብሎ መገመት ያስኬድ ይኾናል፤ ምክንያቱም፡ ባለቤትዎ የሚያስቡትና የሚያደርጉት፡ እንደእርስዎ መስሎዎ፡ "እርሷም፡ እንደዘመኑ ሥጋውያንና ዓለማውያን ሴቶች፡ ሥጋዊው ጥቅምና ዓለማዊው ምቾት ማርኳት፡ ያንን መርጣ፡ በምንም መንገድ፡ ወደእኔ መምጣቷ፡ መቼም አይቀርም!" ብለው፡ በእርስዎ በኩል፡ በፍጹም ተማምነው ጠብቀውት ሊኾን ስለሚችል ነው።

ከሰው ብልሃት፥ ወይም፡ ብልጠት ይልቅ፡ የእግዚአብሔር ሞኝነት እንደሚበልጥ፡ በቅዱሳት መጻሕፍት የተነገረው ቃል፡ እውነት ኾኖ፡ ያው፡ የእርስዎ ዕቅድ ቀርቶ፡ የእግዚአብሔሩ ተፈጽሞ አየን።

እስካኹንና በአኹኑ ጊዜ ያለውን፡ የበደልዎን ዓይነትና መጠን፥ የጤንነትዎን ኹኔታና ደረጃ፥ በጠቅላላ የኑሮዎን አካኼድና ገበና፡ ከእግዚአብሔርና ከእርስዎ ቀጥለው፡ ሌላውና ይልቁንም፡ ባለቤትዎ፡ ደህና አድርገው ያውቁታል። የሰጠውን ተስፋና ያደረገውን ቃል ኪዳን፡ ምንጊዜም፡ የማይረሳውና ከመፈጸም ወደኋላ የማይለው አምላክዎ፡ ከዚህ የተነሣ፡ እርሱን፡ አምላክዎን ብቻ ሳይኾን፡ የእርሱን መስቀል፡ በትዕግሥት ተሸክመው የኖሩትን ባለቤትዎን ጭምር፡ በእውነት መንፈስ ኾነው፡ ይቅርታን እንዲጠይቁ፡ ኹኔታዎችን በማመቻቸት፡ ከላይ የተጠቀሰውን የግል ጉዞዎን፡ ባለቤትዎ ወደሚገኙበት አገር እንዲያደርጉ አዘጋጅቶ፡ ወደአሜሪካ አመጣዎ።

ይህ ኹሉ የኾነው፡ "የኢትዮጵያ አምላክ፡ እርስዎን ሊታረቅዎና ወደንስሓ ሊመራዎ ስለፈለገ ነው!" ብሎ ለመደምደም፡ ምናልባት፡ ለእርስዎ እንጂ፡ ለሃይማኖታዊ ምእመን፡ ፈጽሞ አይከብደውም። እርስዎ ግን፡ በዚያ ታላቅ ዕድል ሳይጠቀሙበት ቀሩ! ይኹን እንጂ፡ ይቅርታው የበዛው አምላክዎ፡ ተስፋውን በማራዘም፡ በመስቀሉ ላይ በቆረሰው ሥጋውና ባፈሰሰው ደሙ የሰጠዎትን የንስሓ ዕድል፡ ይኸው አኹንም፡ በዚህ፡ በእኔ ደብዳቤ አማካይነት፡ እንደገና ሊያቀርብልዎ ፈቃዱ ኾነ!

በመጨረሻ፡ እርስዎንና ባለቤትዎን በሚመለከት፡ ሥርዓተ መንግሥታችን፡ ስለጋብቻችሁና የቤተሰብ ኑሮአችሁ ብቻ ሳይኾን፡ ብሔራዊው ሀብት ስለኾነው ሹመታችሁም፡ የሰጠው ድንጋጌ አለ፤ ይኸውም፡ "ኢትዮጵያዊት" በሚያሰኛቸው፡ በእግዚአብሔር ልጅነታቸው ስም፡ "ጽጌ ማርያም" የተባሉት፡ ባለቤትዎ፡ ወይዘሮ ሳሌም ጳውሎስ፡ በቅዱሱ ኪዳን ኢትዮጵያዊትነታቸው ምክንያት፡ በእግዚአብሔርና በኢትዮጵያ ዘንድ፡ ሥጋዊዉንና መንፈሳዊዉን የ"እቴጌ"ነት ክብርና ማዕርግ እንደተቀዳጁ ኹሉ፥ ይህንም እውነታ፡ አምላከ ኢትዮጵያ፡ እርስዎን፡ ወደእርሳቸው በማምጣት፡ በአካል ባስፈጸመዎ ድርጊት፡ ለራስዎና ለሌላውም፡ በገሃድ በማሳየት ስላረጋገጠው፡ እርስዎም፡ እንደእርሳቸው፡ ራስዎን፡ በሃይማኖትና በምግባር፡ ለቅዱሱ ኪዳን ኢትዮጵያዊነት ካበቁ፡ በቤተ ሕዝቡ የምርጫ ውሳኔ፥ በቤተ ምልክናው አቅራቢነትና በቤተ ክህነቱ ቀቢነት፡ "ሥዩመ እግዚአብሔር" የሚያሰኘውን፡ የ"አጼ"ውን የቅብዓት ስም ለመቀዳጀት የሚችሉ መኾንዎ ነው። ይህም የሚኾነው፡ ይኸው ሥርዓታችን፡ "በከመ ሢመቱ ለመልከ ጼዴቅ"፡ ማለትም፡ "'የእግዚአብሔር ልጅ' የሚያሰኘውን፡ እውነተኛ ሕዝባዊነቱን፥ ክህነቱንና ምልክናውን (ንጉሥነቱን) አጠቃልሎ እንደያዘውና የኢትዮጵያዊነት መሠረት እንደኾነው፡ እንደመልከ ጼዴቅ ሹመት ነው!" ሲል የደነገገውን መመሪያ ተከትሎ ይኾናል።

እርስዎና ባለቤትዎ፡ ለዛሬዋ ኢትዮጵያና ለዛሬዎቹ ኢትዮጵያውያን፡ "አጼ" እና "እቴጌ" ለመኾን የሚከለክላችሁ፡ ምን ምክንያት አለ? ከሌሎቹ፡ ይህን ማዕርግ አግኝተው ከነበሩት፡ ከቀድሞዎቹ የምታንሱበት ምን ጒድለት አለ? ምንም የለም። የመጨረሻው ጭቃ ሹምነት እንኳ፡ ያለእግዚአብሔር ፈቃድ እንደማይኾን ማመን፡ የእኛ ኢትዮጵያውያን ባህልና ፈሊጥ ኾኖ ኖርዋል፤ ታዲያ! እርስዎና ባለቤትዎ፡ ይህን ሹመት፡ አላገኛችሁትምን? "ማርያም የሾመችው!"፥ ወይም፡ "ዘውድ ያቀዳጀችው!" የሚል ትርጒም ያለውን፡ "መክብበ ማርያም" የሚለውን ስም፡ ገና በአርባ ቀንዎ የተቀዳጁ መኾንዎ ብቻ ሳይኾን፡ በግዙፍ አካሉ ጭምር አግኝታችሁትማ፡ ይኸው እኮ፡ ይዛችሁታል። እንደእግዚአብሔር ፈቃድና ውሳኔ ስለኾነ እንጂ፡ እንደሰዎች ፈቃድና ውሳኔ ቢኾንማ ኖሮ፡ "ይህ ሥልጣን የሚገባቸው፡ እነርሱ ናቸው!" እየተባለ የሚነገርላቸው፥ እየራሳቸውም ሳይቀሩ፡ "ይህ ሥልጣን የሚገባን፡ እኛ ነን!" እያሉ፡ አኹን ድረስ፡ ሌላው የሚደክምላቸው፥ ራሳቸውም፡ የሚደክሙ፡ አሉ አይደለምን? ነገር ግን፡ ይህ፡ የዛሬው፡ የኢትዮጵያ ትውልድ፡ "አልገባው!" አለ እንጂ፥ ወይም፡ አምኖ መቀበል አልፈለገም እንጂ፡ እውን ኾኖ እየተፈጸመ ያለው፡ የእነርሱ ሳይኾን፡ የእግዚአብሔሩ ብቻ መኾኑን፡ እግዚአብሔር ማሳየቱን፥ ትውልዱም፡ መመልከቱን ከጀመሩ ቆይተዋል።

ለዚህም፡ ሩቅ መኼድ አያስፈልግም፤ እስኪ፡ ከእርስዎ፡ ከራስዎ ጀምረን፡ ወደኋላ እየተከተልን እንመልከት! እርስዎ፡ ማነዎት? ለቅጣቱና ለጥፋቱም ቢኾን፡ ይኸው፡ ዛሬ፡ እርስዎ፡ አጼ ኃይለ ሥላሴ ተቀምጠውበት በነበረው ዙፋን ላይ፡ ጉብ ብለውበት ያሉ አይደለምን? ይኼስ፡ እውን አይደለምን? ትናንትስ፡ አቶ መለስ ዜናዊ፥ ከትናንት ወዲያስ፡ ለጥቂት ቀናትም ቢኾን ጦር አዝማች ተስፋዬ ገብረ ኪዳን፥ ከዚያም ወዲያ፡ እልፋለቃ መንግሥቱ ኃይለ ማርያም፥ ያን አልፎም፡ ጦር አዝማቾች ተፈሪ በንቴና አማን አንዶም ታይተውበት አልነበረምን? በታሪክ መነጽር፡ ወደኋላ፡ ጥቂት ራቅ ብለን ስንመለከት ደግሞ፡ የቀደሙትን፡ አጼ ላሊበላንና እርሱን የመሰሉትን አቆይተን፡ የቅርቦቹ፡ የኢትዮጵያ ከዋክብት ሰማዕታት የኾኑትን፡ አጼ ዮሓንስንና አጼ ቴዎድሮስን ስናያቸው፡ "እኒህ ኹሉ፡ እነማን ነበሩ?" ብለን እንድንጠይቅ፥ እኒህማ፡ "'የሰሎሞን ዘር አይደሉም!' የተባሉት ናቸዋ!" ብለንም እንድንመልስ እንገደዳለን፡፡

አዎን! እኒህ ኹሉ፡ ግብፃውያን፡ ለጥቅማቸው ሲሉ፡ በሥውር የተማማሉበት፡ የሰሎሞናዊው ዘር ምሥጢራዊ ቃል ኪዳን፡ በእግዚአብሔር የእውነት መንፈስ ላይ ያልተመሠረተ፥ የሰዎች እንጂ፡ የእርሱ ያለመኾኑን፡ እግዚአብሔር፡ ለኢትዮጵያውያንና ለቀረው ዓለም፡ በግልጽ አሳይቶ፡ ያን፡ ቃል ኪዳናቸውን ያፈራረሰው መኾኑን፡ አረጋግጦ ሊያሳውቅ፡ ለአብነትና ለመቀጣጫ ጭምር ያስነሣቸውና ቀብቶ የሾማቸው መኾኑ ሊታበል አይቻልም፡፡ ይህንንስ፡ እኛ ጭምር፡ የዓይን ምስክሮች በመኾን ያረጋገጥነው አይደለምን?

ዳግማዊ አጼ ምኒልክ፡ በዚሁ፡ በሰሎሞናዊው ዘር ፈሊጥ አምነውና ራሳቸውን፡ የዚያ ወገን በማድረግ፡ ልጃቸውን "ዘውዲቱ"ን ትተው፡ የልጅ ልጃቸውን "ኢያሱ"ን፡ በአልጋ ወራሽነት፡ ለአጼነቱ ሥልጣን ማጨታቸውን፡ ለሕዝብ አውጀውና ለሹሞቻቸው አደራ ብለው፡ በመሓላ ያጸኑትን የኑዛዜ ቃል፡ ራሳቸው፡ አጼ ኃይለ ሥላሴ ሳይቀሩ ማፍረሳቸውን፡ ኹሉም ያውቀዋል፡፡ በአጼ ምኒልክ ኑዛዜ ላይ የደረሰውን፡ ያን፡ የእግዚአብሔርን አስተምህሮና ማስጠንቀቂያ፡ አጼ ኃይለ ሥላሴ በመናቅ፡ ቸል ብለው፡ ያንኑ የአጼ ምኒልክን ስሕተትና ጥፋት በመድግማቸው፡ "አልጋ ወራሼ" ብለው በሠየሟቸው፡ በልጃቸው፡ በ"አስፋ ወሰን" ላይ የደረሰውን እንግልትና ፍጻሜ፥ ዛሬም፡ በልጅ ልጃቸው፡ በ"ዘርዓ ያዕቆብ" ላይ እየደረሰ ያለውን ኹኔታ እንመለከታለን፡፡ ታዲያ! ልናምነውና ልንቀበለው የሚገባን፡ የትኛውን ነው? እውን የኾነውንና ተጨባጩን እንጂ፡ እንደምትሓት፡ በአሳብና በምኞት፥ ወይም፡ በሕልም ዓለም የሚዋልለውን ሊኾን አይገባም፡፡

የቃል ኪዳን አምላካችን፡ ለእኛ ለኢትዮጵያውያን፡ እስከዛሬ ድረስ፥ አኹንም፡ እያስተማረን ያለው እውነታ፡ በቅዱሱ ኪዳን ምክንያት፡ እያንዳንዱ ኢትዮጵያዊና እያንዳንዷ ኢትዮጵያዊት፡ ለ"አጼነት" እና "ለንግሥትነት"፥ ወይም፡ "እቴጌነት" የሚበቁ መኾናቸውን ነው፡፡ ይህም ማለት፡ በአማናዊው መልከ ጼዴቅ፡ በኢየሱስ ክርስቶስና በአማናዊቷ ኢትዮጵያ፡ በቅድስት እናቱ ድንግል ማርያም፡ በተገኘው፥ "ኢትዮጵያዊ" በሚያሰኘው፡ የእግዚአብሔር ልጅነት ምክንያት፡ ኢትዮጵያዊቷ ንግሥት ማክዳ፡ ከዳዊት ልጅ፡ ከሰሎሞን ከወለደችው፡ ከምኒልክ፡ የሥጋ ዘርን መካፈል ብቻ ሳይኾን፡ በይበልጥ፡ ከእግዚአብሔር፡ በመንፈስ በመወለድ፡ የወራሴ መንግሥቱን ሥልጣን፡ እያንዳንዱ፡ ኢትዮጵያዊና እያንዳንዷ ኢትዮጵያዊት፡ በቀጥታ፡ በመንፈስ ቅዱስ፡ ከንጉሡ፡ ከኢየሱስ ክርስቶስና ከንግሥቲቱ፡ ድንግል ማርያም ያገኛሉ ማለት ነው፡፡

በሥጋ ዘር የሚተላለፈው፡ ሰብአዊው ልደትማ፡ ኢየሱስ ክርስቶስ፡ ከቅድስት ድንግል ማርያም፡ በተወለደ ጊዜ፡ ቆሟል፤ ከኢየሱስ ክርስቶስ በኋላ የቀጠለው ልደት፡ ሥጋዊው ሳይኾን፡ መንፈሳዊው ነው፤ ይህንም፡ በዮሓንስ ወንጌል፡ ምዕራፍ ፩፥ ቍጥር ፲፪-፲፫ ላይ፡ እንዲህ የሚለው የምሥራቹ ቃል እያረጋገጠ፡ ይነግረናል፡- *"ለሰው ኹሉ የሚያበራው፡ እውነተኛው ብርሃን* [ኢየሱስ ክርስቶስ] *ወደዓለም ይመጣ ነበር፡፡ በዓለም ነበረ፤ ዓለሙም፡ በእርሱ ኾነ! ዓለሙም፡ አላወቀውም፡፡ የእርሱ ወደኾነው መጣ! የገዛ ወገኖቹም አልተቀበሉትም፡፡ ለተቀበሉት ኹሉ ግን፥ በስሙ ለሚያምኑት፥* [ለቅዱሱ ኪዳን ኢትዮጵያውያን] *ለእነርሱ፡ የእግዚአብሔር ልጆች ይኾኑ ዘንድ፡ ሥልጣንን ሰጣቸው፤ እነርሱም፡ ከእግዚአብሔር ተወለዱ እንጂ፡ ከደም፥ ወይም፡ ከሥጋ ፈቃድ፥ ወይም፡ ከወንድ ፈቃድ አልተወለዱም፡፡"*

...፳፰

እንግዴህ፡ በኢትዮጵያ ሰፍና ለኖረችውና ለምትኖረው፡ ለእግዚአብሔር መንግሥት፡ በዚህ፡ በኪዳነ ምሕረቱ ዘመን፡ ተጠሪ ለመኾን፡ "ሥዩመ እግዚአብሔር" ተብሎ፡ በ"አጼ"ነት፥ ወይም፡ "ሥይምተ እግዚአብሔር" ተብላ፡ በ"ንግሥት"ነት ተመርጠው ለመሾምና ለመቀባት፡ በወሳኝ ባለመብትነት፡ የሚያስፈልገው መሥፈሪያና የሚጠየቀው ብቅዓት የሚገኘው፡ ከክርስቶስ ልደት በፊት እንደነበረው ኦሪታዊ ሥርዓት፡ "ከሰሎሞናዊው ዘር"፥ ወይም፡ "የትውልድ ሓረግ"፡ በሥጋ መወለድን ሳይኾን፡ በመንፈስ ቅዱስና በክርስትና የውኃ ጥምቀት፡ የእግዚአብሔር ልጆች የመኾንን ሥልጣን፡ ተቀዳጅቶ፡ ራስን፡ ለቅዱሱ ኪዳን ኢትዮጵያዊነት ሃይማኖትና ምግባር በማብቃት መኾኑን፡ ከላይ የተጠቀሰው፡ የወንጌላዊው ቃል፡ ግልጽ አድርጎ ደንግጎታል።

እንዲህ፡ ከእግዚአብሔር፡ በመንፈስ ቅዱስ ጸጋና በክርስትና የውኃ ጥምቀት ተወልደው፡ የእግዚአብሔር ልጆች የመኾንን ሥልጣን ያገኙት፡ እኒህ፡ የቅዱሱ ኪዳን ኢትዮጵያውያንና ኢትዮጵያውያት፡ በአባልነት በሚያገለግሉበት የ"ቤተ ሕዝብ" መንግሥታዊ ዘርፋቸው አማካይነት፡ "አጼያቸውን"፥ ወይም፡ "ንግሥታቸውን"፡ ከመካከላቸው መርጠው፡ ሹመቱን፡ በ"ቤተ ምልክናው" አቅራቢነትና በ"ቤተ ክህነቱ" ቀቢነት አጽድቀው የሚፈጽሙበትም መመሪያ፡ በሥርዓተ መንግሥታቸው ውስጥ ተደንግጎ ይገኛል። ይኹን እንጂ፡ የዚህ ሥርዓት፡ ፍጹም ፍሬያማነት የማያጠራጥር ሲኾን፡ በሰዎች፡ የሃይማኖት ጉድለትና የምግባር ብልሹነት ምክንያት፡ ከነቀፋና ከውድቀት አዘቅት እስከመውደቅ የሚያደርስ በደል ሊካኼድበት እንደሚቻል፡ እነሆ፡ በዕድሜያችን፡ በአገራችን ላይ ሲወርድ በሚታየው ፈተናና መከራ እንመለከተዋለን።

የዚህን እውነታ፡ በማስረጃ ለማረጋገጥ፡ አኹንም እንደገና፡ የራስዎን አባቶች ምሳሌ አድርጌ አቀርብልዎታለሁ። ልጅ ኢያሱ፡ ሥርዓተ መንግሥታችን በሚፈቅደው፡ በቅዱሱ ኪዳን ሃይማኖትና ምግባር ጸንተው ባለመገኘታቸው፡ በዳግማዊ አጼ ምኒልክ የአደራ ኑዛዜ መሠረት፡ እርሳቸውን፡ ለአጼነቱ ሥልጣን ማብቃቱ ቀርቶ፡ በአልጋ ወራሽነቱም እንኳ ለማቆየት እንዳልተቻለ ይታወሳል፤ ከዚህ የተነሣ፡ በያግጣጫው ሲካኼድ ይታይ በነበረው፡ በአገሪቱ ጸጥታ መታወክ ምክንያት፡ የእርስ በርስ ጦርነት እንዳይቀሰቀስ ያሠጋበትና ያስፈራበት ወቅት እንደነበረም አይዘነጋም። በዘመኑ፡ ቤተ ምልክናውን ይወክሉ የነበሩት፡ ፊታውራሪ ሀብተ ጊዮርጊስ፡ በዚያን ቀውጢ ጊዜ፡ ሕዝቡን በማረጋጋት፡ ተተኪ የሚኾነውን "እጩ አጼ" መርጦ ለማውጣት፡ "መኻል ሠፋሪ" ይባል ከነበረው፡ ከቤተ ሕዝቡና እንዲሁም፡ ከቤተ ክህነቱ ዘርፎች ተጠሪዎች ጋር፡ እንዴት ተባብረው፡ ለከባዱ ችግር፡ ተገቢውን መፍትሔ እንዳገኙ ተነግሩዋል። በዚያ፡ የመፍትሔ ሓሳብ መሠረት፡ ፊታውራሪ ሀብተ ጊዮርጊስ፡ ታላቂቱን የምኒልክን ሴት ልጅ፡ ወይዘሮ ዘውዲቱን፡ ለ"ንግሥትነት"፥ ከጥቂቶቹ እጩዎች ወንዶች መካከል ደግሞ፡ "ቢያለማም፥ ቢያጠፋም፡ የመኰንን ልጅ፡ ተፈሪ ቢኾን ይሻላል!" በሚል አስተያየት፡ ደጃዝማች ተፈሪን፡ ለ"አልጋ ወራሽነት"፡ በተመራጭነት አቅርበው፡ ይኸው አሳባቸው፡ በኹሉም ዘንድ ተቀባይነትን ስላተረፈ፡ በዚሁ ስምምነት መሠረት መፈጸሙ ይታወቃል። ዛሬ፡ democracy እየተባለ፡ የሚለፈፍለት የባዕዳን ፈሊጥ፡ ለኢትዮጵያውያን፡ አዲስ ወይም እንግዳ ነገር አለመኾኑን፥ ራሱን በቻለ የተለየ መልኩና ባሕርዩ፡ በኢትዮጵያ፡ ከጥንት ጀምሮ ሲሠራበት የተኖረ መኾኑን፡ እዚህ ላይ በማስተዋል መመልከቱ አግባብ ይኾናል።

ፊታውራሪ ሀብተ ጊዮርጊስ፡ ይህን የመፍትሔ ሓሳብ አቅርበው፡ የዘመኑ፡ የኢትዮጵያ መንግሥት ችግር እንዲወገድ ከማድረጋቸው በፊት፡ ለአጼነቱ ሥልጣን፡ በኹሉም ዘንድ፡ ሙሉ ተቀባይነት ያለው እጩ በታጣበትና የአለመግባባቱ ውዝግብ፡ በበረታበት ኹኔታ መካከል፡ "ለዚህ ሥልጣን፡ ከእርስዎ የተሻለ፡ ሌላ ሰው የለምና፡ ለምን እርስዎ አይነግሡም?" የሚል ጥያቄ፡ ከቤተ ሕዝቡ ቀርቦላቸው እንደነበረ፥ እርሳቸው ግን፡ ያሉበት የኃላፊነት ቦታና የአገር አገልግሎት የሚበቃቸው መኾኑን በማስረዳት፡ አሳቡን ሳይቀበሉት መቅረታቸው ይዘከራል።

በዚያን ጊዜ፡ ደርሶ ለነበረው ብሔራዊ ችግር፡ መፍትሔ የኾነውን ቀና መንገድ አስይዞ፡ መግባባትን፥ አንድነትንና ስምምነትን ሊያስገኝ የቻለው ፍቱን መዛሪያና ኃይል፡ ይህ ሥርዓተ መንግሥታችን መኾኑ ግልጽ ነው። በእውነተኛው የኢትዮጵያዊነት መንፈስ የተመላ፡ ፊታውራሪ ሀብተ ጊዮርጊስን የመሰለ፡ እውነተኛ ኢትዮጵያዊ ሲኖር፡ በዚህ ሥርዓተ መንግሥታችን፡ እንዲህ አድርጎ፡ በእውነትና በትክክል ይሠራበታል፤ ይኸው ሥርዓተ መንግሥታችን፡ በእውነትና በትክክል ሲሠሩበት ደግሞ፡ ይህን የመሰለውን፡ መልካም ፍሬያማ ውጤት ያበረክታል።

"የሰሎሞን ዘር ናቸው!" ተብለው፡ "ኃይለ ሥላሴ" በሚለው የክርስትና ስማቸው፡ ለአጼነት ከበቁት፡ ከደጃዝማች ተፈሪ ይልቅ፡ ሥርዓተ መንግሥታችን የሚፈቅደው በመኾኑ፡ ቤተ ሕዝቡ፡ ለእርሳቸው ያቀረበውን አሳብ፡ ፊታውራሪ ሀብተ ጊዮርጊስ ተቀብለው፥ ነግሠው ቢኾን ኖሮ፡ አገራችን ኢትዮጵያና ወገናችን የኢትዮጵያ ሕዝብ፡ ዛሬ "ኾነው" የሚገኙትን ይመስሉ ነበርን? አይመስሉም!

ምክንያቱም፡ ሰው የሚሰበስበው፡ የዘራውን ነውና፡ በአኹኑ ጊዜ፡ የአጼ ኃይለ ሥላሴ የሥራ ፍሬ፡ ምን ዓይነት እንደኾነ ለመረዳት፡ እርሳቸው፡ ዘርተው ያፈሩት፡ ይህ ትውልድ፡ በገሃድ እየፈጸመ ያለውን ድርጊት መመልከቱ ብቻ ይበቃል። ይኸውም፡ እነፊታውራሪ ሀብተ ጊዮርጊስ፡ በመሥዋዕትነታቸው፡ ጠብቀው ያስረከቡትን፡ የኢትዮጵያን አንድነትና ነጻነት የመሰለውን መልካም ብሔራዊ ውርስ፡ ይህ ትውልድ፡ ተንከባክቦ ይዞ፡ በዘመናዊው መልክ ለማሳመርና ለማሻሻል በመታገል ፋንታ፡ ለጥፋት ዓላማው፡ "ሥር-ነቀል" የሚል ግልጽ ስያሜ ሰጥቶ፡ ይህንኑ፡ ከወላጆቹ የተረከበውን መልካም ውርስ፡ "ማንነቱን" ሳይቀር፡ ደምስሶ ለማስወገድ፡ እነሆ፡ ሲጥር በመታየቱ ነው።

ጣፋጩን፡ የፊታውራሪ ሀብተ ጊዮርጊስን፡ የሥራ ፍሬማ፡ መላው፡ የኢትዮጵያ ቤተ ሕዝብ፥ ቤተ ምልክናውንና ቤተ ክህነቱን ጨምሮ፡ በጣዕሙ ሳይቀር፡ እስከዛሬና ዛሬ፥ ወደፊትም፡ አብነት እያደረገ ሲጠቀምበት ይኸው፡ ይታይ የለምን? በብሔራዊው፥ በሕዝባዊውና በመንግሥታዊው ደረጃ ብቻ ሳይኾን፡ በግልና በጋብቻ፥ በትዳርና በቤተሰብ ኑሮአቸው፥ ይልቁንም፡ በሃይማኖትና በምግባር ሕይወታቸው፡ ለእያንዳንዱ ኢትዮጵያዊ፥ በተለይም፡ ለዛሬው ትውልድ፡ ትተውት ያለፉት፡ የእውነተኛ ኢትዮጵያዊነት ምሳሌነታቸው፡ እጅግ የሚያኮራ ኾኖ ይኖራል። በእውነተኛ ንስሓ፡ ለፍጹምነት የበቃው፡ የቅዱሱ ኪዳን ኢትዮጵያዊነት ሃይማኖታቸው፡ ቀድሞ፡ በዓፀደ ሥጋ ሣሉ በፈጸሙትና ዛሬ፡ በዓፀደ ነፍስ እያሉ፡ ሲፈጽሙት በሚታዩት ምግባራቸው ተከሥቷል፤ ይኸውም፡ በሕይወተ ሥጋ ሣሉ፡ በቅዱስ ቁርባን በጸደቀና በጸና ጋብቻ ተወስነው፡ እንደሥርዓተ መንግሥታችን፡ በሕዝባዊ ወገንነታቸው፡ ቤተ ሕዝቡን፥ በሹመት ሥልጣናቸው፡ ቤተ ምልክናውን፥ በእግዚአብሔር ልጅነታቸውም፡ ቤተ ክህነቱን፡ በፍጹም የታማኝነት ምግባር በማገልገላቸው ተረጋግጧል፤ አኹን፡ በሕይወተ ነፍስ እያሉም፡ ሰፊ ንብረታቸውን፡ በኑዛዜ ባወረሱት፡ በአዲስ አበባ የበዓታ ለማርያም ቤተ ክርስቲያን ሥር በተቋቋመው፡ በዳግማዊ ምኒልክ በጎ አድራጎት ድርጅትና መኖርያ ቤታቸው በነበረበት ቦታቸው ላይ ታንፆ፡ የሰበካ ጉባዔ ተግባራትን በሚያካኺደው፡ በዛሬው የአዲስ አበባ፡ ደብረ ኃይል ቅዱስ ራጉኤል ቤተ ክርስቲያን አማካይነት፡ ይህንኑ፡ የታማኝነት አገልግሎታቸውን በመቀጠላቸው ይታወቃል።

እንዲህ ከኾነ፡ እርስዎ፡ ተወልደውበትና አድገውበት፥ ኖረውበትና ታውቀውበት ለሚገኙበት፡ ለቅዱሱ ኪዳን ኢትዮጵያዊነት፡ እንደባለቤትዎ፡ ዛሬ፡ ራስዎን፡ በንስሓ አድሰው ካጸደቁ፡ ከዚህ በላይ በተገለጸው መልክ፡ ሕያው ኾኖ፡ ሲሠራ በኖረው፡ ሥርዓተ መንግሥታችን መሠረት፡ እናንተ ባልና ሚስቱ፡ ለ"አጼነቱ" እና ለ"እቴጌነቱ" ማዕርግና ክብር የማትበቁበት፡ ምንም ዓይነት ምክንያት ከቶ የለም። በዚህ ጊዜ፡ የቅዱሱ ኪዳን ኢትዮጵያዊነታችሁ፡ ለእግዚአብሔር ልጅነት ያበቃችሁ በመኾኑ፥ ይህ፡ የእግዚአብሔር ልጅነታችሁ ደግሞ፡ "የሰሎሞን ዘር" የሚያሰኘውንም ቃል ኪዳን ያጠቃልለ ስለኾነ፡ የዚህ እምነት ተከታዮች ሳይቀሩ፡ እንደነአጼ ቴዎድሮስና አጼ ዮሓንስ፡ በዚሁ ሥልጣናችሁና ማዕርጋችሁ እንዲቀበሏችሁ፡ ግድ ይኾንባቸዋል።

...፴

በዚህ መልክ፡ የእናንተ፡ ለዚህ ሥልጣንና ማዕርግ መብቃት፡ ለኢትዮጵያ የአንድነት ህልውናና ለሕዝቧ ሰላማዊ ኑሮ መመለስ፡ እንዴት ያለውን ታላቅ አስተዋጽዖ ሊያበረክት እንደሚችል፡ እውነታውን እንዳመለክትዎ ይፍቀዱልኝ!

"ኢትዮጵያ" በተባለችው ምድር ላይ ይኖሩ የነበሩ፡ የተለያዩ ጎሣዎች፥ ሃይማኖቶችና ቋንቋዎች፡ በእግዚአብሔር የፍቅር ውሕደት ተስማምተው በመጋባታቸውና በመዋለዳቸው፡ ራሳቸውን፡ ቀድሞ፡ በግእዝ ቋንቋቸው፡ 'አግዓዝያን'፡ ማለትም፡ 'ነጻ አውጪዎች'፥ ኋላም፡ 'ዐምሓራ'፡ ማለትም፡ 'ነጻ ሕዝብ' ብለው በመጥራት፡ አንድ ባደረጋቸው፡ የዐማርኛ ቋንቋቸው እየተነጋገሩና በአንዱ የቅዱሱ ኪዳን ሃይማኖታቸው የሚመሩ፡ አንድ የኢትዮጵያ ሕዝብ ኾኑ! 'ኢትዮጵያ ታበጽሕ እደዊሃ ኀበ እግዚአብሔር!' ማለትም፡ 'ኢትዮጵያ፡ እጆቿን ወደእግዚአብሔር ትዘረጋለች!' በተባለችውና ራሷ፡ ድንግል ማርያም፡ ዘለዓለማዊቷ እናታቸውና ንግሥታቸው በኾነችው በአንዲት አገራቸው፡ በኢትዮጵያ የሚኖሩም ኾኑ! ለእስራኤል ልጆች የተሰጡትን ቃል ኪዳናት ኹሉ፡ በእነርሱ ክህደት ምክንያት፡ ወደታማኞቹ ኢትዮጵያውያን ላዛወረው፡ ለኢትዮጵያዊው ሊቀ ካህናታቸውና ንጉሠ ነገሥታቸው፡ ለኢየሱስ ክርስቶስ የተነገረው፡ 'ሞዓ አንበሳ፡ ዘእምነገደ ይሁዳ!' ማለትም፡ 'ከይሁዳ ነገድ የተገኘው አንበሳ፡ ድል አደረገ!' የሚለውን ማኅተም፡ በማዕከሉ ያሠፈረውን፡ የአረንጓዴ፥ የብጫና የቀይ ኅብረ ቀለማትን የያዘውን፡ የሰማዩን ቀስተ ደመና ምልክት፡ ሰንደቅ ዓላማቸው አድርገው እያውለበለቡ፡ በአንዱ በእግዚአብሔር ሥርዓተ መንግሥት የሚተዳደሩ ኾኑ!"

እርስዎና ባለቤትዎ፡ በመጀመሪያ፡ ከእኚህ፡ የእግዚአብሔር የቃል ኪዳን ወገን ከኾኑት፡ ከግንዶቹ አባቶቻችሁና እናቶቻችሁ በቅላችሁ፡ ለፍሬነት የደረሳችሁ፡ የዛሬዎቹ ሕያዋን ቅርንጫፎች በመኾናችሁ፥ ቀጥሎ፡ ከእነርሱ በተወለዳችሁበት፡ የሥጋ ልደታችሁ፡ ለእውነተኛው የቅዱሱ ኪዳን ኢትዮጵያዊነት የሚያበቃውን መደበኛ መብት በማግኘታችሁ፥ በመጨረሻ፡ ከእግዚአብሔር፡ በየራሳችሁ በታደላችሁት፡ የመንፈስ ቅዱስ ልደታችሁ፡ ይህን ማንነታችሁን፡ ፍጹም ሙሉ በማድረጋችሁ፡ ለ"አጼነቱ" እና "ለእቴጌነቱ" ሥልጣንና ማዕርግ ብቁ ኾናችሁ ለመገኘታችሁ፡ እነዚህ መሥፈሪያዎች፡ በቂ ማስረጃዎች ናቸው፡፡ እነዚህ መሥፈሪያዎች፡ በባለቤትዎ በኩል፡ የተሟሉ ሲኾኑ፡ በእርስዎ በኩል፡ እንዲሟላ የሚጠበቅ ቀሪ ቁም ነገር ቢኖር፡ በሃይማኖታዊውና በምግባራዊው ንስሓና ቅዱስ ቁርባን ሊጸድቅ የሚገባውን ኢትዮጵያዊነትዎን፡ በቅዱሱ ኪዳን፡ ማስተካከል ብቻ ይኾናል፡፡

ይልቁንም፡ በአኹኑ ጊዜ፡ የየግል የብልጠት፥ የገንዘብና የሥልጣን ፍትወታቸውን ለማርካት ብቻ ሲሉ፡ የጎሠኝነት ጠንቅ ተጠናውቷቸው፡ የኢትዮጵያን ሕዝብ፡ በጥላቻ መንፈስ፡ እርስ በርሱ እንዲለያይ የሚያተረማምሱትን ጥቂቶች ቡድኖች ቅስም ለመሥበር የሚያስችለውን ኃይል፡ ኹለታችሁም፡ በዚህ መልክ መታጠቃችሁ፡ መፍትሔ አጥቶ ለቆየው፡ ለዚህ መርዘኛ ብሔራዊ በሽታ፡ "ፍቱን መድኃኒት ተገኘለት!" ማለት ይኾናል፤ በዚህ ጊዜ፡ ይህ የእናንተ፡ የ"አጼነቱ" እና የ"እቴጌነቱ" ሹመት፡ ለኢትዮጵያና ለሕዝቧ ደህንነት ለሚያስብ ኹሉ፡ ታላቅ የምሥራች ዜና እንደሚኾንለት እሙን ነው፤ ምክንያቱም፡ ኹሉን ጎሣ፥ ቋንቋና እምነት ካጠቃለለው፡ ከኹለታችሁም ዐምሓራነት በላይ፡ እያንዳንዳንዳችሁ፡ ከየወላጆቻችሁ፡ "በተጨማሪ አግኝታችሁታል!" የሚባለውን፡ በእርስዎ በኩል ያለውን፡ "ኦሮሞነትንና ጕራጌነትን"፥ በባለቤትዎም በኩል ያለውን፡ "ትግሬነትን" አክላችሁ ስለተገኛችሁ፥ በጎሣ ሰበብ፡ እንደኤርትራ፡ ተገንጥለው ሊለዩ አቆብቁበው የሚጠባበቁትን፡ በተለይ ትግሬዎችንና ኦሮሞዎችን፡ እግዚአብሔር፡ በመለኮታዊ ቃሉም ኾነ በሰውነት ደሙ አንዲት ባደረጋት፡ በአገራቸው በኢትዮጵያና አንድ ባደረገው፡ በኢትዮጵያ ሕዝብነታቸው ጸንተው ይኖሩ ዘንድ፡ የሚያሳምንና የሚመልስ ጽኑ ማስረጃ በመኾኑ ነው፡፡

ማንኛውም ሰብአዊ ፍጡር፡ ኢትዮጵያዊዉንና ኢትዮጵያዊቷን፥ እርስዎንና እኔንም ጨምሮ፡ ቢያምንበትም፡ ባያምንበትም፥ ቢቀበለውም፡ ባይቀበለውም፡ ሥርዓተ መንግሥታችን፡ አያሌ ቊም ነገሮችን አጠቃልሎ ስለያዘው፡ ስለኢትዮጵያና ኢትዮጵያዊነት የሚገልጸው እውነታ፡ እንግዴህ፡ ይህ ነው፡፡

ክቡር ርእሰ ብሔር!

በዚህ ደብዳቤ ውስጥ የተጠቃለለው፡ ይህ መልእክት፡ በኢትዮጵያ፡ የእግዚአብሔር መንግሥት አገልጋይነቴ፡ ለእርስዎ፥ በአኹኑ ጊዜም፡ እርስዎ፡ በርእሰ ብሔርነትዎ፡ የኢትዮጵያና የዚህ የኢትዮጵያ ትውልድ ተጠሪ እንደመኾንዎ፡ በእርስዎ አማካይነት፡ ለመላው የኢትዮጵያ ሕዝብ፡ ለወንዱና ለሴቱ፥ ለሽማግሌውና ለወጣቱ ኹሉ፥ ለቤተ ሕዝቡ፥ ለቤተ ክህነቱና ለቤተ ምልክናው አለቆችና ባልደረቦች ጭምር፡ አደርስ ዘንድ፡ የእግዚአብሔር መንግሥት ከኾነችው፡ ከኢትዮጵያ የተላከ መኾኑን፡ በታላቅ የዓዋጅ ቃል አስታውቃለሁ።

የእግዚአብሔር ሥርዓተ መንግሥት ሰፍኖባት፡ ለረዥም ዘመናት፡ በህልውናዋ፥ በነጻነቷና በአንድነቷ ጸንታ የኖረችው፡ አገራችን ኢትዮጵያ፡ በእኛ፡ በልጆቿ ጥፋትና ስሕተት ምክንያት፡ ዛሬም፡ ምን ዓይነቱን የፈተናና የመከራ ጽዋ፡ እኛው ልጆቿ፡ ተቀብለን፡ እየተሳተፍን እንደኾን፡ እርስዎ፡ “ፈተናውና መከራው አልደረሰብኝም!” ካላሉ በቀር፡ እያንዳንዳችን፡ በየራሳችን እየተጐነጨንለት ስለምንገኝ፡ ኹላችንም እናውቀዋለን። በአንድ በኩል፡ በክፉ ገጽታው ሲታይ፡ ዛሬ፡ የምንገኝበትን ኹኔታ ያመጣነው፡ እኛው ስለፈለግነው፥ ጸንቶ የቀጠለውም፥ ወይም፡ እየከፋ የኼደው፡ እኛው፡ “ተስማምቶናል!” ብለን ስለተቀበልነው መኾኑን፡ ከእግዚአብሔር ያገኘነው፡ ይኸው ሥርዓተ መንግሥታችን ይነግረናል፤ በሌላው በኩል ደግሞ፡ በደጉ ገጽታው ሲታይ፡ በምድር ላይ፡ ለእያንዳንዱ ሰው፡ ፍጹሟን መልካም ሕይወት ታቀዳጅ ዘንድ፡ ቀድሞ፡ በአዳምና ሔዋን፥ ኋላም፡ በኢየሱስ ክርስቶስና ቅድስት እናቱ ድንግል ማርያም ንጉሥነትና ንግሥትነት፡ ለዓለም የተገለጠችው፥ የምንናፍቃት መልካሟ የእግዚአብሔር መንግሥት እንድትመለስልን ከፈለግን፡ ይኸው ፍላጎታችን እንደሚፈጸምልን ያበሥረናል፤ ከዚህም ጋር፡ የዛሬዪቱ ኢትዮጵያና የዛሬዎቹ ኢትዮጵያውያን ፍላጎትና ምኞት፥ ውጥንና ዕቅድ፥ እምነትና ምግባር፡ በአጠቃላይ፡ ማንነታቸውና ምንነታቸው፡ ምን ዓይነት እንደኾነ፡ ለራሳቸው ብቻ ሳይኾን፡ ለመላው ፍጥረተ-ዓለም፡ በይፉ ሊያሳውቅ፡ እግዚአብሔር፡ እርስዎን፡ በርእሰ ብሔርነት፥ መሰሎችዎንም፡ በቤተ ሕዝቡ፥ በቤተ ክህነቱና በቤተ ምልክናው መንበሮች ላይ ማስቀመጡን፡ አኹንም፡ ይኸው ሥርዓተ መንግሥታችን ያረጋግጥልናል።

እንግዴህ፡ ከላይ እንደጠቀስሁት፡ እንደሥርዓተ መንግሥታችን ድንጋጌ፡ እርስዎንና መሰሎችዎ የኾኑትን፡ የየቤቱን ተጠሪዎች የሚያካትተው፡ ይህ፡ የኢትዮጵያ ትውልድ፡ “የአገሬንና የራሴን ዕድል፡ ዛሬ ባለው ኹኔታ፡ ማለትም፡- ኢትዮጵያና ሕዝቧ፡ ለሰባት ሺ፡ አራት መቶ ዘጠና ሰባት ዓመታት፡ ጠብቀውት በኖሩት፡ በእግዚአብሔር ቃል ኪዳናት ላይ የጀመርሁትን፡ የክህደት፥ የዓመፅና የአመንዝራነት ኃጢኣቴን እቀጥልበታለሁ!” ካለ፡ ይችላል፤ ዛሬ ያለው፡ የመከራና የሥቃይ ውጣ ውረድ ይቀጥላል ማለት ነው። “አይ! ከዚህ የኃጢኣት አካኼዴ፡ በንስሓ እመለሳለሁ!” ካለም፡ ከጥፋት መንገዱ ተመልሶ፡ እውነተኛዋን የተድላ ደስታ ሕይወት ለመኖር ይቻለዋል ማለት ነው። እኔም፡ በዚህ ደብዳቤዬ፡ እርስዎንና የየቤቱን ተጠሪዎች፥ ትውልዱንም የምማፀነው፡ ምርጫችሁ፡ ይህ፡ ኹለተኛውና የመጨረሻው ጽዋ እንዲኾን ነው።

የእርስዎና የየቤቱ ተጠሪዎች፥ በጠቅላላም፡ የትውልዱ ምርጫ፡ ይህ፡ ኹለተኛውና የመጨረሻው የንስሓ ጽዋ ከኾነ፡ ከኹሉ ሊቀድም የሚገባው ሃይማኖታዊው ምግባራችን፡ እርስዎና እያንዳንዱ ኢትዮጵያዊ፥ እያንዳንዷም ኢትዮጵያዊት፥ ኹላችንም፡ እስካኹን ሲከማች የኖረውን፥ በየራሳችንና በየሰዉ፥ በእግዚአብሔርም ላይ የፈጸምነውን፡ የየግልና የጋራ ጥፋታችንን (ኃጢኣታችንን) ኹሉ ይደመስስልን ዘንድ፡ እየራሳችንንና ሰዉን፥ እርሱንም ፈጣሪያችንን፡ በያለንበት፡ በመንፈስና በእውነት፡ ከልባችን ይቅርታን መጠየቅ ነው፤ “ንስሓ” ማለት ይህ ነውና።

የቃል ኪዳን አምላካችንም፡ በክህደት ኃጢኣት ጸንቶ ከሚገኝ ሰው በቀር፡ ሌላውን፡ ማናቸውንም ዓይነት በደል፡ በቀኙ የተሰቀለውን ወንበዴ፡ እዚያውና ወዲያው ይቅር እንዳለው፡ በፊቱ፡ ለቅጽበት በሚቀርብ እውነተኛ ንስሓ የሚያስተሰርይ፡ ቸርና ርኅሩኅ ጌታ ስለ ኾነ፡ በቅድስት ድንግል ማርያም እናትነትና በጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ቤዛነት የተገኘው፡ ይህ "ንስሓ"፡ ኃጢኣተኛውን የሰውን ልጅ፡ ለእውነተኛዪቱ ሃይማኖትና ለእውነተኛው ምግባር አብቅቶ፡ በራሱ ውስጥ÷ በሰው ዘንድና በፈጣሪው ፊት፡ ፍጹም ንጹሕ አድርጎ ያቀርበዋል።

በዚህ ጊዜ፡ በዚህ ንስሓው አማካይነት፡ እያንዳንዱ ኢትዮጵያዊ፡ ከየራሱና እርስ በርሱ÷ ከእግዚአብሔርም ጋር ይታረቃል! ይህም ዕርቅ፡ የእግዚአብሔርን ምሕረት፡ በእያንዳንዱ ኢትዮጵያዊ ላይ ማውረድ ይጀምራል፤ በፀሓይ ንዳድ በተቃጠለ ምድር ላይ እንደሚወርድ ዝናመ ጠል ማለት ነው። ቀጥሎም፡ በፈተና ማዕበል እየተናወጠችና በመከራ እሳት እየተለበለበች የቆየችውን መላዋን ኢትዮጵያን ያጥለቀልቃታል!

ከዚህ በኋላ፡ በኢትዮጵያውያን መካከል፡ ፍቅርና ሰላም÷ ጤንነትና ብልጽግና÷ ዕረፍትና ጥጋብ ይኾናል! *"ንስሓ ከማያስፈልጋቸው፡ ከዘጠና ዘጠኝ ጻድቃን ይልቅ፡ ንስሓ በሚገባ፡ በአንድ ኃጢኣተኛ፡ በሰማይ÷ በእግዚአብሔር መላእክት ፊት፡ ደስታ ይኾናል!"* ተብሎ፡ በአምላክ አንደበት የተነገረው ቃል፡ በሰማይ፡ በእግዚአብሔር መላእክት ፊት ብቻ ሳይኾን፡ በምድርም፡ በእግዚአብሔር ሰዎች ዘንድ፡ በእርግጥ፡ ተፈጻሚነት ይኖረዋል።

የዚህ ንስሓችን እውነተኛነት፡ ለየራሳችንና ለሰው÷ ለእግዚአብሔርም፡ በሚያስተማምን ኹኔታ የሚታወቀው፡-

መጀመሪያ፡ እያንዳንዳችን፡ በእውነትና በመንፈስ ኾነን፡ በአሳብ÷ በቃልና በተግባር ከምናመልከው፡ ከእግዚአብሔር በቀር፡ የተጠመድንበት፡ ሌላ አምልኮ አለመኖሩን ስናረጋግጥ ነው፤ በውስጣችንና በመካከላችን፡ አንዳች ዓይነት ባዕድ አምልኮ ካለ፡ ያን፡ ከሰውነታችንም ኾነ፡ ከቤታችን÷ ከኅብረተሰባችንና ከአገራችን፡ ፈጥነንና ፈጽመን ማስወገድ ይገባናል፤ ከጥንት ጀምሮ፡ ምድራችን፡ ከሰብአዊም ኾነ፡ ከሰይጣናዊ አምልኮ፡ ካልጠዳች በቀር፡ እውነተኛዎቹ፡ የእግዚአብሔር ሰላምና ፍቅር÷ ደኅንነትና ብልጽግና ሊኖሩ እንደማይቻል፡ የዚሁ ሥርዓተ መንግሥታችን ድንጋጌ መላልሶ ያስታውቀናል።

ቀጥሎ፡ በጋብቻ ትዳር ላይ ያለን፡ ከትዳር ጓደኞቻችን ጋር÷ በብቸኝነት የምንኖር፡ ለየብቻችን÷ በጋብቻ፡ ትዳር መሥርተን ለመኖር የምንፈልግም፡ አብረን፡ ቅዱስ ቍርባንን ስንቀበል ነው።

በመጨረሻ፡ ቅጂያቸው፡ ከዚህ ጋር በተያያዘው፡ በኢትዮጵያውያን የሃይማኖትና የቃል ኪዳን÷ የምስጋናና የሰላምታ ጸሎታት መሠረት፡ የቅዱሱ ኪዳን ኢትዮጵያዊነታችንን የምስክርነት ቃል፡ በኢየሱስ ክርስቶስና በድንግል ማርያም መንበር ፊት፡ በይፋ ስንሰጥ ነው።

እርስዎና እርስዎን የመሰሉት፡ የመንግሥቱ ዘርፎች የኾኑት፡ የየቤቱ ተጠሪዎችና ባልደረቦቻቸው÷ መላውም የኢትዮጵያ ትውልድ፡ እንዲህ፡ በእውነተኛ ንስሓ ተመልሳችሁ፡ እንደባለቤትዎና ልጅዎ፡ እየራሳችሁን፡ ለቅዱሱ ኪዳን ኢትዮጵያዊነት ካበቃችሁ፡ እያንዳንዱ ኢትዮጵያዊና እያንዳንዷ ኢትዮጵያዊት፡ በቤተ ሕዝቡ አባልነታቸው፡ ለእግዚአብሔርዋ መንግሥት አገልግሎት፡ ተጠሪዎች የሚኾኑትን፡ "አጼ"ውን÷ ወይም፡ "ንግሥቲቱን"÷ እንዲሁም፡ የየቤቱን አለቆች ሊመርጡና እየራሳቸውም ሊመረጡ የሚችሉበትን መብት የሚቀዳጁ ይኾናሉ። እርስዎና የዛሬዪቱ ኢትዮጵያ መንግሥታዊ ሥልጣን ተሳታፊዎች ኾነው፡ አብረዎት የሚገኙት መሰሎችዎ ደግሞ፡ ኹላችሁም፡ አኹን ባላችሁበት፡ በሰብአዊው ፈሊጥና በክፋት ኃይል÷ በባዕዳኑም ጦር መሣሪያ ሳይኾን፡ በኢትዮጵያዊው፡ የእግዚአብሔር ሥርዓተ መንግሥት መሠረት፡ በመንፈስ ቅዱስ ተመርጣችሁና ተሠይማችሁ፡ እስካኹን ይዛችሁ በቆያችሁበት የክብርና የሥልጣን ማዕርግ ጸንታችሁ፡ የእግዚአብሔርን አገር፡ በእውነተኛዋ ሰላም የምታስተዳድሩ÷ የእግዚአብሔርን ሕዝብ፡ በእውነተኛዋ ፍቅር የምትጠብቁና የእግዚአብሔርን መንግሥት፡ በእውነተኛዋ እምነት የምታገለግሉ ኾናችሁ፡ ሥራችሁን ትቀጥላላችሁ።

...፴፫

ክቡር ርእሰ ብሔር!

ይህን ደብዳቤዬን ለመደምደም፡ ለኹለቱ ባለአድራሻዎች፡ የተላከውን መልእክቴን አጠቃልዬ፡ እንደሚከተለው አቀርበዋለሁ፡-

የመጀመሪያው ባለአድራሻ፡ እርስዎ ነዎት፡፡ በአኹኑ ጊዜ፡ እርስዎ፡ በርእሰ ብሔርነትዎ፡ ኢትዮጵያንና የኢትዮጵያን ሕዝብ፥ አገዛዙንም የሚወክሉ በመኾንዎ፡ አገሪቱን፡ ዛሬ ከምትገኝበት፡ እጅግ ከባድ ችግርና በዚህ ኹኔታዋ ከቀጠለች፡ ወደፊት ሊደርስባት ከሚችለው ታላቅ ውድቀት ለማዳን፡ ከማነኛችንም፡ በሕይወተ-ሥጋ ቆመን ከምንገኘው ኢትዮጵያውያንና ኢትዮጵያውያት ይልቅ፡ የበለጠውን፡ ከፍተኛ አደራና ኃላፊነት ተቀብለውና ተሸክመው ይታያሉ፡፡

ስለዚህ፡ ለአገርዎ፡ ለኢትዮጵያ፥ ደግሞም፡ ለዛሬውና ለወደፊቱ የኢትዮጵያ ትውልድ ደህንነትና ጥቅም ሲሉ፡ ዝክረ ነገራቸው፡ ቀደም ብሎ እንደተወሳው ስመ ጥሩ አባቶችዎ፡ እርስዎም፡ ዘመኑ ለጠየቀው፡ ለግላዊው፥ ለቤተሰባዊውና ለብሔራዊው የተቀደሰ ዓላማ፡ ራስዎን፡ መሥዋዕት አድርገው እንዲያቀርቡ፡ በእግዚአብሔርና በኢትዮጵያ ስም፡ እለምንዎታለሁ፡፡ መሥዋዕትነትዎም፡ ለእያንዳንዱ ኢትዮጵያዊና ለእያንዳንዷ ኢትዮጵያዊት፡ መልካም አርአያና ጥሩ ምሳሌ የመኾን ግዴታ ስላለብዎ፡ በዚህ ደብዳቤዬ ውስጥ ያተትኋቸውን ቍም ነገሮች ኹሉ፥ በተለይም፡ ከላይ ያሠፈርኋቸውን የብቅዓት ዓላማዎች፡ በቅን ልቦና አመዛዝነው፡ "ቆይ፥ ለነገ! ቆይ፥ ለተነገወዲያ!" ሳይሉ፡ ዛሬ፡ በሥጋ ጤንነትና ሕይወት እያሉ፡ በቅድሚያ፡ ራስዎን፡ ለጣፋጩ የንስሓ ፍሬ አብቅተው፡ በተግባር ላይ እንዲያውሏቸው ነው፡፡

በዚህ ጊዜ፡ እርስዎ፡ እንደቀድሞው፡ ክብርት ባለቤትዎንና ልጆችዎን፡ በመልካም ቤተሰብነት አሰባስበው፡ የጋብቻ ትዳርዎን ይቀጥላሉ፤ ኢትዮጵያና ሕዝቧም፡ እንደጥንቱ፡ በእግዚአብሔር ሥርዓተ መንግሥት እየተመሩ መተዳደራቸውን ይቀጥላሉ፡፡

ኹለተኛው ባለአድራሻ፡ የኢትዮጵያ ሕዝብ ነው፡፡ ማንነቱና ምንነቱ፡ በእርስዎ ርእሰ ብሔርነት፡ ለራሱና ለዓለሙ ኅብረተሰብ ተጋልጦ የታወቀው፡ ይህ፡ የዛሬው የኢትዮጵያ ትውልድ፡ ከነአገዛዙ፡ በወኪሉ፡ በእርስዎ አማካይነት፡ ይህ መልእክት፡ ተብራርቶ እንዲደርሰው፡ እነሆ፡ ቀርቦለታል፤ ይኸውም፡- በቅድሚያ፡ እያንዳንዱ ኢትዮጵያዊና እያንዳንዷ ኢትዮጵያዊት፡ የእርስዎን፡ የንስሓ አብነት በመከተልና ከላይ የሠፈሩትን የብቅዓት ዓላማዎች በመፈጸም፡ እየራሳቸውን፡ በእውነተኛ ንስሓ አስተካክለውና አጽድቀው፡ ከእየራሳቸውና እርስ በርሳቸው፥ ከአባታቸው፡ ከእግዚአብሔርና ከእናታቸው፡ ከኢትዮጵያ ጋር ካስታረቁ በኋላ፡ መለኮታዊው ሥርዓተ መንግሥታችን በሚደነግገው መሠረት፡ እስካኹን እንደተብራራው፡ እርስዎ፡ በ"አጼነቱ"፥ ባለቤትዎ፡ በ"እቴጌነቱ" ቀብዓት፡ ለዙፋን ትበቁ ዘንድ፥ እንዲሁም፡ ዛሬ፡ በቤተ ሕዝቡ፥ በቤተ ምልክናውና በቤተ ክህነቱ መንበሮች ላይ ተቀምጠው ያሉት፡ የአኹኖቹ ተጠሪዎች፡ እንደእርስዎ፡ እየራሳቸውንና የጋብቻ ትዳራቸውን በንስሓ አንጽተውና አስተካክለው በማጽደቅ፡ ያሉበትን ሥልጣን፡ ለ"ሥዩመ እግዚአብሔሩ" ሹመት ካበቁ፡ የቤተ ሕዝቡ ተጠሪ፡ በ"ቢትወደድነቱ"፥ የቤተ ምልክናው፡ በ"ጸሓፌ ትእዛዝነቱ"፥ የቤተ ክህነቱም፡ በ"እጨጌነቱ" ሹመትና ማዕርግ ይከብሩ ዘንድ፡ በቅዱሱ ኪዳን ኢትዮጵያዊነታቸው፡ በአንድ የተባበረ የምርጫ ድምፅ፡ ፈቃዳቸውንና ስምምነታቸውን እንዲያስታውቁ ነው፡፡

በዚህ ጊዜ፡ ምን እንደሚኾን፡ ለእርስዎና ለኢትዮጵያ ሕዝብ መንገር ያስፈልገኛልን? ካስፈለገኝ፡ ባጭሩ የምለው፡ ይህ ነው፡-

"ቀደም ብዬ እንዳወሳሁት፡ በቅድስት እናቱ ድንግል ማርያም ቃል ኪዳን ምክንያት፡ በልጇ፡ በኢየሱስ ክርስቶስ የተገኘው፡ የእግዚአብሔር ምሕረት፡ በምልዓት፡ ወደኢትዮጵያ፡ ወደምድሩዋና ወደሕዝቧ ይወርዳል።

"ኢትዮጵያውያን፡ ከጥንት ጀምሮ፡ በዓለም ሕዝቦች መካከል ያላቸው ቀዳሚነትና ታዋቂነት፥ ተከባሪነትና ተፈሪነት፥ ተወዳጅነትና ተደማጭነት፡ ባጠቃላይ፡ ከእግዚአብሔር፡ በቃል ኪዳን ያገኙት፡ ግርማ ሞገሳቸው ይመለሳል።

"ይህም ማለት፡ በዘር፡ 'ሴማዊ፥ ካማዊና ያፌታዊ' ተባብሎ፥ በቀለም፡ 'ቀይ፥ ጥቁርና ነጭ' ተባብሎ፥ በሃይማኖት፡ 'አረማዊና ይሁዲ፥ እስላምና ክርስቲያን' ተባብሎ የተከፋፈለውና የተለያየው፡ የዓለም ሕዝብ፡ ኢትዮጵያንና ኢትዮጵያውያንን የሚያውቃቸው፡ በዚህ ሥርዓተ መንግሥታቸውና ማንነታቸው ስለኾነ፡ ባገር ውስጥም ኾነ፡ በውጪው ዓለም የሚኖረው፡ ይኸው የዓለም ሕዝብ፡ እነርሱን፡ በፍቅርና በአክብሮት ዓይን ወደመመልከቱ፥ በሰላም ይዞታ ወደማስተናገዱ፥ በከፍተኛ ግምትና በልዩ ጥንቃቄ ወደማወያየቱ ደረጃ ይመለሳል ማለት ነው።

"በኢትዮጵያ ምድር ላይ፡ በድርቅ ፋንታ፡ ልምላሜ፥ በረሃብ ፋንታ፡ ጥጋብ፥ በበሽታ ፋንታ፡ ጤንነት፥ በድህነት ፋንታ፡ ብልጽግና፥ በጦርነት ፋንታ፡ ሰላም፥ በስደት ፋንታ፡ ዕረፍት ይኾናል።

"ለእያንዳንዱ ኢትዮጵያዊና ለእያንዳንዷ ኢትዮጵያዊት፡ ከሰው ሳይኾን፡ ከእግዚአብሔር የተሰጣቸው፡ የክብራቸውና የኩራታቸው ጸጋ ይመለሳል። ነጻነታቸውና መብታቸው፡ በሰው ኃይል ሳይኾን፡ በመለኮታዊው ሥርዓት ይጠበቃል።

"ሐሰት ተወግዶ፡ እውነት፥ በደልና ግፍ ተወግደው፡ ፍትሕ ርትዕ ይሰፍናሉ።

"በአጠቃላይ፡ 'ኢትዮጵያዊነት' ይነግሣል።

"እርስዎ፡ በ'አጼ'ነት ተጠሪዋ ኾነው የሚያገለግሏት፡ በኢየሱስ ክርስቶስ፡ እግዚአ ብሔርነት፥ ሊቀ ካህናትነትና ንጉሠ ነገሥትነት፥ በድንግል ማርያም፡ እመ ብሔርነት፥ መቅደስነትና ንግሥትነት የምትመራው፡ ኢትዮጵያ፡ የእግዚአብሔር መንግሥት፡ ባሕርይዋ የኾኑትን እኒህን መልካም ፍሬዎች ለማበርከት፡ በይፋ ትሰፍናለች።"

አዎን! በዚህ ጊዜ፡ "'እኛው፡ በባዕዳን የክፋት ፍልስፍና ተነሣሥተን ያጠፋነውን፡ እኛው፡ በራሳችን የደግ ሃይማኖታችን መልሰን አለማነው! ለልጆቻችንም፡ መልካሙን ውርስ ትተንላቸው ልናልፍ ነው!' ብሎ፡ ከእርስዎ ጀምሮ ያለው፡ እያንዳንዱ፡ የዚህ ትውልድ አባል፡ በፈጸመው የአገርና የወገን ፍቅር ሙያ፡ እጅግ ደስ ይለዋል!" በሚል ቃል፡ ይህን የመልእክት ደብዳቤዬን እደመድማለሁ።

የምንኖርበት ዘመን፡ የእግዚአብሔርን ምሕረት ያገኘንበት በመኾኑ፡ “ዓመተ ምሕረት” የሚለውን ስያሜ የሰጠነው ሲኾን፡ እኛ ግን፡ በክፋት ሥራችን ምክንያት፡ የቀጣት አድርገነው ያቆየንበትን የጥፋት አካኼዳችንን፡ አኹን፡ በእውነተኛ ንስሓችን፡ ወደመልካሙ ልማት የምንመልሰው ከኾነ፡ አዲሱ ዓመት፡ የዚህን ሃይማኖታዊ ምግባራችንን መከር የምንሰበስብበት ሊኾን ይችላልና፡ በእኔ በኩል ላለው፡ ለዚህ ምኞቴና ጸሎቴ፡ መገለጫ ይኾን ዘንድ፡ አገልግሎታችን ያዘጋጀውን፡ የ፲፱፻፺፪ ዓመተ ምሕረት ቀን መቁጠሪያ፡ ከዚህ ጋር አባሪ አድርጌ፡ በአክብሮት ልኬልዎታለሁ፡፡

በዚህ ግልጽ ደብዳቤዬ ውስጥ ለተጠቀሱት ቍምነገሮች፥ ስለእርስዎ ለሡነዘርኋቸው አስተያየቶች ጭምር፡ ራሴ ከማውቀው በቀር፡ መነሻ የኾነኝን እውነታ፡ ያገኘሁት፡ “ድሮና ዘንድሮ” ከሚለው መጽሓፍዎ መኾኑን፡ አስቀድሜ ግልጽ ያደረግሁ ይመስለኛል፡፡ ይኸው መጽሓፍዎ፡ በሽያጭ መልክ፡ ለሕዝብ፡ በይፋ የተሠራጨ እንደመኾኑ መጠን፡ እኔም፡ የዚህኑ መጽሓፍዎን ፈለግ በመከተል፡ በዚህ ግልጽ ደብዳቤዬ አማካይነት ያቀረብሁትን፡ ይህን፡ የማብራሪያ መልስና መልእክት፡ እርስዎ ብቻ ሳይኾኑ፡ መላው የኢትዮጵያ ሕዝብ፥ ጉዳዩ የሚመለከታቸውም፡ ባለቤትዎና ልጅዎ፥ እንዲሁም፡ እንደሥርዓተ መንግሥታችን፡ የቤተ ሕዝቡ፥ የቤተ ክህነቱና የቤተ ምልክናው ተጠሪዎች ጭምር ሊያውቁት የሚገባ በመኾኑ፡ ቅጂው፡ ለእነርሱና ለዜና ማሠራጫዎች እንዲደርስ ማድረጌን፡ በትሕትና እገልጻለሁ፡፡

አክባሪዎ፡-

______________________________

ንቡረ እድ ኤርምያስ ከበደ ወልደ-ኢየሱስ
የአገልግሎቱ ተጠሪ

ግልባጭ፡-

የልዑል እግዚአብሔር፡ የቃል ኪዳን ወገን ለኾነው፡
ለተከበረውና ለተወደደው፡ የኢትዮጵያ ሕዝብ፥
በኢትኦጵ ጦማረ ሕዝብና መጽሔት አማካይነት፥
አዲስ አበባ፤ ኢትዮጵያ፡፡

ለክቡር አቶ ዳዊት ዮሓንስ፥
የኢትዮጵያ ቤተ ሕዝብ አፈ ጉባኤ፤
ለክቡር አቶ መለስ ዜናዊ፥
የኢትዮጵያ ቤተ ምልክና ጠቅላይ ምሉክ፤
ለብፁዕ አባ ጳውሎስ፥
የኢትዮጵያ ቤተ ክህነት እጨጌ፤
አዲስ አበባ፤ ኢትዮጵያ፡፡

ለክቡር አቶ ካሣሁን አየለ፤
የኢትዮጵያ መንግሥት እንደራሴ፤
ዋሽንግተን፥ ዲሲ፤ ዩ.ኤስ.ኤ.

ለክብርት ኪዳናዊት ወይዘሮ ሳሌም ጳውሎስ ምንአመኖ፤
ለተወዳጁ ኪዳናዊ መሓንዲስ ሶምሶን ግርማ ወልደጊዮርጊስ፤
በያሉበት፡፡

## <u>የኢትዮጵያውያን</u>

## <u>የሃይማኖት ጸሎት</u>

እኛ ኢትዮጵያውያን፡ ኹሉን በያዘ፥ ሰማይንና ምድርን፥ የሚታየውንና የማይታየውን በፈጠረ፡ አንድ አምላክ በሚኾን፡ በእግዚአብሔር አብ እናምናለን።

ዓለም ሳይፈጠር፡ ከእርሱ ጋራ በነበረ፥ አንድ የአብ ልጅ፥ አንድ ጌታ በሚኾን፡ በእግዚአብሔር ወልድም እናምናለን። እርሱም፡ ከብርሃን የተገኘ ብርሃን፥ ከእውነተኛ አምላክ የተገኘ አምላክ፥ የተወለደ እንጂ ያልተፈጠረ፥ በመለኮቱ፡ ከአብ ጋራ የሚተካከል፥ ኹሉ በእርሱ የኾነው ኢየሱስ ክርስቶስ ነው። በሰማይ ካለው፥ በምድርም ካለው፡ ያለእርሱ ምንም ምን የኾነ የለም። ስለእኛ ስለሰዎች፥ እኛን ለማዳን፡ ከሰማይ ወረደ፤ በመንፈስ ቅዱስ ግብር፡ ከቅድስት ድንግል ማርያም፡ ከሥጋዋ ሥጋ፥ ከነፍሷ ነፍስ ነሥቶ፡ ፍጹም ሰው ኾነ። በጴንጤናዊው ጲላጦስ ዘመን፡ ስለእኛ መከራን ተቀበለ። ተሰቀለ። ሞተ። ተቀበረ። በሦስተኛውም ቀን፡ ከሙታን ተለይቶ ተነሣ። በክብር በምስጋና ወደሰማይ ዐረገ። በአባቱም ቀኝ፡ በዙፋኑ ተቀመጠ። ዳግመኛም፡ በሕያዋንና በሙታን ለመፍረድ፡ በምስጋና ይመለሳል። ለመንግሥቱ ፍጻሜ የለውም።

በእግዚአብሔር መንፈስ ቅዱስም እናምናለን። እርሱም፡ ሕይወትን የሚሰጥ፥ ከአብ የሠረፀና በነቢያት አድሮ የተናገረው፥ በሐዋርያት ላይ የወረደውና በኢየሱስ ክርስቶስ ቤዛነት፡ ዓለሙን በጸጋው የሞላው፡ ቅዱሱ የእውነት መንፈስ ነው። ለእርሱም፡ ከአብና ከወልድ ጋራ፡ በአንድነት እንሰግድለታለን፤ እናመሰግነዋለንም።

ኢየሱስ ክርስቶስ፡ በአበው ልቦና በመሠረታት፥ በነቢያት ቃል ባጸናትና በሐዋርያት ጉባዔ በፈጸማት፥ የእርሱ ሥጋና ደም፡ ለመሥዋዕትነት በሚቀርብባትና የመንፈስ ቅዱስ ጸጋዎች በሚሰጡባት፡ በአንዲት ቅድስት ቤተ ክርስቲያን እናምናለን።

ኃጢአት በሚሠረይባት፡ በአንዲት ጥምቀት እናምናለን።

የሙታንን መነሣት፥ የሚመጣውንም ሕይወት ተስፋ እናደርጋለን።

ለዘለዓለሙ፥ አሜን።




መልእ. ሣ. ቁ. ፰፻፲፪፤ ስልክ ቁ. ፲፮-፲፰-፹፭፤ ፳-00-፹፭፤ አዲስ አበባ፤ ኢትዮጵያ።
P. O. Box 812, Tel. Nos. 16-18-85; 20-00-85, Addis Abeba, Ethiopia.
P.O.Box 43262, Washington, DC 20010-9262 U.S.A.
Tel. (301) 587-8074 ~ Fax: 301-587-1971 ~ E-mail: ekogyesus@aol.com
Website: www.ethkogserv.org

# <u>የኢትዮጵያውያን</u>

## <u>የቃል ኪዳን ጸሎት</u>

እኛ ኢትዮጵያውያን፡ እግዚአብሔር ለሰው ልጆች፡ የሰጣቸውን ቃል ኪዳናት፡ ጠብቆ በኖረው፡ በቅዱሱ ኪዳን ኢትዮጵያዊነታችን እናምናለን፡፡

አምላካችን፡ ይህን ኢትዮጵያዊ ሰውነት፡ **በመጀመሪያው የአበው ዘመን፡** በአዳምና ሔዋን ሥርዓተ ጋብቻ፡ **በኪዳነ ልቦና መሠረተው፤** ከዚያም፡ በኖኅ ቀስተ ደመና፥ በመልከ ጼዴቅ ቁርባንና በአብርሃም ግርዛት፡ ገንብቶ አሳደገው፤ **በመካከለኛውም የሕግ ዘመን፡** በሙሴ ጽላትና በዳዊት ዙፋን አዋቅሮ፥ የኢትዮጵያዊቷን ንግሥት፡ የማክዳንና የእስራኤላዊዉን ንጉሥ፡ የሰሎሞንን የዘር ሓረጎች በማዋሃድ፡ በኪዳነ ኦሪት አከናወነው፤ **በመጨረሻውም የሕይወት ዘመን፡** ከዚህ ምሉእ ትውልድ ከተገኘችው፡ ከድንግል ማርያም በተወለደው ልጁ፡ በኢየሱስ ክርስቶስ ሥጋና ደም አጽንቶና ዘለዓለማዊዉን ዘውድ አቀዳጅቶ፡ በኪዳነ መንፈስ ቅዱስ ፈጸመው፡፡ ኢትዮጵያ፡ እንዲህ በቀጠለው፡ በቅዱሱ ኪዳን ኢትዮጵያዊው ሰውነት፡ ቤተ ሕዝቧን፥ ቤተ ክህነቷንና ቤተ ምልክናዋን አንድ አድርጋ የኖረች፡ የእግዚአብሔር መንግሥት እንደኾነች እናምናለን፡፡

እርሱ፡ "ክርስቶስ" ተብሎ፡ እኛን "ክርስቲያን" ያሰኘን፡ ኢየሱስ ክርስቶስ፡ በቀደመው ዘመን፡ ምሳሌው ኾኖ በተገለጠው፡ በመልከ ጼዴቅ ኢትዮጵያዊነትና ሹመት፡ ከሴም፥ ከካምና ከያፌት ዘሮች ተወልዶ፡ የዘለዓለም ካህናችንና ንጉሣችን እንደኾነ እናምናለን፡፡

እርሷ "ኢትዮጵያ" ተብላ፡ እኛን "ኢትዮጵያውያን" ያሰኘችን፡ ድንግል ማርያም፡ አምላክን በመውለዷ፡ አማናዊቷ የሕያዋን እናትና ዘለዓለማዊቷ ታቦተ ጽዮን፥ የሰማይና የምድር ንግሥትም እንደኾነች እናምናለን፡፡

አረንጓዴ ብጫ ቀይ የኾነው፡ የቀስተ ደመና ምልክት፡ በኖኅ አማካይነት፡ ከእግዚአብሔር የተቀበልነው፡ የዘለዓለም ሰንደቅ ዓላማችን እንደኾነ እናምናለን፡፡

የቅዱሱ ኪዳን ፍጻሜ ለኾነው፡ ለኢየሱስ ክርስቶስ የተነገረው፡ "ሞአ አንበሳ ዘእምነገደ ይሁዳ" የሚለው፡ መለኮታዊ ቃልና ለድንግል ማርያም የተነገረው፡ "ኢትዮጵያ ታበጽሕ እደዊሃ ኀበ እግዚአብሔር" የሚለው ትንቢታዊ ቃል፡ ከአምላካችን ያገኘነው፡ የዘለዓለም ማኅተማችን እንደኾነ እናምናለን፡፡

በቅዱሱ ኪዳን ጸጋ፡ ከእግዚአብሔር በመንፈስ፡ የመወለድን ክብር ስላገኘን፡ በዚህ ልጅነታችን፡ የእግዚአብሔር መንግሥት ወራሾችና አገልጋዮች እንደኾንን እናምናለን፡፡

ይህን ልጅነታችንን፡ አጽንተን ለመጠበቅ፥ የመንግሥቱ ወራሽነታችንን ለማረጋገጥና ንጹሕ አገልግሎታችንን ለመቀጠል፡ ኃጢአታችንን ዘወትር፡ በንስሓ እያጠራንና የክርስቶስን ሥጋና ደም እየተቀበልን መኖር እንዳለብን እናምናለን፡፡

የኢትዮጵያዊነት ሃይማኖታችን፡ በይፋ የሚገለጠውና ተለይቶ የሚታወቀው፡ በኢየሱስ ክርስቶስና በድንግል ማርያም ፍቅር ኾነን በምንፈጽመው፡ የኢትዮጵያዊነት ምግባራችን እንደኾነ እናምናለን፡፡

የቅዱሱ ኪዳን ኢትዮጵያዊነታችንን፡ በየልቦናችን ጽፎ ያስተማረን፥ ጠብቀነው እንድንኖር ያደረገም፡ እንደቃል ኪዳኑ፡ እግዚአብሔር እንደኾነ እናምናለን፡፡ ለዘለዓለሙ፤ አሜን፡፡

## ኢትዮጵያውያን:

## ለእግዚአብሔር የሚያቀርቡት: የምስጋና ጸሎት::

አባታችን እግዚአብሔር ሆይ! “እናንተ ስትጸልዩ: ፡አቡነ ዘበሰማያት! ይትቀደስ ስምከ፤ ትምጻእ መንግሥትከ፤ ወይኩን ፈቃድከ፥ በከመ በሰማይ፥ከማሁ በምድር፤ ሲሳየነ፥ ዘለለዕለትነ፥ ሀበነ ዮም፤ ሕድግ ለነ፥ አበሳነ፥ ወጌጋየነ፥ ከመ ንሕነኒ ንሕድግ: ለዘአበሰ ለነ፤ ኢታብአነ እግዚኦ: ውስተ መንሱት፤ አላ አድኅነነ፥ ወባልሃነ እምኵሉ እኩይ፤ እስመ ዚአከ ይእቲ መንግሥት፥ ኃይል ወስብሓት፤ ለዓለመ ዓለም!: በሉ!” ብሎ: ልጅህ ኢየሱስ ክርስቶስ: ያስተማረንን ጸሎታችንን: በእርሱው ቤዛነት ተቀብለህ: ለነፍሳችንና ለሥጋችን: ቸርነትህን አበረከትክልን፤ ምሕረትህን አደረግህልን፤ ፍቅርህን ፈጸምክልን፤ ጸጋህንም ሰጠኸን:: ስለዚህ እናመሰግንሃለን::

ከቅድስት ድንግል ማርያም: በተወለደው ልጅህ መድኃኒትነት: የመንፈስ ቅዱስ ጸጋ: በዓለሙ ኹሉ ወረደልን:: ስለዚህ: በሰማይ ብቻ ሳይኾን: ዛሬ በምድርም የምትኖር ኾንህ:: ስምህ: በምድርም ተቀደሰ:: መንግሥትህም መጣችልን:: በሰማይ የኾነው ፈቃድህ: በምድርም እንዲሁ ኾነ::

የዕለት እንጀራችንን ብቻ ሳይኾን: በዕድሜያችን ኹሉ የሚያስፈልገንን ምግበ ሥጋ: በሥነ ፍጥረት አዘጋጀህልን:: ለዘላለም ሕያዋን የሚያደርገንን፥ መድኃኒትና ምግበ ነፍስ የኾነንን: የልጅህን ቅዱስ ሥጋና ክቡር ደም: ለዘወትር ሰጠኸን:: በእርሱም: ኃጢአታችንንና በደላችንን ኹሉ: ለመቼውም ጊዜ ደምስሰህ: ፈጽመህ ይቅር አልኸን:: እኛም የበደሉንን ኹሉ: እንዲሁ ይቅር እንድንል አስቻልኸን::

ያንተ ልጆች ለመኾን የምንበቃበትን: የጥምቀትን ልደትና የንስሓን ጸጋ አደልኸን::

ከማናቸውም ፈተና አውጥተኸንና ከክፉው ኹሉ አድነኸን፥ ዲያብሎስንና ሞትንም ድል አድርገህ: በትንሣኤህ ሕይወት ለመኖር አበቃኸን::

ጌታ ሆይ! ሊነገር ስለማይቻል ቸርነትህና ምሕረትህ፥ ፍቅርህና ጸጋህ፥ እንዲሁም የሚያስፈልገንን ኹሉ: ሳንለምንህ ስለምትሰጠን: ዘወትር እናመሰግንሃለን::

“ሞአ አንበሳ ዘእምነገደ ይሁዳ” በተባለው: በንጉሣችን በኢየሱስ ክርስቶስ: ዛሬ የምንኖርባት: የእውነት መንግሥትህ: ክፉትን፥ ኃጢአትንና ሞትን: ፈጽማ አጥፍታ: ለግዙፉ ዓለም: በገሃድ የምትገለጥበትንና በይፋ የምትሰፍንበትን ጊዜ: እንደተስፋ ቃልህ እንጠብቃለን::

ኃይልና ምስጋና፥ መንግሥትም ያንተ ናቸው፤ ዛሬም፥ ዘወትርም፥ ለዘለዓለሙ፤ አሜን::

## ኢትዮጵያውያን

## ለድንግል ማርያም የሚያቀርቡት፡ የሰላምታ ጸሎት፡፡

እናታችን ማርያም ሆይ! በመልአኩ በቅዱስ ገብርኤል ሰላምታ፡ “ሰላም!” እንልሻለን፡፡ በአሳብሽ ድንግል ነሽ፤ በሥጋሽም ድንግል ነሽ፡፡ በዚህ የንጽሕና ባሕርይሽ፡ የአሸናፊው የእግዚአብሔር እናት ኾነሻልና፡ ሰላምታ ላንቺ ይገባል፡፡

ማኅጸንሽ፡ የሕይወት ዛፍ ፍሬ የኾነውን፡ ቅዱሱን አዳም ስላስገኘ፡ አንቺ፡ ከሴቶች ኹሉ ተለይተሽ፡ የተባረክሽ፡ ቅድስቲቱ ሔዋን ነሽ፡፡ ቀድሞ በነቢያት፡ “ኢትዮጵያ ታበጽሕ እደዊሃ ኀበ እግዚአብሔር” የተባልሽ፥ እኛም፡ “እምነ ጽዮን” ስንልሽ የኖርን፡ በሰማይና በምድር፡ ንግሥታችን ሆይ! ደስ ይበልሽ፡፡

እግዚአብሔር አንቺን፡ የድኅነታችን ምክንያት አድርጎ፡ ኪዳነ ምሕረቱን ለዘለዓለም ፈጽሟልና፡ “ጸጋን የተመላሽ፡ ብፅዕት ነሽ” እያልን፡ ዘወትር እናወድስሻለን፡፡

በአምላካችንና በመድኃኒታችን፡ በኢየሱስ ክርስቶስ፡ አንቺ ለእኛ፡ የአደራ እናታችን፥ እኛም ለአንቺ፡ የአደራ ልጆችሽ ነንና፡ ከተወደደው ልጅሽ፡ ያልተለየው እናትነትሽ፡ ከእኛም፡ ምንጊዜም እንደማይለየን እናምናለን፡፡ ይህን ያደረገ፡ ቸሩ አባታችን፡ ልዑል እግዚአብሔርን እናመሰግነዋለን፡፡ ለዘለዓለሙ፤ አሜን፡፡



ሞአ    አንበሳ    ዘእምነገደ    ይሁዳ
ኢየሱስ ክርስቶስ
ካህኑ ለዓለም፥ ንጉሠ ጽዮን
ወንጉሠ ነገሥት ዘኢትዮጵያ
The Conquering Lion of the Tribe of Judah
Jesus Christ
Eternal Priest, King of Zion and
King of Kings of Ethiopia

ኢትዮጵያ ታበጽሕ እደዊሃ ኀበ እግዚአብሔር
ድንግል ማርያም
እሙ ወእምነ፥ ንግሥተ ጽዮን
ወንግሥተ ነገሥታት ዘኢትዮጵያ
Ethiopia stretches out Her Hands to God
The Virgin Mary
Mother of God and Our Holy Mother
Queen of Zion and Ethiopia

# የኢትዮጵያዊ/ት የቃል ኪዳን ምስክርነት

በስመ አብ ወወልድ ወመንፈስ ቅዱስ፡ አሐዱ አምላክ፤ አሜን።

እኔ፡ ከአባቴ፡ ከ ________________ ወስመ ጥምቀቱ________________
ከእናቴ፡ ከ ________________ ወስመ ጥምቀታ ________________
በ________________ ቀን፥ ፲፱፻ ______ ዓ.ም. በ________________
በተወለድኩበት የሥጋ ልደት፡ ________________የተባልሁ፥ በ________________
________________ቤተ ክርስቲያን፡ በሥርዓተ ጥምቀት፡ ከእግዚአብሔር ዳግመኛ የመወለድን ክብር በአገኘሁበት የመንፈስ ልደት፡ ________________የተባልሁ ኢትዮጵያዊ/ት፡

በኢትዮጵያውያን የቃል ኪዳንና የሃይማኖት ጸሎቶች ውስጥ እንደተገለጸው፡ በአዳምና ሔዋን ተጀምሮ፡ በኖኅ፥ በመልከ ጼዴቅ፥ በአብርሃም፥ በሙሴና በዳዊት በኩል እየታደሰ፡ እስከኢየሱስ ክርስቶስና ድንግል ማርያም ደርሶ በተፈጸመው፡ በእግዚአብሔርና በሰው መካከል የተደረጉትን እነዚህን ሰባቱን ኪዳናት በአጠቃለለው፡ በቅዱሱ ኪዳን ተመሥርታ የቆመችውን፡ በምሥጢረ ተዋህዶ የጠራችውንና የቀናችውን ሃይማኖቴን ጠብቄና በምግባር አጽንቼ፡ ራሴን በንስሓና በሥጋ ወደሙ እያጸደቅሁ የምኖር የቅዱሱ ኪዳን ኢትዮጵያዊ/ት መሆኔን፡ ዛሬ፡ በኢየሱስ ክርስቶስና በድንግል ማርያም ዙፋን ፊት፡ በእውነተኛው መንፈሳዊ አምልኮት ቆሜ በምሰጠው፡ በዚህ የቃል ኪዳን ምስክርነቴ አረጋግጣለሁ።

አምላካችንና መድኃኒታችን፥ ካህናችንና ንጉሣችን ኢየሱስ ክርስቶስ ሆይ! “በሰው ፊት፡ በእኔ አምኖ ለሚመሰክርልኝ ሁሉ፡ እኔ ደግሞ በሰማያት በአለው አባቴ ፊት፡ ስለታማኝነቱ እመሰክርለታለሁ። በሰው ፊት የሚክደኝንም፡ እኔ ደግሞ በሰማያት በአለው አባቴ ፊት፡ ስለክህደቱ እመሰክርበታለሁ።” ያልከውን መለኮታዊ ቃልህን አምኜ፡ በቅዱሱ ኪዳን ኢትዮጵያዊነቴ፡ ይህን የምስክርነት ቃል፡ በይፋ እንድሰጥ ስላበቃኸኝ፡ በመንበርህ ፊት እየሰገድኩ፡ አመሰግንሃለሁ።

እናታችንና አገራችን፥ ጽዮናችና ንግሥታችን ቅድስት ድንግል ማርያም ሆይ! በቅዱሱ ኪዳን ኢትዮጵያዊነቴ ጸንቼ እኖር ዘንድ፡ በፍቅርሽና በረድዔትሽ ስላልተለየሽኝ፡ በመልአኩ በቅዱስ ገብርኤል ቃል፡ የምስጋና ሰላምታዬን አቀርብልሻለሁ። አሜን።

________________ ቀን፥ ፲፱፻፺ ______ ዓ.ም.

ኢትዮጵያ፡ የእግዚአብሔር መንግሥት አገልግሎት። መልእ.ሣ.ቁ. ፰፻፲፪። ስልክ ቁ. ፲፮-፲፰-፹፭። አዲስ አበባ፣ ኢትዮጵያ።
Ethiopia: The Kingdom of God Services, P.O.Box 812, Tel. No. 16-18-85 Addis Abeba, Ethiopia.
P.O.Box 43262, Washington, DC 20010-9262 U.S.A.
Tel. (301) 587-8074 Fax: 301-587-1971 E-mail: ekogyesus@aol.com Website: http://members.aol.com/ekogyesus